# ኤዱኬሽን ፎር
# ሰስተነብል ዲቨለፕመንት

## ሞጁል አራት

# የልዩ ፍላጎት/ አካቶ ትምህርት
# Special Needs/Inclusive Education



## የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን
## ስልጠና ሞጁል


ጥቅምት 2004 ዓ.ም
አዲስ አበባ


FEAT

ESD

# ኢዱኬሽን ፎር ሰስተነብል ደቨሎፕመንት

# ልዩ ፍላጎት/ አካቶ ትምህርት

## Special Needs/Inclusive Education

## የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን ስልጠና ሞጁል

**አማካሪ፡** ፍሮምሲስ የትምህርትና ስልጠና አ.ማ

**አዘጋጅ ፡** ዓለሙ አበራ ባቢሶ

## ምስጋና

ይህ ሞጁል የተዘጋጀዉ በፍሮምሲስ  የትምህርትና ስልጠና አ.ማ እና በኢዱኬሽን ፎር ሰስተነብል ዲቨለፐመንት ትብብር ሲሆን ለዚህም  ማህበሩ ለኢዱኬሽን ፎር ሰስተነብል ዲቨለፐመንት ከፍ ያለ ምስጋና ያቀርባል፡፡ በተለይም በፍሮምሲስ  የትምህርትና ስልጠና አ.ማ ስር ሆነዉ በሞጁል ዝግጅትና በስልጠ በየሞያ ዘርፋቸዉ አስተዋፅኦ ያደረጉትን ባለሙያዎች ከልብ ያመሰግናል ፡፡

በመጨረሻም የኢዱኬሽን ፎር ሰስተነብል ዲቨለፐመንት ሰራተኞች ለስልጠናዉ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን በማስተካከል ስልጠናዉ የተሳካ እንዲሆን ላደረጉት አስተዋፅኦ ማህበሩ  ምስጋናዉን ያቀራባል፡፡

## ማውጫ


ምስጋና ........ iii

መግቢያ ........ v

የትምህርቱ  አስፈላጊነት ........ v

የሞጁሉ ይዘቶች በአጭሩ ........ vi

የሞጁሉ አጠቃቀም ዘዴዎች ........ vi

ምዕራፍ አንድ ........ 2

የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፅንሰ ሃሳብ ........ 2

1.1 መግቢያ ........ 2

1.2  የልዩ ፍላጎት ትምህርት ታሪካዊ እድገት ........ 4

1.2.1 የልዩ ፍላጎት ትምህርት ታሪካዊ እድገት በአለም አቀፍ ደረጃ ........ 4

1.2.2  የልዩ ፍላጎት ትምህርት ታሪካዊ እድገት በኢትዮጵያ ደረጃ ........ 8

1.3 ልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት አሰጣጥና አደረጃጀት ........ 10

1.4 ልዩ የመማር ማስተማረው ስልት የሚያስፈልጋቸው የጉዳት አይነቶች ........ 11

**2.2** የተለያዩ ጉዳቶች ያሉባቸው ህፃናትን ማስተማር ........ 16

2.2.1 ማየት የተሳናቸው ሕፃናት ........ 17

2.2.2 መስማት የተሳናቸው ሕፃናት ........ 25

2.2.3 የአእምሮ ውስንነት ያለባቸው ሕፃናት ........ 34

2.2.4 የአካል/የእንቅስቃሴና የጤንነት ጉዳት ........ 46

2.2.5 የመግባባትና የቋንቋ ችግር ያለባቸው ሕፃናት ........ 58

2.2.7 የመማር ችግር (Learning Deficiency) ያለባቸው ሕፃናት ........ 68

2.2.8 የአካባቢያዊና ባህላዊ ተፅዕኖ ያለባቸው ሕፃናት ........ 71

2.2.9 ተደራራቢ የአካል ጉዳቶች ያለባቸው ህፃናት ........ 75

2.3 ልዩ ተሰጥኦ ችሎታ ያላቸው ህፃናት ........ 77

የዋቤ መጽሐፍት (References) ........ 87

## መግቢያ

ይህ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ሞጁል በቅድመ መደበኛ መዋዕለ ሕፃናት ደረጃ ለሚያስተምሩ ዕጩ ሠልጣኝ መምህራን የተዘጋጀ ነው:: ለሕፃናት የሚያስፈልጉ ነገሮችን አሟልተን አስፈላጊውን እገዛ ከመስጠታችን በፊት እእነርሱን መረዳት ቅድሚያ የሚሰጣው ጉዳይ ነው:: ስለዚህ በቅድመ መደበኛ መዋዕለ ሕፃናት ደረጃ የሚያስተምሩ መምህራን ሕፃናትን ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት እነርሱን በመረዳት አስፈላጊውን እእገዛና ድጋፍ እየሰጡ እንዲያስተምሩ ስለልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት መረጃ በማግኘት ሕፃናትን ለማስተማር የሚያስችሉ እውቀት፣ ችሎታና ክህሎት ማዳበር ከሁሉም ቅድሚያ የሚሠጠው ጉዳይ ስለሆነ ይህ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ሞጁል ተዘጋጅቷል።

የሰው ልጅ እንደየሰብዕናው የተለያዩ ፍላጎቶች አሉት:: እነዚህ ፍላጎቶችን አሟልቶ የተስተካከለ ሰብዕና ኖሮት በአካላዊ፣ በአዕምሮአዊና በሥነ ልቦናዊ ዕድገቱ የተስካከለ ብቁ፣ ንቁና ምርታማ ዜጋ እንዲሆን ማድረግ የሚቻለው ከህጻንነት ጊዜ ጀምሮ ስለሆነ ሕፃናትን ከመዋዕለ ሕፃናት ዕድሜ ጀምሮ በትምህርት ኮትኩቶ ማሳደግ የሚቻለው ፍላጎታቸውን በመረዳት፣ በመለየትና በማገዝ እንነደሆነ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ሳይንስ ያረጋግጣል::

ስለዚህ በቅድመ መደበኛ ትምህርት ዕጩ መምህርነት የሚሠለጥኑ ሠልጣኞች የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርትን በመማር ሠልጥነው በቅድመ መደበኛ ትምህርት በመምህርነት ሲመደቡ ሕፃናትን በመረዳት አሰፈላጊውን ድጋፍና እእገዛ በማድረግ የሚያስትምሩበትን ዕውቀት፣ ችሎታና ክህሎት አዳብረው ይወጣሉ:: በተግባርም ያውላሉ::

## የትምህርቱ አስፈላጊነት

ይህ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት እንዲዘጋጅ ያስፈለገበት ምክንያት በቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህርነት የሚሠለጥኑ ዕጩ መምህራን ስለልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ምንነት በመረዳት በሕፃናት መካከል የሚኖሩትን የችሎታና የፍላጎት ልዩነቶች በማወቅና ሕፃናትን በመረዳት አሰፈላጊውን ድጋፍና እእገዛ በማድረግ የሚያስትምሩበትን ዕውቀት፣ ችሎታና ክህሎት እንዲያዳበሩና በተግባርም እንዲያውሉ ነው::

## የሞጁሉ ይዘቶች በአጭሩ

ይህ ለቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን ስልጠና የተዘጋጀ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ሞጁል ሁለት ትላልቅ ምዕራፎች አሉት፡፡ ምዕራፎቹም በውስጣቸው በንኡሳን ክፍሎች የተከፋፈሉ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ ስለልዩ ፍላጎት ትምህርት ጽንሰሀሳብ ፣ስለ ዩ ፍላጎት ተምህርት ታሪካዊ ዕድገት፣’ ስለ ልዩ ፍለጎት ትምህርት አገልግሎት አሰጣጥና አደረጃጀት፤ ልዩ የመማር ማስተማር ስልት የሚያስፈልጋቸው ጉዳት አይነቶችን ሸፍኗል፡፡ምእራፍ ሁለት በተለይ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ህፃናት እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ያትታል። ይህ ምእራፍ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ልጆች እነማን እንደሆኑና እነርሱንም ማስተማር የሚቻልበትን ሁኔታ የሚያስረዳ ነው።

**የሞጁሉ አቀራረብ**

ከላይ እንደተጠቀሰው ይህ በልዩ ፍላጎት/ አካቶ ትምህርት ለቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን ስልጠና የተዘጋጀ ሞጁል ሁለት ትላልቅ ምዕራፎች ያሉት ሲሆን የሞጁሉ አቀራረብ በየምዕራፉ መጨረሻ ላይ ተግባር ተኮር በሆኑ መልመጃዎች የተደገፈ ነው፡፡

## የሞጁሉ አጠቃቀም ዘዴዎች

ሠልጣኞች ሞጁሉን ሲቀጠቀሙ መከተል የሚገባቸው ዘዴዎች፡-

- ♥ በመጀመሪያ ገረፍ ገረፍ አድርገው ማንበብ፣
- ♥ መልሰው መከለስ፣
- ♥ ግልጽ ያልሆኑና አዲስ ሐረጎችንና ቃላቶችን ለይተው በማውጣት ከጓደኛ ጋር መነጋገርና መረዳት፣
- ♥ ጽንሰ ሀሳቦችን መረዳትና ከነባራዊና ከአካባቢያችን ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ መረዳት፣
- ♥ በየርዕሶቹ መጨረሻ የተቀመጡ መልመጃዎችን መሥራት፣

## ምዕራፍ አንድ

## የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፅንሰ ሃሳብ

### 1.1 መግቢያ

ውድ የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች እንኳን ለቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን ሥልጠና የተዘጋጀውን የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ሞጁል ምዕራፍ አንድ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፅንሰ ሃሳብ (ምንነት) ለማንበብ አበቃችሁ። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሰው ልጅ የትምህርት አቀባበል ሂደትን፣ ከትምህርት አኳያ የልዩ ፍላጎት ትምህርት የተባለበት ምክንያትን፣ስለ ልዩ ፍላጎት ምንነትና ትርጉም፣ ስለ ልዩ ፍላጎት ትምህርት ታሪካዊእድገት ትረዳላችሁ:: በተጨማሪም ስለ ምዕራፉ ዓላማዎችና አተገባበራቸው በሚገባ ትገነዘባላችሁ::

**የምዕራፉ አላማዎችና ግቦች፡-**

ሠልጣኞች ይህንን ምዕራፍ ሲጨርሱ፡-

- የልዩ ፍላጎት ትምህርት ጽንሰሀሳብን ያውቃሉ፣
- በሰው ልጅ የትምህርት አቀባበል ሂደት ላይ ያለውን ልዩነት ይረዳሉ፣
- ከትምህርት አኳያ የልዩ ፍላጎት ትምህርት የተባለበትን ምክንያት ይገነዘባሉ፣
- ስለ ልዩ ፍላጎት ትምህርት ታታሪካዊእአድገት ይረዳሉ፣
- ስለልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት አሠጣጥና አደረጃጀት ያውቃለ፣

ይህ ምዕራፍ በአራት ንዑሳን ክፍሎች ተከፍሏል።:: እነርሱም፡-

- ♥ የምዕራፉ መግቢያ፣
- ♥ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ታታሪካዊ እእድገት፣
- ♥ የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት አሠጣጥና አደረጃጀት፣
- ♥ ልዩ የመማር ማስተማር ስልት የሚያስፈልጋቸው የጉዳት ዓይነቶች የሚሉት ናቸው።

የሰው ልጅ በትምህርት አቀባበል ሂደት አንዱ ፈጥኖ የሚገነዘብ (Children with superior ability)፣ ሌላው አማካይ የትምህርት አቀባበል ክህሎት ያለው (Children with average ability) ሆኖ፣ ሌላው ደግሞ ከዕድሜ ጓደኞቹ ጋር ለመራመድ የሚቸገር (Children with certain disability) ሊሆን ይችላል:: በዚሁ ሁኔታ  ላይ ያሉ ሁሉ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ልዩ ህፃናት (exceptional children) በመባል ይጠራሉ::

የልዩ ፍላጎት ትምህርትም የእነዚህን ህፃናት/ሰዎች ፍላጎት የሚዳስስ፣ ለማሟላትና ለማርካት የሚሞክር የመደበኛ ትምህርት አካል ነው:: ስለልዩ ፍላጎት ትምህርት መጻፍ የተጀመረው እ.ኤ.አ. በ1950ዎቹ ነው:: በጅምሩም የልዩ ፍላጎት ትምህርት ዓላማም በግልፅ በሚታይ የአካልና የአእምሮ  ጉዳት ላይ ያተኩረ እንደነበር አንዳንድ ጽሑፎች ይጠቁማሉ::

የኋላ ኋላ በዚህ ዙሪያ የሚመራመሩ ባለሙያዎች በዓለም ላይ ሲኖሩ ራሳቸውን ከአካባቢያቸው ጋር ማዋሃድ፣ አካባቢያቸውን መጥቀምና መጠቀም የሚሳናቸው ግልፅ ጉዳት ያለባቸው ብቻ ሳይሆኑ ችግራቸው በአይን የማይታይ ጉዳተኞችም እንዳሉ በመገንዘብ የትምህርት ክፍሉን ልዩ ፍላጎት ትምህርት በማለት ሰይመውታል።::

ከትምህርት አኳያ ልዩ ፍላጎት ትምህርት የተባለበት ምክንያት የተማሪዎች ማንነት (Who)፣ ምን መማር እንዳለባቸው (What)፣  እንዴት መማር እንዳለባቸውና (How) የት መማር እእንዳለባቸው (Where) ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ የተማሪዎችን ፍላጎት፣  አቅምና ችሎታን መዝኖ የድጋፍ/እእገዛ አገልግሎት የሚያመቻች የትምህርት መርሀ ግብር (ፕሮግራም) አደረጃጀትስለሆነ ነው ።

የልዩ ፍላጎት ትምህርት ግለሰቦች በራሳቸው በመተማመን ራሳቸውን እንዲሆኑና የአቅማቸውን አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ የሚያበረታታ የመደበኛ ትምህርት ክፍል ነው:: ልዩ ፍላጎት ትምህርት ከተለያዩ ባለሙያዎች ጋር በጋራ ችግሮችን ለመረዳትና ለማገዝ ሁሉን አቀፍ የሆነ አራረብ ያለው /Wholistic approach/ የመደበኛ ትምህርት ክፍል ነው:: ለምሳሌ ከመደበኛ መምህራን (Regular Teachers)፣ ከስነባህሪ ባለሙያዎች (psychologists)፣ከንግግርና የቋንቋ ቴራፒስት (Language/Communication thereapists)፣ ከአካል ቴራፒስት (Physical thereapiests)፣ ከአካልና የአካል ድጋፍ ከሚሠጡ ባለሙያዎች

(Orthopedicits)፣ ከህክምና ባለሙያዎች (Physicians) ፣ ከማህበራዊ ህይወት ባለሙያዎች (Social workers)፣ ከወላጅና ከማኅበረሰቡ(Parents and Community) ጋር በጋራ የሚሠራ የትምህርት ዓይነት ነው::

የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተጠቃሚዎች ቁጥር የተለያዩ ዓለም አቀፍ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት እሁለት መቶ ሚለዮን ይሆናል ተብሎ ይገመታል። ከዚህ ውስጥ ሰማንያ በመቶው (80%) የሚሆነው በታዳጊ አገሮች ውስጥ የሚገኝ ሲሆን አሥር በመቶውን እ(10%) የያዙት ልዩ ፍላጎት ያላቸው ናቸው:: ከእነዚህም መካከል የትምህርትና የጤና አገልግሎት የሚያገኙት ሁለት ከመቶ /2%/ ብቻ ናቸው:: በአገራችን ኢትዮጵያ ደግሞ ከአሥር ከመቶው (10%)ውስጥ የመማር ዕድል የሚያገኙት አንድ በመቶ /1%/ ብቻ ናቸው::

### 1.2 የልዩ ፍላጎት ትምህርት ታሪካዊ እድገት

| |
|---|
| **?** **የልዩ ፍላጎት ትምህርት ታሪካዊ ዕድገት እበአለም አቀፍ ደረጃና በኢትዮጵያ እንዴት ተጀመረ?** |

#### 1.2.1 የልዩ ፍላጎት ትምህርት ታሪካዊ እድገት በአለም አቀፍ ደረጃ

በዓለምአቀፍ ደረጃ የልዩ ፍላጎት ትምህርት አጀማመርን የሚያሰረዳ መረጃ በተደራጀ መልኩ ባይገኝም እንቅስቃሴውን የሚያሳዩ ጽሁፎች እንደሚገልጹት አራት የታሪክ ዘመናት አሉት:: የልዩ ፍላጎት ትምህርት ታሪካዊ አመጣጥና እዕድገት ከኀብረተሰቡ አመለካከት፣ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኀበራዊ፣ ሀይማኖታዊ ዕድገትና ስልጣኔ ጋር ተያያዥነት እንዳለውም ያመለክታሉ።:: በአለምአቀፍ ደረጃ የልዩ ፍላጎት ትምህርት አራቱ የታሪክ ዕድገት ዘመናትን እንመልክት:

ሀ. የመጀመሪያው የታሪክ ዘመን/ ቅድመ ታሪክታ(Early Hisotry) እእ.ኤ.አ ከ1800 በፊት የነበረ፣

ለ. የተቋማት ዘመን (Era of Institution) ከ1800-1900 ያለው ጊዜ፣

ሐ. በመደበኛ ትምህርት ልዩ ክፍሎችየተሰጡበ ዘመን (Era of Public School-Special Clases) 1900-1960/70፣

መ. ፈጣን የዕድገት ዘመን (Ear of Accelerated Growth) 1960/70ዎቹ እእስከ አለንበት ዘመን ተብለው የተከፋፈለ ዘመን ነው።

## ሀ. ቅድመ ታሪክ እእ.ኤ.አ አስከ1800

በጥንቱ ዘመን በባህሪም ይሁን በአካላዊ አቋምና አቅም ከጤናማ ሰዎች ለየት የሚሉትን ኅብረተሰቡ ከሰይጣን (በርኩስ መንፈስ) ከባዕድ አምልኮና ከፈጣሪ ቁጣ ጋር አዛምዶ ሲመለከታቸው በተለይ አባቶች ካልተቀበሏቸው ወደ ባህር ይወረወሩ፣ በጫካ፣ በበረሃ ዳርቻና በየጎዳናው ይጣሉ እንደነበር አንዳንድ ጽሁፎች ይዘግባሉ። ይኸውም ማኅበረሰቡ እእነዚህን ማስወገድ ሰይጣንን እንዳሰወገደ አድርጎ ይቆጥር ስለነበር ነው፡፡የኋላ ኋላ በግለሰቦች (በፈላስፎች)፣ በመንግስትና በሃይማኖት ድርጅቶች ጣልቃ ገብነት ሁኔታዎች እየተቀየሩ ቀስ በቀስ ለውጥ እየታየ መጣ። ታላላቅ ሃሳቦችን በማመንጨት ለልዩ ፍላጎት ትምህርት መዳበር አስተዋፅኦ ካደረጉት ግለሰቦች መካከል የሚከተሉት በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡

| ሃሳብ አመንጪ ግለሰብ/ምሁር | የኖሩበት ጊዜ | ዜግነት | ዋና ያመነጨው ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| ጆን ማርክ ዲሰፐርድ ኢታርድ | 1775-1838 | ፈረንሳዊ | ነጠላ የምርምር ውጤት /ሂደት/ የአዕምሮ ዕድገት ዝግመት ያለባቸው ስልትን ያዳብራል፡፡ |
| ቶማስ ሆፕቶንስ ጋሊደት | 1787-1851 | አሜሪካዊ | መስማት የተሳናቸው ልጆች በፊደላት፣ በሰውነት እንቅስቃሴና በጣት መግባባት ይችላሉ፡፡ |
| ሳሙኤል ግረደለይ ሆዊ | 1801-1876 | አሜሪካዊ | አካል ጉዳተኞች ማካካሻ እንክብካቤ ሳይሆን የተደራጀ ትምህርት ሊማሩ ይገባል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሉዊስ ብሬይል | 1809-1852 | ፈረንሳዊ | ማየት የተሳናቸው ልጆች አማራጭ ስልትን መሰረት በማድረግ መማርና መግባባት ይችላሉ:: |
| ኤድዋርድ ሲጓን | 1812-1880 | ፈረንሳዊ | የአዕምሮ እዕድገት ዝግመት ያለባቸው ልጆች ለየት ያለ ስልት ተዘጋጅቶላቸው ሊማሩ ይችላሉ:: |
| ፍራንሲስ ገላትን | 1822-1911 | እንግሊዛዊ | ሃሳቡ በቤተሰብ ላይ ያጠነጠነ ነበር:: (የቤተሰብ ወሳኝነትን በማመን) |
| አለክሳንደር ግራምቤል | 1847-1922 | አሜሪካዊ | መስማት የተሳናቸውና አነስተኛ የመስማት አቅም ያላቸው ልጆች ድምፅ ማጉያ (ሃስሮቄሽቃሽ ሮሽሳ) ከተገጠመላቸው በመነጋገር ይማራሉ:: |
| አልፍሬድ ቤኑት | 1857-1911 | ጣሊያናዊት | ልጆች በህፃንነት ዕድሜ በተጨባጭ ተሞክሮና ለየት ባለ የማስተማሪያ ስልትና መሣሪያ ብዙ ማውቅ ይችላሉ:: |
| ሉስተር ተርማን | 1877-1956 | አሜሪካዊ | የተለየ ተሰጥኦ ያላቸውን በብስለት ፈተና በመለካት የዕድሜ ልክ ዕውቀታቸውን መለየት/ማወቅ |
| እናፋሩድ ስትረስ | 1897-1957 | ጀርመናዊ | የስሜት መረበሽ ችግር ያለባቸውን ልጆች በስነባህሪያዊ ትንታኔ መለየት ይቻላል:: |
| አልፍረድ ስትረስ | 1897-1957 | ጀርመናዊ | አንዳንድ ልጆች የተለየና ብቃት የለሽ የመማር ስልት የሚያሳዩበት ምክንያት በጭንቅላታቸው ውስጥ ጉዳት ስለሚኖርባቸው ስለሆነ ስልጠና ይፈልጋሉ:: |

ለ. <u>የተቋማት ዘመን እእ.ኤ.አ ከ1800-1900 ያለው ጊዜ</u>

ተቋማትን መገንባትና ማስፋፋት በአውሮፓ ሲጀመር በአካልም ሆነ በተለያዩ ሁኔታዎች ህዝብን ያስቀይማሉ ተብለው የሚገመቱት ከህዝብ ዕይታ ለማራቅ ወደ ተቋማቱ እንዲገቡ ይደረግ ነበር። የኋላ ኋላ ግን ማየት ወይም መስማት ለተሳናቸው በፈረንሳይ፣ በጀርመን፣፣ በስኮትላንድ፣ በእንግሊዝና በአሜሪካም ሀኪሞችና የትምህርት ባለሙያዎች በከፈሉት አስተዋጽኦ የጎብረተሰቡ አመለካከት በመጠኑም የተለወጠበት ዘመን ነበር:: የአእምሮ ዕድገት ዘገምተኞች ተቋም ማሰብ የተጀመረው እ.ኤ.አ ከ1831 በኋላ ሲሆን በዚያን ወቅት አካል ጉዳተኞችን ማሰባሰብና መጥር የሚያስጸድቅ መሆኑን በሀይማኖት ትምህርት የሚሰበክበት ጊዜ ነበር::

የተለየ ሁኔታ ያላቸው ግለሰቦችን በተቋማት የማሰባሰቡ ስራ እእስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ቀጥሎ አሌክሳንደር ግርሃበቤል ባቀረበው አዲስ ሃሳብ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ግለሰቦች በመደበኛ ትም/ቤቶች ልዩ የመማሪያ ክፍሎች እንዲዘጋጅላቸው ስምምነት ላይ ተደረሰ:: ይህ ስምምነት ተግባር ላይ ሊውል የቻለው አለክሳንደር ግርሃበቤል እ.ኤ.አ በ1896 መስማትና ማየት የተሳናቸውና የአእምሮ ዘገምተኞች እንዲማሩ የሚያሳስብ ለብሔራዊ ትምህርት ማኅበር በቀረበው ጽሁፍ ነበር:: ከዚያም በኋላ እ.ኤ.አ በ1896 ዓ/ም የመጀመሪያው የአእምሮ ዕድገት ዘገምተኛ የሆኑ ህፃናት ት/ቤት በአሜሪካን አገር ተጀመረ:: በተጨማሪም በ1902 ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች በመኖሪያ ቤታቸው አካባቢ እንዲማሩ ተመቻችተው የታሪክ ዘመኑ ተለወጠ::

ሐ. <u>የመደበኛ ትምህርት ቤት ልዩ ክፍሎች ዘመን 1900- 1960/70</u>

ልዩ ፍላጎት ትምህርት በመደበኛ ትም/ቤቶች ውስጥ መጀመሩ ከነበረው የተቋማት ክምችት የተሻለ በመሆኑ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራም አዘጋጅቶ የማቅረብ ተቀባይነት ጥረትና ውጤት በጥሩ ሁኔታታ ሲተገበር ከቆዩ በኋላ ትችት ገጠመው::

ሆኖም በጥናትና ምርምር ውጤቶች፣መንግሥታት በሚያወጡት ህጎችና የአካል ጉዳተኞች በማኅበራት ድጋፍ ጋር ተዳምሮ ልጆችን በልዩ ክፍል ማስተማር ማከማቸትና የማግለያ ስልት መሆኑ የተረጋገጠ ልዩ ክፍል የሰዎች ስሜት የሚነካና የበታችነትን የሚቀሰቅስ ስለሆነ የተገለለ ትምህርት ለአካቶ ትምህርት ፅነሰ ሀሳብ የመተካት ሂደት ተጀመረ።

**መ. ፈጣን የዕድገት ዘመን ከ1960/70 እእስከ አለንበት ወቅት**

የልዩ ፍላጎት ትምህርት ደረጃ በደረጃ በፍጥነት በማደግ ግለሰቦች፣ የሃይማኖት ድርጅቶችና መንግስት እንዲሁም ከፍተኛ የፖለቲካ ባለስልጣናትና የአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማኅበራትና የተለያዩ ማኅበራት ባበረከቱት አስተዋፅኦ አሁን የደረሰበት የዕድገት ደረጃ ደርሷል። በመሆኑም ልዩ ፍላጎት ያላቸው አካላት፡-

- ☞ መብታቸው ተጠብቆ ምቹ የመማር ማስተማር ሂደት፣ በኅብረተሰብ ውስጥ የመሳተፍ መብት፣ እእኩል ዕድል የማግኘት መብት እንደጉዳታቸው ዓይነትና ደረጃ በአቅም፣ በፍላጎትና ችሎታቸው በትምህርት መርጃ መሳሪያ የተደገፈ ትምህርት ማግኘት ችለዋል። ሆኖም ይህ ተግባርና ዕድገት እንደየሀገሩ የኅብረተሰብ አመለካከት፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊና ሀይማኖታዊ የዕድገት ስልጣኔ ደረጃ የተለያየ መሆኑን መገንዘብ ይገባል።
- ☞ የተዛባ አመለካከት ስያሜ ቀርቶላቸው ወላጆች በልጃቻቸው ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ተሳታፊ ሆነዋል።

### 1.2.2 የልዩ ፍላጎት ትምህርት ታሪካዊ እድገት በኢትዮጵያ ደረጃ

በኢትዮጵያ ትምህርት ከረዥም ጊዜ በፊት በባህላዊ መንገድ በገዳማት፣ የቅኔ፣ የዜማ የድቁና፣ የፆመ ድጓ እንዲሁም በመስጊዶች የቁርአን ትምህርት ሲሰጥ ማየት የተሳናቸው ግለሰቦች ጥሩ አስተዋፅኦ እንደነበራቸው ይነገራል። በአገራችን ዘመናዊ ትምህርት በ1908 ዓ.ም ሲጀመር በ1917 ዓ.ም ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው በተለይ ማየት ለተሳናቸው ዜጎች በሃይማኖት ድርጅቶች፣ በመንግስታዊ ድርጅቶችና በግለሰቦችተጀመረ። ሆኖም ውጤቱ የመደበኛ ትምህርትን ያክል የጎላ አልነበረም። ትምህርቱም የሚሰጠው በጥቂት ልዩ ትምህርት ቤቶች በልዩ ክፍሎችና/ዩኒት/ በልዩ ክፍል መጠነኛ ተማሪዎች፣ መጠነኛ አገልግሎት በሚያገኙበት ሁኔታ ነበር። ይህም አገልግሎት ፦-

- በ1917 ዓ/ም ለመጀመሪያ ጊዜ በምዕራብ ወለጋ በደምቢዶሎ ለዓይነ ስውራን ህፃናት ት/ቤት በፕሮቴስታንት ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን አማካይነት ተጀመረ፤ በኋላም ከ1928 እስከ 1933 ዓ/ም በነበረው የጣሊያን ወረራ ምክንያት አገልግሎቱ ተቋረጠ።

- እንደገና ደግሞ በ1936 ዓ/ም በአዲስ አበባ ካዛንቺስ አካባቢ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጎ አድራጎት ድርጅት አማካይነት የዓይነ ስውራን ት/ቤት ተጀመረና ውስን የሆኑ ዓይነ ሰውራን ልጆች ሲማሩ ቆይተው ይህ ት/ቤት በ1950 ዓ/ም ወደ ሰበታ ተዛውሮ መርሀ ዕውራን አዳሪ ት/ቤት ሆኖ እቀጠለ::

- ይህ እንዳለ ሆኖ በ1951 ዓ/ም በአዲስ አበባ ቀጨኔ/ሽር ሜዳ እንጦጦ አካባቢ የዓይነ ስውራን ት/ቤት በመካነ እየሱስ ቤተ ክርስቲያን አማከይነት ተጀምሮ የነበረ ቢሆንም በኋላ ወደ ባኮ ተዛውሮ እእስከ ዛሬ ድረስ የባኮ ዓይነ ስውራን ት/ቤት ሆኖ እእያገለገለ ይገኛል:: በተመሳሳይ ወቅት በሌሎች የሀገሪቷ አካባቢያዎች ለምሳሌ በወላይታ ሶዶ ኦቶና ዓይነ ስውራን ት/ቤት በኤስ አይ ኤም (ሚስዮኖች) አማከይነት የተጀመረው ሲሆን እእስከአሁን ድረስም አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል:: እንደዚሁም በሌሎች  አካባቢዎች በተለያዩ ሀይማኖቶች አማካይነት የዓይነ ስውራን ት/ቤቶች ተከፍተውእ እስከዛሬ ድረስ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ::

- ቀደም ሲል የትምህርት ዕድል አገኝተው ለመማር የበቁት ዓይነ ስውራን ሕፃናት ብቻ ነበሩ:: በኋላ ግን በ1956 ዓ/ም በአዲሰ አበባ መካኒሳ አካባቢ መስማት የተሳናቸው ት/ቤት በመሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አማካይነት ተጀመረ::

- በመቀጠልም በ1959 ዓ/ም በአዲሰ አበባ ቦሌ አካባቢ አልፋ መስማት ተሳናቸው ት/ቤት በአሜሪካን ሚስዮኖች የተጀመረ ሲሆን  ት/ቤቱ እእስከአሁንም አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል::

- የኋላ ኋላ ከዓይነ ስውራንና መስማት ከተሳናቸው ሌላ በ1980 ዓ/ም በአዲስ አበባ ካዛንቺስና መካኒሳ አካባቢ በመካነ እየሱስ ቤተክርስቲያን አማካይነት የአእምሮ ዕድገት ዘገምተኛ ለሆኑ ህፃናት  ልዩ ት/ቤት ተከፍቶ አገልግሎት መስጠት ጀመረ።

- የ1986 ዓ/ምቱን አዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ሥራ ላይ መዋል ተከትሎ በተለያዩ ጊዚያት በተለያዩ ቦታዎች ልዩ ት/ቤቶችና ክፍሎች ተከፍተው የልዩ ፍላጎት ላላቸው ህፃናትና ወጣቶች ትምህርት እየተሰጠ ይገኛል፡፡

የልዩ ፍላጎት ትምህርት በተለያየ ወቅትና ቦታ የተለያየ ገጽታ እንደነበረው ከታሪካዊ እድገቱ ተገንዝበናል፡፡ ይህ ታሪካዊ እድገቱ ጠቅለል ባለ መልኩ በሁለት ሊከፈል የሚችል ሲሆን እነሱም፡-

1. **የተገለለ ትምህርት** /Segregated/Discriminate Education
2. **የተቀናጀ/አካቶ ትምህርት** /Integrated Education / inclusive/ ተብለው ይጠራሉ፡፡

### 1.3 ልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት አሰጣጥና አደረጃጀት

የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት አሠጣጥና አደረጃጀት ከታች ጀምረን ወደ ላይ ስንመለከት አመጣጡ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

- ደረጃ 7 አዳሪ ልዩ ተቋም
- ደረጃ 6 ቀን ልዩ ትምህርት ቤት
- ደረጃ 5 ልዩ ክፍል /ዩኒት/ በመደበኛ ትምህርት ቤት
- ደረጃ 4 መደበኛ መማሪያ ክፍል ማበልፀጊያ (ሪሶርስ ማዕከል)
- ደረጃ 3 መደበኛ መማሪያ ክፍል/ተጨማሪ መመሪያና እርዳታ ለመምህሩ
- ደረጃ 2 መደበኛ መማሪያ ክፍል/ለመምህሩ የምክር አገልግሎት
- ደረጃ 1 መደበኛ መማሪያ ክፍል ናቸው።

ለመደበኛ መምህር ምክርና መመሪያ የሚሰጠው ባለሙያ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ባለሙያ/ ተዘዋዋሪ መምህር ይባላል፡፡ የችግሩ መጠን ከፍተኛ ሲሆን የተማሪው ቁጥር ይቀንሳል፡፡ ከላይ የተዘረዘሩት ትምህርት መስጫ ደረጃዎች የሚያሳዩት አንድ ተማሪ በመደበኛ መማሪያ ክፍል በሚያሳየው ልዩ ሁኔታ የሚማርበትና የሚረዳበትን አቅጣጫ የሚያመለክት ነው፡፡ ስለሆነም የልዩ ፍላጎት ትምህርት ጥቅም፡-

- የተማሪን አቀፍ ፍላጎትና ችሎታን ለመለየት ይረዳል::
- ግለሰቦች ራሳቸውን ከማኅበረሰቡ ጋርእንዲያስማሙ፣በራሳቸው የሚተማመኑና ተወዳዳሪ በመሆን ጠቃሚና ተወዳዳሪ ዜጎች እንዲሆኑ ያግዛል::
- በመደበኛ ክፍል ውስጥ ያለውን የመማር ማስተማር ሂደት ችግር ይፈታል።
- የማህበረሰቡን አመለካከት ይለውጣል::
- አገሪቱ የሁሉም ዜጎች ተጠቃሚ እንድትሆን ያደርጋል::
- /አካል ጉዳተኞችን ለማሳተፍ እንደነብሬል፣የምልክት ቋንቋ ወዘተ ከማወቅ ጋር ተያይዞ ተጨማሪ ክህሎት ያስጨብጣል።

### 1.4 ልዩ የመማር ማስተማረው ስልት የሚያስፈልጋቸው የጉዳት አይነቶች

ልዩ ፍላጎት ያላቸው ልጆች የችግራቸውን አይነትና ጥልቀት ለመለየት ጥንቃቄ የሚጠይቅ ተግባር መከናወን ይገባዋል። ለዚሁም የሚከተለውን ሠንጠረዥ መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል።

| ተ.ቁ | የጉዳቱ ዓይነት | የጉዳቱ ንዑስ ክፍሎች |
|---|---|---|
| 1 | የማየት ጉዳት | • ሙሉ የዓይንታ ጉዳት (ዓይነ ስውር)<br>• አነስተኛ የማየት ችሎታታ |
| 2 | የመስማት ጉዳት | • መስማት የማይችሉ<br>• ድምፅን ከፍ በማድረግ የሚሰሙ |
| 3 | የአእምሮ ዕድገትእውስንነት | • መለስተኛ<br>• መካከለኛ<br>• ከፍተኛ<br>• በጣም ከፍተኛ |

| | | |
|---|---|---|
| 4 | የአካል ጉዳትና ከባድ የጤንነት ችግር | • አካላዊ ጉዳት<br>• የእንቅስቃሴ ችግር<br>• የሚጥል በሽታታ<br>• አለርጅክ<br>• የአስም በሽታታ<br>• የስኳር በሽታታ<br>• የልብ በሽታታ<br>• የመተንፈሻ አካል ችግር<br>• የኤች አይቪ/ኤድስ በሽታታ |
| 5 | የቋንቋና የመግባባት ችግር | • የቋንቋ ችግር<br>• የንግግር ችግር |
| 6 | ተደራራቢ ችግር | ከአንድ አካል ጉዳት በላይ ሲከሰት |

**መልመጃ: አንድ**

**ክፍል አንድ:** ከተራ ቁጥር 1-5 ያሉ ጥያቄዎችን እውነት ወይም ውሸት በማለት መልሱ::

1. የልዩ ፍላጎት ትምህርት በትምህርት አቀባበል ሂደት ፈጥኖ ለሚገነዘቡና ከዕድሜ ጓደኞቻቸው ጋር ጋር እእኩል ለመራመድ ለሚቸገሩ ሰዎች ብቻ የተዘጋጀ የመደበኛ ትምህርት አካል ነው::

2. የልዩ ፍላጎት ትምህርቱ ታሪካዊ አመጣጥና ዕድገት ከህብረተሰቡ አመለካከት□ ኢኮኖሚያዊ□ ፖሊቲካዊ□ ማህበራዊና ሀይማኖታዊ ዕድገትና ሥልጣኔ ጋር ተያያዥነት የለውም::

3. በአለማችን ባለው የልዩ ፍላጎት ታሪካዊ የዕድገት ዘመን ከ1800-1900 ባለው ጊዜ ተቋማትን መገንባትና ማስፋፋት በአውሮጳ ሲጀመር ዓላማው አካል ጉዳተኛ የሆኑ ሰዎች በአካልም ሆነ በተለያዩ ሁኔታዎች ህዝብን ያሰቀይማሉ ተብሎው ስለሚገመቱ ከህዝብ ዕይታታ ለማራቅ ነበር::

4. በአለምአቀፍ ደረጃ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ታሪካዊ ዕድገትን ስንመለከት የመጀመሪያው ዘመን የተቋማት ዘመን ይባላል::

5. ድህነት፣ የቤተሰብ መፍረስ፣ የወላጆች ወይም የአሳዳጊዎች ቸልተኛነት፣ የባህሪ ተጽዕኖና የመሳሰሉት በሕፃናት ላይ የተለያዩ የአካል ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ::

**ክፍል ሁለት:-** ከተራ ቁጥር 6-10 ላሉት ት ጥያቄዎች በ "ሀ" ምድብ የተገለፁትን በ "ለ" ምድብ ከተገለፁት ጋር በማዛመድ መልሱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 6. የመደበኛ ትምህርት ልዩ ክፍሎች ዘመን | ሀ. ልዩ ክፍል /ዩኒት/ በመደበኛ ት/ቤት |
| 7. ከ1960/70ዎቹ እስከ አለንበት ዘመን | ለ. መደበኛ መማሪያ ክፍል |
| 8. የመጀመሪያ ዘመን ታሪክ (ቅድመ ታታሪክ) | ሐ. ፈጣን የዕድገት ዘመን |
| 9. ልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት አሠጣጥና አደረጃጀት ደረጃ 5 | መ. የተቋማት ዘመን |
| 10. ልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት አሠጣጥና አደረጃጀት ደረጃ 1 | ሠ. ከ1800 በፊት የነበረው ዘመን |
| | ረ. ከ1900-1960/70 የነበረው ዘመን |

**ክፍል ሦስት:-** ከተራ ቁጥር 11-13 ላሉት ጥያቄዎች ለእያንዳንዳቸው ከሀ-መ ከተሰጡት አማራጮች ተስማሚ የሆነውን መልስ የያዘ ፊደል በመምረጥ መልሱ::

11. ስለ ልዩ ፍላጎት ትምህርት ጥቅም ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. በመደበኛ ክፍል ውስጥ ያለውን የመማር ማስተማር ሂደት ችግር ይፈታል።

ለ. ግለሰቦች ራሳቸውን ከማኅበረሰቡ ጋር እንዲያስማሙ አያግዝም::

ሐ. በብሬል ለመጻፍ ናየምልክት ቋንቋ ለማወቅ ብቻ ጥቅም አለው::

መ. ሀ ናሐ መልስ ናቸው።

12. ጉዳት /እንከን ያላቸው ህጻናትን የማይመለከተው የትኛው ነው?

**ሀ. የአካል እንቅስቃሴና የጤንነት ጉዳት ያለባቸው፣**

ለ. የመግባባት፣የቋንቋና የባህሪ ችግሮች ያሉባቸው
ሐ የመማር ችግር እና ተደራራቢ የአካል ጉዳቶች ያሉባቸው

መ. ልዩ ተሰጥኦና ችሎታ ያላቸው

13. ስለልዩ ፍላጎት ትምህርት ጥቅም ትክክል ያልሆነውን ምረጡ፡፡

ሀ. የተማሪን አቀፍ ፍላጎትና ችሎታን ለመለየት ይረዳል

ለ. የማኅበረሰብ አመለካከትን ይለውጣል

ሐ. በመደበኛ ክፍል ውስጥ ያለውን የመማር ማስተማር ሂደት ችግር አይፈታም

መ. ለናሐሀ መልስ ናቸው።

# ምዕራፍ ሁለት

# ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕፃናት

## 2.1 ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕፃናትን ማስተማር

**መግቢያ**

ውድ የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህጻናትና ወጣቶች እእነማን እነደሆኑ፣ የተለያዩ ጉዳት ስለአላቸው ህጻናቶችና ወጣቶች ምንነት፣ ልዩ ተሰጥኦና ችሎታ ያላቸው ትርጉምና ምንነት፣እንዲሁም እእነዚህን ህፃናት ማስተማር የሚሉ ጽንሰ ሀሳቦችን ትረዳላችሁ:: በተጨማሪም ስለ ምዕራፉ ዓላማዎችና አተገባበራቸው በሚገባ ትገነዘባላችሁ::

**የምዕራፉ አላማዎችና ግቦች፡-**

ሠልጣኞች/የዚህ ሞጁል ተጠቃሚዎች ይህንን ምዕራፍ ሲጨርሱ፡-

- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህጻናትና ወጣቶች እእነማን እንደሆኑ ለይተው ያውቃሉ፣
- የተለያዩ ጉዳት/እ ስለአላቸው ህጻናቶችና ወጣቶች ምንነት ይረዳሉ፣
- ልዩ ተሰጥኦና ችሎታ ያላቸው ሕፃናት ትርጉምና ምንነት ይገነዘባሉ፣
- ልዩ ተሰጥኦና ችሎታ ያላቸው ህጻናትን ማስተማር የሚያስችሉ ዜደዎችንና ስልቶችን ይረዳሉ፣
- ስለልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት አሠጣጥና አደረጃጀት ያውቃሉ::

በዚህ ምዕራፍ ስር የሚከተሉት ይዘቶች ተካተው ቀርበዋል።

**ሀ/ የተለያዩ ጉዳት ያላቸው ህጻናት ምንነት**

☞ ማየት የተሣናቸው ሕፃናት፣

☞ መስማት የተሣናቸው ሕፃናት፣

- ☞ የአእምሮ  ውስንነት ችግር ያለባቸው ሕፃናት፣
- ☞ የአካል/ የአንቅስቃሴና የጤንነት ጉዳት ያለባቸው ሕፃናት፣
- ☞ የመግባባትና የቋንቋ ችግር ያለባቸው ሕፃናት፣
- ☞ የባህርይና የስሜት ችግሮች ያሉባቸው ህጻናት፣
- ☞ የመማር ችግር ያለባቸው ሕፃናት፣
- ☞ የአካባቢያዊና ባህላዊ ተፅዕኖ ያለባቸው ሕፃናት፣
- ☞ ተደራራቢ የአካል ጉዳቶች ያሉባቸው ሕፃናት

**ለ/ተሰጥኦና ችሎታ ያላቸው ህጻናት የሚሉት ናቸው።**

### 2.2 የተለያዩ ጉዳቶች ያሉባቸው ህፃናትን ማስተማር

በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ስር ዘጠኝ የተለያዩ ዓይነት ጉዳቶች ያሉአቸው  ህጻናቶች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ማብራሪያ ቀርቧል። በተጨማሪም ስለ እያንዳንዳቸው ትርጉምና ምንነት፣ክፍፍል፣ መንስዔዎቻቸው ማህበራዊ፣ ሥነ ልቦናዊና የትምህርትእገዛዎች/ ድጋፎች ተብራርተው ቀርበዋል።በአጠቃላይ ሲታይ የተለያዩ ጉዳት አለባቸው የሚባሉት ህጻናት የሚከተሉት ናቸው። ያላቸው ሕፃናት የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው ::

ሀ/ ማየት የተሣናቸው ሕፃናት

ለ/ መስማት የተሳናቸው ህጻናት
ሐ/ የአእምሮ  ውስንነት ችግር ያለባቸው ሕፃናት

መ/የአካል አንቅስቃሴ ና የጤንነት  ጉዳት ያለባቸው ህጻናትƒ

**ሠ/ የመግባባትና የቋንቋ ችግሮች ያሉባቸው  ህጻናት**
ረ/  የባህሪና የስሜት ችግሮች ያለባቸው ሕፃናት

ሰ/  የመማር ችግር ያለባቸው ሕፃናት

ሸ/ የአካባቢያዊና ባህላዊ ተፅዕኖ ያለባቸው ሕፃናት

ሸ/ ተደራራቢ የአካል ጉዳቶች ያለባቸው ሕፃናት

### 2.2.1 ማየት የተሳናቸው ሕፃናት

**ሀ/ ማየት የተሳናቸው ሕፃናት ትርጉምና ምንነት**

ማየት መሳን ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ የሚሰጡ ሁለት ዓይነት አመለካከቶች አሉ:: አንዱ ሕጋዊ (Legal) ትርጉም ሲባል ሁለተኛው ትምህርታዊ (Educational) ትርጉም ተብሎ ይጠራል:: የመጀመሪያው ሕጋዊው መሠረት ያደረገው የዓይን ጥራት ስፋት አንግል መሠረት በሚያደርጉ መለኪያዎች ላይ የተመረኮዘ ነውጹ እነርሱም በእንግሊዝኛው (Visual acuity and field vision) በመባል ይታወቃሉ። በዚህ መለኪያ መሠረት 20/20 ውጤት ያለው ሰው በጤነኛ ሰው ዓይን ከሃያ ጫማ ያየውን ይህም ሰው አይቷል ማለት ስለሆነ ቁጥሩ ሙሉ ጤንነትን ያሳያል:: በሌላ ሰው 20/200 ውጤት ቢያገኝ ትርጉሙ ጤነኛ ዓይን ያለው ከ200 ጫማ ርቀት ያየውን ይህ ውጤት የተሰጠው ሰው ሃያ ጫማ ርቀት ላይ ካልቀረበ አያይም ማለት ነው:: ይህም ሕጋዊ ዓይነ ሰውር ነው ያሰኛል::

በሁለተኛው መለኪያ መሠረት ደግሞ ማንኛውም ጤነኛ ዓይን ያለው ሰው 180° ከተመለከተ ጤነኛ ተብሎ ሲጠራ ሌላው በተመሳሳይ መለኪያ 10° ብቻ የሚመለከት ከሆነ ማየት የተሳነው የሚል ትርጉም ያገኛል::

በሌላ በኩል ግን ማየት የተሳነው ማለት ምን ማለት ነው? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥ ሁለተኛ አመለካከት አለ:: እርሱም ትምህርታዊ ትርጉም የሚባለው ነው:: በዚህ ትርጉም መሠረት ከላይ በህጋዊ ትርጉም ውስጥ የተጠቀሱትን ወደ ጎን በመተው እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ህጻናት ጉዳቱ እንዳለበቸውም ቢሆን ሊማሩ ይችላሉ ወይም አስፈላጊውን እርዳታና ማካካሻ መሳሪያዎችን ብናሟላላቸው እንደማንኛውም ሰው ሊማሩ ይችላሉ የሚለውን ሃሳብ ቅድሚያ በመስጠት የተሳናቸው የሚለውን ቃል ውድቅ የሚያደርግ ነው::

ትርጓሜውን ከሁለት አቅጣጫ ካየን ማየት የተሳነው የሚለውን ሁለት ዓይነት የዕይታ ታ ችግር ያለባቸውን በጋራ የሚያጠቃልል ነው:: የመጀመሪያው የማያዩ (Total Blindness) ሲሆን ሁለተኛው በጣም ዝቅተኛ እእይታ ያላቸውን ( Low vision ) ነው። እነዚህ ህጻናትእ በቀሪው የአይናቸው ብርሀንና ሌሎችንም ማካካሻዎች በመጠቀም ብዙ እንዲገለገሉበት ማድረግ ይችላሉ ማለት ነው።:

የአይንን ሁኔታ በተመለከተ የዓለም ጤና ድርጅት (World Health Organization /WHO) እ.ኤ.አ በ1993 . በሚከተሉት ደረጃዎች ተርጉሚል፡፡

| የዕይታ ምድብ | የማየት ችግር ደረጃ | የተሻለ የማየት ችሎታ | አማራጭ ትርጉም |
|---|---|---|---|
| ኖርማል እዕይታይታ (Normal Vision) | ምንም ችግር የለም | ≥ 0.8 (6/7.5) | ጤናማ |
| መጠነኛ ወይም በከፊል ማየት (Low Vision) | ሀ. በትንሹ (Slight) | < 0.8 | ወደ ጤናማ የተጠጋ |
| | ለ. መካከለኛ (Moderate) | < 0.3 (6/18) | በከፊል/ መካከለኛ የማየት ችሎታ ያለው |
| | ሐ. በከፍተኛ (Severe) | ≥ 0.12 (6/48) | የከፋ ደረጃ ያለ ከ6 ሜትር ላይ ጣቶችን መቁጠር የማይችል |
| ሙሉ በሙሉ የማያዩ (Blindness) | ሀ. በጥልቀት (Profound) | < 0.05 (3/60) | ከ3 ሜትር ባነሰ ርቀት ላይ ሆኖ ጣቶችን መቁጠር የሚችል |
| | ለ. ሙሉ ለሙሉ የተጠጋ (Near - Total) | < 0.02 (1/60) | በአንድ ሜትር ርቀት ላይ ጣቶችን መቁጠር የሚችል ወይም በ5 ሜትር ላይ ሆኖ የሚንቀሳቀሱ ነገሮችን መለየትን የሚችል፡፡ |
| | ሐ. ሙሉ በሙሉ የማያዩ | ምንም ብርሃን የማያዩ | ምንም ዓይእ በቦታው የሌሉት |

**ለ. ለማየት መሳን መንስዔዎች**

የአይንታ ችግር መንስዔ የሚሆኑ ብዙ የተለያዩ ችግሮች አሉ፡፡ ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- <u>ከርቀትና ከቅርብ የማየት ችግር</u> (Refractive Error)፡- ይህ አብዛኛውን ጊዜ ለሁሉም ሰዎች ሊከሰት የሚችል ዕይታ ችግር ነው፡፡ ይህ ችግር የሚፈጠረውም ወደ

ዓይናችን ውስጥ የሚገባው ብርሃን ወደ ሬትና (Retina) ሳይደርስ ሲቀር ነው:: ይህም የቅርብ ዕይታ ችግር (Myopia or near sightedness) ማለትም በሩቅ የሚገኙ ነገሮችን ለማየት ያለመቻል ሲሆን ሌላው የሩቅ ዕይታእችግር (hyperopia or farsightedness) ይባላል። ይህ የዕይታ ችግር በቅርብ የሚገኙ ነገሮችን ለማየት ያለመቻል ነው።

- **<u>የሞራ ግርዶሽ</u>:-** በዓይን ሌንስ ምስርት ላይ ደመና ወይም አቧራ ሆኖ ነገሮችን እንዳናይ የሚያደርግ ወይም የሚሸፍን የሞራ ግርዶሽ ነው:: ይህ ጉዳት አሰፈላጊው ሕክምና ካልተደረገለት የመታወር ችግር የሚያስያከትል በሽታ ነው።
- **<u>ከዓይን ጋር የተያያዘ ኢንፌክሽን</u> (Infections to Eyes):-** ይህ ጉዳት በአብዛኛው እንደ ትራኮማ በዓይን ንጽሕና ጉድለትና እንደ ቂጥኝ፣ ጨብጥ ወዘተ... በመሳሰሉት የአባላዘር በሽታዎች ምክንያት የሚመጡ የዓይን ኢንፌክሽኖችን ያጠቃልላል:: እነዚህም በሺታዎች በዓይን ላይ ጉዳት የሚያመጡና መታወርን የሚያስከትሉ ናቸው::
- **<u>መርዛማነት ያላቸው ማቴሪያሎች</u>:-**በአካባቢ በሚከሰት የአየር ብክለት፣ በኬሚካሎች፣መርዛማነት ባላቸው ዕፅዋት፣ ወዘተ. የሚፈጠሩ ናቸው።
- **በዓይን ውስጥ ግፊት በመጨመሩ** (Glaucoma):- በደም ብዛት ምክንያት በሚከተሰው ግፊት ምክንያት የመታወር ችግር ይከሰታል።
- **<u>በሌሎች በሽታዎች ምክንያት</u>**:- እንደ መንጋጋ ቆልፍ፣ ሀይለኛ ትኩሳት ወዘተ... በመሳሰሉት የሚከሰት ነው::
- **<u>በተለየዩ አደጋዎች</u>:-** ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ በሆኑ አደጋዎች ምክንያት ዓይነስውርነት ይከሰታል። ለምሳሌ በመኪና አደጋዎች፣ በእሳት ቃጠሎ፣ በሀይለኛ ምቶችና በሌሎች ሁኔታዎች አደጋዎች ሊደርሱ ይችላሉ።:

በአጠቃላይ ለአይን በሽታ መከሰት ምክንያት የሚሆኑ ችግሮችን በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ልንመድባቸው እንችላለን። እነርሱም፡-

- በዘር የሚተላለፉ፣
- በቫይረስ አማካይነት የሚመጡ፣
- በእሳትና በተመሳሳይ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ አደጋዎች የሚመጡ
- በተፈጥሮ ጉድለት የሚመጡ ብለን ልንከፋፍላቸው እንችላለን።

**ሐ/ የማየት ጉድለት ያለባቸው ሕፃናት አጠቃላይ ባሕሪያት**

የማየት ችግር ያለባቸው ሕፃናትንና ወጣቶችን መለየት ከሚያስችሉ ባሕሪያት የሚከተሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው::

- ነገሮችን ወደ ዓይን ማቅረብ፣
- ቀርፋፋ አረማመድ፣
- የሰውነትን ሚዛን የመጠበቅ ችግር፣
- ስለራስ አሉታዊ አመላከትን ማንጸባረቅ፣
- ከቅርብ ዕይታ በኋላ ድካም  ራስ ምታት መኖር፣
- የብርሃን መቋቋም ችግር . . . ወዘተ ናቸው።

**መ/ የማየት ችግር ያለባቸው ሕፃናትን ስለማሰስ (Assessment)**

የማየት ችግር ያለባቸው ሕፃናትን ለመለየት የሚከተሉት የአሰሳ ዘዴዎችን መጠቀም ይቻላል::

- ሙሉ በሙሉ ብርሃንን ማየት የማይችሉትን ለይቶ ማወቅ፣
- ብርሃንን ያለአጉሊ መሣሪያ ማየት መቻልን መለየት፣
- በአጉሊ መሣሪያ ተቸግረውም ቢሆን ብርሃንን ማየት መቻላቸውን ማረጋገጥ፣
- ቅርጽ ያለውን ነገር ማየትና ማረጋገጥ፣
- የማየት ችሎታቸውን መለየት . . . ወዘተ ናቸው::

**ሠ/ ማየት ለተሳናቸው ሕፃናት የሚሰጡ የትምህርትና ማኀበራዊ እእገዛዎች፣**

ማየት የተሳናቸወ ሕፃናት ለመዘዋወር እንዲችሉ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ይኖርባቸዋል። እነዚህን ዘዴዎች ለመጠቀም ደግሞ መማር አለባቸው።:: በመሆኑም ማየት ለተሳናቸው ህጻናት ቀጥሎ ያሉትን የትምህርትና ማኀበራዊእ ዕገዛዎችን ማድረግ ያስፈልጋል።

**በሰው መመራት** / The Sighted guide technique /: - የዕይታ ችግር ያለበት ሰው የአይናማ ሰው ክንድ ይዞ በመመራት የመሄድ ዘዴ ነው:: መሪው ሰው የዓይነ ሥውሩን እርምጃ በማጥናትና አረማመዱን ሳይለውጥ አንድ ዓይነት ዘዴ ሊያስጠናው ይገባል::

**ረጅም ነጭ በትር መጠቀም** /The long white came/:- ይህም በስፋት ብዙ ዓይነ ሥውራን ከቦታ ቦታ ለመዘዋወር የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው:: ይህን ዘዴ ለመጠቀም ተማሪዎቹ የሞቢለቲና ኦሬንቴሽን ዘዴዎችን መማር አለባቸው:: ዋወር መልካምና የኦሬንቴሽን ትምህርት ያለው ሰው ነጭ በትርን በመጠቀም ከአደጋ ራስን በመጠበቅ የፈለገበት ቦታ መሄድና መዘዋወር ያስችለዋል።

**በሰለጠነ ውሻ መጠቀም** /Guide Dog/:- በሰለጠኑ መሪ ውሾች መጠቀም የሚችሉት ዕድሜአቸው ከ16 ዓመት በላይ የሆኑት ናቸው:: ይህን ለማድረግ የአካል ጥንካሬም አስፈላጊ ነው:: በውሻ መመራት ውጤታማ የሚሆነው ውሻው ከባለቤቱ በስተቀር ሌላ ሰው እንዳይለምድ ሲደረግ ብቻ ነው::

**በነፃ ራስን ችሎ መሄድ** /Independent Travel/:- ራስን ችሎ ያለመሪ ለመሄድ አይነ ሥውሩ ሰው ስለአካባቢው አስተማማኝ ኦሬንቴሽን ሊኖረው ይገባል። በተጨማሪም በመንገድ ላይ በግድየለሽነት የሚጣሉ እንቅፋቶች መወገድ አለባቸው:: እእቃዎችን በተለመደ አንድ ቦታ ላይ ማስቀመጥና ይህ አሰራር ደግሞ በህፃንነት ጊዜ የተጀመረ ከሆነ የተመቻቸ ሁኔታን ይፈጥራል ተብሎ ይታመናል።

**ረ. ማየት የተሳናቸውን ህጻናት ለማስተማር የሚያገለግሉ አንዳንድ ማቴሪያሎች**

- ኦኘታኮን ማሽን ጽሑፍን ወደሚዳሰስ ጽሑፍ የሚለውጥ መሣሪያ፣
- ስቴሪዮቶነር ጽሑፍን ወደሚሰማ (Auditory Tone) የሚለውጥ መሳሪያ፣
- ኩርዝዊል በወረቀት ላይ ያለ ጽሑፍን ወደ ንግግር ቃላት የሚለውጥ ጽሑፍን መተየቢያ ነው፡፡

**ሰ. ማየት ለተሳናቸው የሕይወት ክህሎትና ሙያዊ እድገት ገዛ አሰጣጥ** በተጨማሪ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፡-

- በከፊል ለሚያዩ ኃከፍተኛ  አጉሊ መነጽር
- ስሌትና ታስታይለስ
- ኮንታክት ሌንስ
- በከፊል ለሚያዩ መነጽሮች

ማየት የተሣናቸው ተማሪዎችን ለመርዳት መምህራን መከተል ያለባቸው መመሪያዎች፡-

- ☞ በተናጋሪውና በተማሪው መካከል ያለውን ርቀት በተቻለ መጠን ማጥበብ፣
- ☞ ትኩረት የሚስቡ ድምጾችን ማስወገድ፣
- ☞ ለክፍል ውስጥ ዝውውር እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን ማስወገድ፣
- ☞ ቁምሳጥኖችን በሮችንና የመሳሰሉትን ሙሉ ለሙሉ መክፈት ወይም መዝጋት፣
- ☞ ዕቃዎችን አንድ የተለመደ ቦታ ላይ ማስቀመጥ፣
- ☞ ኦቨር ሄድ ፕሮጀክትን በመጠቀም ጽሑፍንና ስዕሎችን በስክሪን ላይ በማሳደግ ዝቅተኛ ዕይታታ ያላቸው ተማሪዎች እንዲጠቀሙበት፣
- ☞ የሚናገር የሂሳብ መኪናን በመጠቀም የሂሳብ ትምህርትን እንዲማሩ ማገዝ፣

## መልመጃ: ሁለት

**ክፍል አንድ: -** ከተራ ቁጥር 1-6 ያሉ ጥያቄዎችን እውነት ወይም ውሸት በማለት መልሱ፡፡

1. የመማርና የማዬት ችሎታ በባለሙያ ሲታይ ከ0.8 በታች ነው፡፡ ስለዚህ ለመማርታ የሚሰጠው አማራጭ ጤናማ የሚለው የዕይታ ትርጉም ነው፡፡

2. በዓይን ሌንስ ምስርት ላይ ደመና ወይም አቧራ ሆኖ ነገሮችን እንዳናይ የሚያደርግ/ የሚሸፍንና አስፈላጊው ሕክምና ካልተደረገ የመታወር ችግር የሚያስከትል በሽታ የሞራ ግርዶሽ ይባላል::

3. በኢትዮጵያ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ለመጀመሪያ ጊዜ የተጀመረው በምዕራብ ወለጋ በደምቢዶሎ መስማት ለተሳናቸው ህፃናት አገልግሎት ለመስጠት የተመሰረተው ት/ቤት ነው።

4. ኦኘታኮን ማሽን ጽሑፍን ወደሚዳሰስ ጽሑፍ የሚለውጥ መሣሪያ ነው ::

5. ሙሉ በሙሉ የማያዩ ሰዎች መካከለኛ የማየት ችሎታ ያላቸው ተብለው ይመደባሉ።ታ

6. ከርቀትና ከቅርብ የማየት ችግር ለሁሉም ሰዎች ሊከሰት የሚችል የዕይታ ችግር ነው።

**ክፍል ሁለት: -** <u>ከተራ ቁጥር 7-14 ላሉት ጥያቄዎችእከሀ-መ ከተሰጡት አማራጮች ተስማሚ የሆነውን መልስ የያዘ ፊደል በመምረጥ መልሱ::</u>

7. የማየት ችግር ያለባቸው ሕፃናትንና ወጣቶችን መለየት ከሚያስችሉ ባሕሪያት የሚከተሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው::

   ሀ. ነገሮችን ወደ ዓይን ማቅረብ፣

   ለ. ቀርፋፋ አረማመድ፣

   ሐ. የሰውነትን ሚዛን የመጠበቅ ችግር፣

   መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

8. ማንኛውም ዓይነት የአካል ጉዳትእ እንዳይከሰት በእርግዝና ወቅት የሚያስፈልገው ጥንቃቄ የቱ ነው?

   ሀ. የእናት ጡት ወተት በብቃት እንዲያገኙ ማድረግ

   ለ. በቂና የተመጣጠነ ምግብ አለመመገብ

   ሐ. ዕድሜ በጣም ከገፋ በኋላ ልጅ መውለድ

   መ. ሁሉም መልስ ናቸው::

9. የዕይታ ችግር መንስዔ የሚሆነው የትኛው ነው

ሀ. ከርቀትና ከቅርብ የማየት ችግር ብቻ

ለ. ከዓይን ጋር የተያያዘ ኢንፌክሽን ብቻ

ሐ. መርዛማነት ያላቸው ማቴሪያሎች ብቻ

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

10. የማየት ችግር ያለባቸው ሕፃናትን ለመለየት የሚያስችለው ባሕርይ የትኛው ነው?

ሀ. ነገሮችን ወደ ዓይን ማቅረብ

ለ. የብርሃን መቋቋም ችግር

ሐ. ከቅርብ ዕይታ በኋላ ድካም ወይም ራስ ምታት መኖር

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

11. ረጅም ነጭ በትርን ብሎ ሞቢለት ኦሬንቴሽን ካለ ------------- ብሎ

የአይናማ ሰው ክንድ ይዞ በመመራት መሄድ ይባላል ::

ሀ. በሰለጠነ ውሻ መጠቀም

ለ. የምልክት ቋንቋ

ሐ. በሰው መመራት / The Sighted guide technique /

መ. ለናሐ መልስ ናቸው

12. የአየለች የዕይታ ሁኔታ በመሳሪያ ሲታይ በ6 ሜትር ላይ ሆና ጣቶችን መቁጠር

አትችልም:: ስለዚህ የአየለች የማየት ችግር ደረጃ ----------- ይባላል::

ሀ. ወደ ጤናማ የተጠጋ

ለ. መለስተኛ የዕይታ ችግር

ሐ. መካከለኛ የዕይታ ችግር

መ. በጥልቀት የዕይታ ችግር

13. የማየት ችግር ያለባቸው ሕፃናትን ለማሰስ የማያገለግል የትኛው ነው?

ሀ. ሙሉ በሙሉ ብርሃንን ማየት የማይችሉትን ለይቶ ማወቅ

ለ. ብርሃንን በአጉሊ መሣሪያ ማየት መቻልን ማወቅ

ሐ. ቅርጽ ያለውን ነገር ማየትን ማረጋገጥ

መ. መልስ አልተሠጠም

14. ማየት የተሣናቸው ተማሪዎችን ለመርዳት መምህራን መከተል ካለባቸው መመሪያዎች ውስጥ የማይካተተው የትኛው?

ሀ. ለክፍል ውሰጥ ዝውውር እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን ማስወገድ
ለ. ትኩረት የሚስቡ ድምጾችን ማስወገድ
ሐ. በተናጋሪውና በተማሪው መካከል ያለውን ርቀት በተቻለ መጠን ማስፋት
መ. ቁምሳጥኖችን፣ በሮችንና የመሳሰሉትን ሙሉ ለሙሉ መክፈት ወይም መዝጋትና ዕቃዎችን በአንድ በተለመደ ቦታ ላይ ማስቀመጥ

### 2.2.2 መስማት የተሳናቸው ሕፃናት

**ሀ/ መስማት የተሳናቸው ሕፃናት ትርጉምና ምንነት**

መስማት ከጆሮ ተግባር ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ነው:: ስለዚህም መስማት የተሳነው ካልን በውጫዊ ወይም በውስጣዊ መንስኤዎች ጆሮ ድምጽን ተቀብሎ የማስተላለፍ ችግር አለበት ማለታችን ነው። አንድ ሰው ሰማ የምንለው ከውጭ የተፈጠረው ድምጽ በአየሩ ውስጥ በመርገብገብ በጆሮ ቀዳዳ በኩል አልፎ የጆሮን ታምቡር ሲያርገበግብና እርሱም በተራው ፡ « ሀመር » አንቪልና «ስቲሪፕ» የተባለ በመካከለኛው ጆሮ ውስጥ ያሉ ቀጫጭን አጥንቶችን በማርገብገብ ኦቫል ዊንዶው በተባለው አማካኝነት ወደ ውስጠኛው ጆሮ (ኮኪሊያ) በማለፍ የተለያዩ የድምጽ ፍሪኮንሲ ያላቸውን ፀጉሮችን አልፈው በኦዲተር ነርቭ አማካይነት አእምሮ ላይ ደርሰው ትርጉም ሲያገኙ ነው:: ከእነዚህ ከተዘረዘሩ ቦታዎች በአንዱ ላይ እክል ካጋጠመ እንደቦታው ዓይነትና እንደ እክሉ መጠን መጠን የተለያየ ደረጃ ያላቸው የመስማት ችግሮች ይፈጠራሉ:: ስለዚህም የመስማት ችግር የሚባለው አንድ ድምጽ ከተፈጠረበት ተነስቶ በጆሮ ቀዳዳ አልፎ ትርጉሙ እስከሚያገኝበት ድረስ ባሉት መንገዶች ውስጥ ማለፍ አቅቶት የመግባባት ችግር ሲፈጠር ነው::

**ለ/ መስማት የተሳናቸው ሕፃናት ክፍፍል**

መስማት የተሳነው ማለት በጥቅሉ ሲተረጎም ከ70 ዴሲቤል (above 70 deciable ) በላይ የሆነ ፍፁም የመስማት አለመቻል ጉዳት የደረሰበት ወይም በመደበኛ ሁኔታ መስማት የማይችል ማንኛውም ሰው ነው:: መስማት መሳንን የተለያዩ ባለሙያዎችና ሊቃውንቶች በሁለት ደረጃዎች መድበው ተርጉመውታል።:: ከዚህ አንጻሬ ፓሶኔላና ከራ (Pasoneela and Cara, 1981) በሁለት ክፍሎች በመክፈል የሚከተለውን ተርጕመዋል:: እ

**<u>በደንብ የማይሰማ</u>** (Hard of Hearing)፣ ይህም ጮክ ብሎ በመናገር ወይም በድምፅ አጉሊ መሣሪያ እገዛ (Hearing Aid) በመጠቀም መስማት የሚችሉ ሲሆኑ የመስማት ከፍታው ከ26 እእስከ 70 ዴስቤል (26dB – 70dB) የሆኑትን የሚያጠቃልል ነው:: ይህም የሕፃናትንና የወጣቶችን የመስማት ይህም ክፉኛ ይጎዳል::

**<u>ሙሉ በሙሉ የማይሰሙ</u>** (Deaf)፣ ይህም በድምፅ አጉሊ መሣሪጅበንጠቀም ም ንም ዓይነት ድምፅ መስማት የማይችሉትን ያጠቃልላል:: ይህ የመስማት ችግር የመስማት ከፍታው ከ70 ዴሲቤል በላይ የሆኑትን የሚያጠቃልል ሲሆን ማንኛውም ዓይነት ድምፃዊ መልዕክት የማይሰማቸውና ክፉኛ የተጎዱት ናቸው:: የዚህ ዓይነት ጉዳት ያለባቸው ሕፃናትና ወጣቶች በምልክት ቋንቋና በጽሑፍ ካልሆነ በስተቀር በድምፅ ማንኛውንም ትምህርት ሊማሩ የማይችሉ ናቸው::

**ሐ/ የመስማት መሳን መንስዔዎች (Causes of Hearing Impairment)**

የመስማት መሣን ችግሮቹና መንስዔዎች የተለያዩ እንደሆኑ ሁሉ ፥ የሚያስከትሉትም ችገሮች የተለያዩ ናቸው:: መስማት መሣን ከልደት በፊት (Prenatal stage)፣ በልደት ጊዜና (Perinatal stage) ከልደት በኂላ (Postnatal stage) ሊከሰት ይችላል:: እ እነዚህም የመስማት መሳን ችግሮች መንስዔዎች በአብዛኛው የሚከተለት ናቸው::

የመስማት ችግር መንስዔዎች በዘር የሚተላለፉ ከእናት ወደ ልጅ በሚተላለፍ በሽታ፣ የጀርመን ኩፍኝ (Maternal rubells)፣ ማጅራት ገትር፣ በመንጋጋ ቆልፍ (Meningitis)፣ የጆሮ ውስጥ ቁስል (Otitis media) ከፍተኛ ትኩሳት (Fever)፣ ኢንፌክሽን ቁስል (Trauma)፣ በወሊድ ወቅት የሚያጋጥም ችግር (Birth Complication)፣ እእድገትን ሳይጨርሱ መውለድ፣ የደም ልዩነት (RH Fator)፣ በእርግዝና ወቅት በቂ አዮዲን እጥረትናእ የጆሮ

አካባቢ በጥፊ መመታት ከፍተኛ የድምፅ ፍንዳታታ፣ በእርግዝና ወቅት የሚወሰዱ መድሀኒቶችና  አልኮል መጠጣት ሌሎች ያልታወቁ መንስኤዎች (Unknown causes) ናቸው::  እንደመንስኤአቸውም  ብዛት ችግሮችን እንደገና በሶስት ከፍሎ ማየት ይቻላል። እነርሱም: -

- **<u>በአየር የሚተላለፍ ድምጽ የመቀበል እእጦት</u> (Conductive Hearing Loss)** ብዙውን ጊዜ ከውጭ የምንሰማው ድምጽ በጆሮ በኩል አድርጎ ወደ አእምሮ ደርሶ ትርጉም ሲያገኝ በሚያስችል ሂደት በአየር እርግብግቢት አማካይነት የመጣ ስለሆነ በ እእግሊዝኛ ኮንዳክሽን (Conduction) ይባላል::  ሆኖም ግን ይህ ዓይነቱእርግብግቦሽ በጆሮ ውስጥ አንድ  ቦታ ላይ ከተገታና  ወደ ሚቀጥለው ክፍል መተላለፍ ሲያቅተው (Conductive Hearing Loss ) በመባል ይታወቃል።  የዚህ ዓይነት አለመስማት ችግር ወደ አእምሮ  ደርሶ ትርጉም ማግኘት የሚገባው ድምጽ በውጭኛው፣በመካከለኛው ወይም በውስጠኛው ጆሮ ውስጥ በሚፈጠሩ የመርገብገብ ችግሮች መንስኤነት የሚመጣ ነው::

**<u>ከአእምሮ ጋር የተያያዘው የነርቭ መልዕክት ተቀባይ ችግር</u> (Sensorineural Hearing Loss):-** ይህ የሚገኘው በውስጠኛው የጆሮ ክፍል ሲሆን መልዕክቱን ከእርግብግቦሽ (Vibration)  ኤሌክትሪካል ወደ ሆነ መንገድ በመለዋወጥ ለአእምሮ በነርቭ አማካይነት የሚያስተላልፍ ነው:: ይህ ክፍል ጉዳት ከደረሰበት በህክምና ለማስተካከል በጣም አስቸጋሪና ከመስማት ችግሮች ሁሉ ከፍተኛው የሚባለው ነው:: ይህ ክፍል ተጎዳ (Sensorineural HearningLoss) የሚባለው የተለያዩ ፍሪኩዌንሲ የሚቀበሉ በኮኪሊያ ጥቅል ውስጥ የሚገኙት መልዕክት ተቀባዮች ወደ እምሮ የሚየስተላልፉ ነርቮች የሰውነትን ሚዛን የሚጠብቁት ክፍሎች ሲጎዱ ነው::

**<u>ሁለቱም ክፍሎች ሲጎዱ</u> (Mixed Hearing Loss):-** የእንግሊዝኛው Mixed የሚለው ሁለት ነገሮች ሲቀላቀሉ ነው:: በዚህኛው ዘዴ በአየሮርግቢግቢት መሰና  ከል የሚፈጠር የመስማት መሳን (Conductive Hearing Loss )ና ከአእምሮ ጋር  የተያዘው የነርቭ መልዕክት ተቀባይ (SensorineuralHearing Loss) መስማት መሳን ሁለቱም በአንድ ሰው ላይ ሲከሰቱ ነው::  ይህ ማለት ይህ ጉዳት ሰው ጆሮቹ ፈጽሞ በየትኛውም ዓይነት መንገድ ድምጽን መቀበል አይችልም ማለት ነው። እእንግዲህ የመስማት መሳን አይነቶች እእነዚህ

ሲሆኑ አሁንም በመጠን የተለያዩ ስለሆኑ የመስማት ችሎታን መለኪያ በሆነው ኦዲዮ ሜትር በመጠቀም ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ መሠረት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡

| የመስማት ጉድለት መጠን | ለመስማት የሚችለው የድምጽ ጉልህነት | በትምህርት አሰጣጥ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ |
|---|---|---|
| ቀላል የመስማት ጉድለት | 20 - 40 ዴሲቤል | ራቅ ያለ ድምጽን መከታተል ስለሚያስፈልገው ክፍል ውስጥ ወደ መምህሩ ቀረብ ብሎ መቀመጥ አለበት፡፡ |
| መጠነኛ የመስማት ጉድለት | 40 - 55 ዴሲቤል | ጠጋ በማለት ንግግርን ያዳምጣል፡፡ የክፍል ውይይትን ለመከታተል ያዳግተዋል፡፡ ረዳት መስሚያ መርጃ ያስፈልገዋል፡፡ |
| በመጠኑ ከባድ የመስማት ጉድለት | 55 - 70 ዴሲቤል | ረዳት የመስሚያ መሣሪያ ያስፈልገዋል፡፡ የምልክት ቋንቋ ሥልጠናም ያስፈልገዋል፡፡ |
| ከባድ የመስማት ጉድለት | 70 - 90 ዴሲቤል | በጣም የጎላ ድምጽ ብቻ ይሰማል፣ የምልክት ቋንቋ መሰረታዊ ቋንቋው መሆን አለበት፡፡ |
| መስማት የማይችል (Deaf) | 90 ዴሲቤልና ከዚያም በላይ | ንዝረት ሊሰማው ይችላል፡፡ መረጃዎችን መሰብሰብ የሚችለው በድምጽ ሳይሆን በማየት ስለሆነ ምልክት ቋንቋ የመግባቢያውና የመማሪያ ቋንቋው ሊሆንለት ያስፈልጋል፡፡ |

**መስማት ለተሣናቸው ሁኔታዎች ያለመመቻቸት የተነሳ የሚከሰቱት ዋና ዋና ችግሮች መካከል የሚከተሉት በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።**

- ከአካባቢ ኅብረተሰብ ጋር በቀላሉ ለመግባባት ያለመቻል፣
- ለተለያዩ አደጋዎች መዳረግ፣

◈ የገለልተኝነት (የብቸኝነት) ስሜት መኖር፣

እነዚህ ሁሉ ችግሮች መስማት ለተሣናቸው በመማር ሂደት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራሉ::

**የመስማት መሳን መከላከያ ዘዴዎች (Preventive Methods)**

- በእርግዝና ወቅት በየጊዜው የህክምና ክትትል ማድረግ፣
- በእርግዝና ወቅት ያለሐኪም ትዕዛዝ ማንኛውንምመድሀኒት አለመውሰድ፣
- በእርግዝና ወቅት የሚሰጡ ክትባቶችን ተከታትሎ መውሰድ፣
- ለሕፃናት የሚሰጡ ክትባቶችን በወቅቱ መውሰድ፣
- ከፍተኛ ትኩሳትና የራስ ምታት ሕመም ሲሰማ ፈጥኖ ወደ ሐኪም ቤት መሄድ፣
- ሹል በሆኑ ነገሮች ጆሮን አለመነካካት፣
- የጆሮ ሕመም ያለበት ሰው የጆሮው ሕመም ሲነሳበትና ሳል ወይም ጉንፋን ሲይዘው በአፋጣኝ መታከም፣
- በጆሮ ላይ ጉዳት ሊያደርስ ከሚችል ከፍተኛ ድምፅ መራቅ፣
- በወሊድ ጊዜ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ ማድረግ፣
- የግልና የአካባቢን ንጽሕና መጥበቅና የመሳሰሉት ናቸው

**መ/ መስማት የተሳናቸውን መለየትና አሰሳ ማድረግ**

የአንድ ሕፃን መስማት መሳንን በመጀመሪያ የሚለዩት ወላጆች፣ መምራንና የሕፃናት ሐኪሞች ናቸው:: ይህ ጉዳት የደረሰባቸው ህጻናት ብዙ የመለያ ባሕሪያትን ያንጸባርቃሉ።

ዩሲድክና አልጎዝን (1995) አሥር ዋና ዋና የመስማት መሳንን የሚገልፁ ምልክቶችን በተማሪዎች ላይ ሊታዩ እንደሚችሉ የገለጹ ሲሆን እነሱም የሚከተሉት ናቸው።:

- ☞ በቃል የሚነገሩ መመሪያችንና ገለጻዎችን ያለመረዳት፣
- ☞ የመምህራንና የሌሎች ተናጋሪዎችን የከንፈር መነቃነቅን ይከታተላሉ፣
- ☞ እራሳቸውን ወደ ተናጋሪው አዙረው ያዳምጣሉ፣
- ☞ የተወሰኑ  ቃላትን ለንግግራቸው ይጠቀማሉ፣
- ☞ የንግግር ድምፃቸው ደካማ ነው፣
- ☞ በቋንቋ እእድገታቸው የዘገዩ ናቸው፣
- ☞ ከበስተጀርባቸው በኩል ሲጠሩ አይሰሙም፣
- ☞ በንግግራቸው ደካሞች ናቸው፣
- ☞ ሬድዮና ቴሌቪዥን ከፍተኛ ድምፅ ካልሆነ ስለማይሰማቸው ድምፅ ጨምረው ይሰማሉ::
- ☞ የጆሮ ሕመም ሁልጊዜ የሚሰማቸው ከመሆኑም በላይ ኢንፌክሽንና መግል አዘል ሁኔታዎች ይታዩባቸዋል።

ቀጥሎ የቀረቡ ዘዴዎችን በመጠቀም የመስማት ችግር የለባቸውን ሕፃናት በማሰስ መለየት ይቻላል::

- ♥ የችግሮቹ መንስዔዎችንና ያስከተለትን ችግሮችን ከወላጆች ጋር በመሆን ለይተው ማጥናት (ታ1994)፣
- ♥ የተለያዩ አማራጮች የያዙ ቴስቶችን መጠቀም፣ ያለመስማት ችግር ምን ያህል እንደሆነ ለይተው ማወቅ (ፊርላንድ 1989)፣
- ♥ የጋራ  ቴስቶችንና ጨዋታዎችን ለምሳሌ የቀለበት ጨዋታዎችን እእንዲጫወቱ በማድረግ ወዘተ... (ፊርላንድ 1989) መስማት የተሳናቸውን ህጻናት ማሰስ እንደሚቻል ጠቁመዋል::

**ሠ/ የትምህርትና ማኀበራዊ እገዛ አሰጣጥ ዘዴዎች (Intervention Strategies)**

መስማት የተሣናቸውን ሕፃናትና ወጣቶችን በማሰስ ከለየን በኋላ አሰፈላጊውን የትምህርትና የማህበራዊ ዕገዛዎችን በመስጠት እንዲማሩና እንዲሰለጥኑ ዕድል በመስጠት እንደማንኛውም ዜጋ ውጤታማና አምራች ማድረግ ይቻላል:: ለዚሁም ዋናው መፍትሄ መስማት ከተሳናቸው ሕፃናትና ወጣቶች ጋር መገናኘት መቻል ነው:: ይህም የመገናኛ ዘዴዎችን ክህሎት ማዳበር ነው::

መስማት ከተሳናቸው ጋር እንዴት መገናኘት እንደምንችል (Methods of Communication) ስቹልዝ ካርፔንቴርና ትሩንቡል (Schulze, Carpenter and Trunbull, 1991) የተባሉ ሊቃውንቶች የሚከተሉትን መሰረታዊ ዘዴዎች አስቀምጠዋል።

**<u>በቃል መናገር</u>** (Oral Method) በዚህ ዘዴ እንዲናገሩና እንዲሞክሩ ዕድል በመስጠት የሚከናወን ነው:: ይህ ዘዴ፡-

- የማዳመጥ ሥልጠና በመስጠት (Auditory training)
- በከንፈር የማንበብ ሥልጠና (Lip Reading) በመስጠት
- መጫወት ዘንግ ምልክትእጅ በማድረግ (Cued Speech) የሚከናወን ይሆናል።

**<u>በመመሪያዎች መገናኘት</u>** (Manual Communication) ይህም የምልክትና የጣት ፊደላትን ቋንቋ በመጠቀም የሚተገበር ነው።

**<u>ሁሉንም የመገናኛ ዘዴችዎች በመጠቀም</u>** (Total Communication) ይህ ዘዴ በከንፈር፣ በመናገር፣ በመጻፍ፣ በማንበብና የምልክት ቋንቋን በመጠቀም ማስተማርና ማሠልጠንን ያጠቃልላል።

**ረ/ መስማት ለተሳናቸው የሕይወት ክህሎትና ሙያዊ እድገት እገዛ አሰጣጥ**

በት/ቤቶች መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን ለመርዳት መምህራንና ሌሎች የትምህርት ባለሙያዎች የሕይወት ክህሎትን ለማዳበርና ከእኩዮቻቸው ጋር በአንድነትእ እንዲማሩ የሙያ እድገት እገዛ ሊሰጡ ይችላሉ:: እ

የመስማት ጉድለት ያለባቸው ተማሪዎችን ለመርዳት በት/ቤት መደረግ ያለበት ነጥቦች፡-

- በተናጋሪውና በተማሪው መካከል ያለውን ርቀት መቀነስ፣
- የጎላ ድምጽ ከመናገር በግልጽና በዝግታ መናገር፣
- በአካባቢ የሚሰማውን ድምጽ ማስወገድ፣
- ተማሪው በክፍል ውስጥ በሌላ ድምጽ በማይረበሽበት ሁኔታ ፊት ለፊት እንዲቀመጥ ማድረግ፣
- በትምህርት ጊዜ በንግግር ወቅት ፊት ለፊት የመተያየት እድል በሰፊው እእንዲኖራቸው ማድረግ፣
- በትምህርትና በንግግር ወቅት ለተማሪዎች መልዕክት ለማስተላለፍ ሲፈለግ ሙሉ ዓረፍተ ነገሮችን መጠቀም፣
- ትምህርት ሲሰጥና ወደ አንድ ዕቃ አቅጣጫ ለማመልከት ሲፈለግ ተማሪውና መምህሩ ዕይታን እንዲጠቀሙ ማድረግ፣ ለተማሪው በትምህርት ወቅት የመምህሩን ማስታወሻ የሚጽፍለትና የሚተረጉምለት ጓደኛ እእንዲኖረው ማድረግ፣
- ተማሪው በራሱ እንዲሰራ ማበረታታት ማኀበራዊ ክህሎቶችን ማስተማር፣
- የመስሚያ መሳሪያውን በመክፈት ተማሪው መስማቱን ማረጋገጥ ያሻል::

**መልመጃ ሦስት**

**<u>ቀጥሎ ያሉት ጥያቄዎችን እውነት ወይም ውሸት በማለት መልሱ::</u>**

1. በደንብ የማይሰሙ ሕፃናት በትምህርት አቀባበላቸው ብዙም አይጎዱም::
2. መስማት መሣን ከልደት በፊት፣ በልደት ጊዜና ከልደት በኋላ ሊከሰት ይችላል::

3. ቀላል የመስማት ጉድለት ያለበት ሕፃን ራቅ ያለ ድምጽን መከታተል ስለሚያስፈልገው እክፍል ውስጥ ወደ መምህሩ ቀረብ ብሎ መቀመጥ የለበትም፡፡
4. የመስማት መሳንን ለመከላከል በእርግዝና ወቅት የሚሰጡ ክትባቶችን ተከታትሎ መውሰድ ብዙ ጥቅም የለውም፡፡
5. የመስማት መሳንን የሚገልፁ ምልክቶች አንዱ የመስማት ችግር ያለባቸው ሕጻናት የመምህራንና የሌሎች ተናጋሪዎችን የከንፈር መነቃነቅን መከታተላቸው ነው ።
6. በት/ቤቶች መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችን ለመርዳት መምህራንና ሌሎች የትምህርት ባለሙያዎች የሕይወት ክህሎትን ለማዳበርና ከእኩዮቻቸው ጋር በአንድነት እንዲማሩ የሙያ እድገት እገዛ ሊሰጡ አይችሉም፡፡
7. የመስማት ችግር ያለበት ተማሪ በራሱ እንዲሰራ ማበረታታት ማኀበራዊ ክህሎቶችን ለማስተማር ያግዛል።
8. ሙሉ በሙሉ የማይሰሙ ሕፃናት በምልክት ቋንቋ እና በጽሑፍ ካልሆነ በስተቀር በድምፅ ማንኛውንም ትምህርት ሊማሩ የማይችሉ ናቸው፡፡
9. እድገታቸውን ሳይጨርሱ የሚወለዱ ህጻናት ምንም ዐይነት የመስማት ችግር አይየገጥማቸውም።
10. በአየር የሚተላለፍ ድምጽ የመቀበል እጦት በውጭው፣ በመካከለኛው ወይም በውስጠኛ ው ጆሮ ውስጥ በሚፈጠሩ የመርገብገብ ችግሮች መንስኤነት የሚመጣ ነው።

### 2.2.3 የአእምሮ ውስንነት ያለባቸው ሕፃናት

የአእምሮ ውስንነት ችግር ታ ታሪክን ስንመለከት ቀደም ባሉት ጥንታዊት ግሪክና በሮማን ዘመን እንደነበረና በኋላም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በአንዳንድ ቦታ ላይ እንደተጠቀሰ ባር (1913)፣ቀጥሎም ሊንድማንና ማክሊንታኖግ (1951) በፃፉት ጽሑፎቻቸው ጠቅሰዋል።

ሰዎች ስለ አእምሮ ውስንነት ችግር ቀደም ብለው ያወቁ ቢሆንም ከታሪክ እንደምንረዳው ከሆነ ከእርግማን፣ ከሀጢያት፣ ከክፉ መናፍስቶች ሥራና ከመሳሰሉት ጋር በመያያዙ የጉዳቱ ሰለባ የሆኑት ሰዎች የተለዩ፣ የተጠሉ፣ የሚገደሉ፣ ብዙ መከራና መገለል ይደርስባቸው ነበር:: ዘመንእ እየተለዋወጠ በመጣ ቁጥር ሰዎችም የአእምሮ ዕድገት ዝግመት ላለባቸው ሰዎች ያላቸው አመለካከት ቀሕ እያለ እ እየተቀየረ አሁን ያለንበት ዘመን ተደርሷል:: በተለይም ዘርን ማጥራት በሚል ብዙ ስቃይ በነበረበት ጊዜ ካነር /1964/ ያንን ሃሳብ እንደሚከተለው ገልጸታል።

*«የአእምሮ ውስንነት ችግር ያለባቸው ሰዎች ለሥልጣኔ የማይሆኑ፣ ለትምህርት ቤት ሸክሞች፤ ዘገምተኞችን የሚወልዱ፣ የድህነት ድር አድራች ፣ ጨካኝ፣ በሽተኞች ናቸውና ህብረተሰቡን ለማጥራት ሲባል ለብቻቸው ተገልለወ እንዲቀመጡ እነሱን ከህብረተሰቡ የሚለይ ጠንካራ ግንብ መኖር አለበት::»*

*ሀ/ <u>የአእምሮ ውስንነት ችግር ትርጉም</u>* <u>(**Definition of** Intellectual Disabilities)</u>

የአእምሮ ውስንነት ችግር ማለት የአአእምሮ ብሰለት ጉልህ በሆነ ልዩነት ከአማካዩ በታች መሆንና የግላዊና ማኅበራዊ ክንዋኔዎች ብቃት መጓደል ማለት ነው:: የአእምሮ ውስንነት ችግር ያለባቸው ሕፃናትና ወጣቶች በአእምሮአዊ ዕድገታቸው ማለትም በግንዛቤ፣ በማስታወስ፤ በአስተሳሰብ፣ በቋንቋ ዕድገታቸው፣ በስሜት ሕዋሳት መዳበር፣ በማኅበራዊ ግንኙነትና በመሳሰሉት ሁኔዎች ዕድገታቸው ከዕድሜ እ እኩዮቻቸውዮች አንፃር ሲታዩ ዝግመት የማታይባቸው ናቸው::

ይሁን እንጂ የአእምሮ ውስንነት ችግር ምንድነው? ለሚለው ጥቅል ጥያቄ አንድ ምላሽ መስጠት አይቻልም:: ምክንያቱም የአእእምሮ ውስንነት ችግር እንደየሰዉ አመለካከት የተለያየ ነው::  ለምሳሌ ያህል የአእምሮ ውስንነት ችግር ማለት:-

- **በግለሰብና በቤተሰብ** አመለካከት ትርጉም ከሆነ አንድን ተግባር የማከናወን ድክመት ማለት ነው::
- **በመንግስት ደረጃ** ሲታይ ትርጓሜው በውስጡ ትምህርታዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እእንድምታ ያለው ሆኖ ይገኛል::
- **በሐከኪሞች እእይታ** የአእምሮ ውስንነት ችግር ማለት እእንደማንኛውም ዓይነት በሽታ በህክምናእእርዳታታ ሊያገኝ እእንደሚችል ይታመናል።
- **ለማህበራዊ ጠበብቶች** ደግሞ የአእእምሮ ውስንነት ችግር  ማለት ማህበረሰቡ የፈጠረውና ሰዎች ለአንድ ሰው ተግባር የሚሰጡት የተለየ ምላሽ  እንደሆነና ከዚህ የተለየ  ሚስጥር የለውም ይላሉ::

የአእምሮ ውስንነት ችግር ከአሁን በፊት የነበሩት ስያሜዎች በሙሉ አሉታዊ ችግሩን የሚያጎሉ እንጂ የሰውየውን ጠንካራ ጎን የሚያበረታታቱ አልነበሩም:: ከእነዚህም ውስጥ በእንግሊዝኛው ቃል (Dump, stupid, Immature, Defective, subnormal, Feeble minded, Incompet, Dull)  የሚሉ ነበሩ::

በአሁኑ ጊዜ  የተለያዩ የአእምሮ ውስንነት ችግር  ትርጉሞች ከጊዜ ወደ ጊዜ እእየተሻሻሉ የመጡ ሲሆን ይህ ሂደት ወደፊትም በተመሳሳይ ሁኔታ እንደሚቀጥል ይታመናል። በ1992 የአሜሪካ የአእምሮ ውስንነት ችግር ያለባቸው ማህበር (AAID) ያወጣው ትርጉም: - በአንድ የተግባር ክንዋኔ ወቅት የሚታይ ውሱንነት መግለጫዎች ሆኖ ከአማካይ ደረጃ በታች ዝቅ ያለ አእምሮአዊ ክንውንን አሁን ባሉ ተግባሮች ላይ የሚገልጽ ሲሆን በተጨማሪም ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ህይወትን ለመምራት በሚያስችሉ የዕለት ተዕለት ተግባራት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ባህሪያት ውስንነት ያሉበት መሆኑን ያሳያል። እነዚህም የመግባባት፣ ራስን መንከባከብ፣ የጤንነት፣ የአኗኗር፣ የማህበራዊ ክህሎቶች፣ የማህበረሰቡ ንብረት አጠቃቀም፣ ራስን የመምራት፣ ለራስ የሚደረግእ ጥንቃቄና የቀለም ትምህርቶች፣ በመዝናኛና በሥራ ቦታታ ሲሆኑ  በእነዚህ ተግባራት የአእምሮ  ዝግመት ከ18 ዓመት እእድሜ በፊት የሚገለጽ ነው::

"Intelectual Disability refers to substantial limitations in present functioning. It is characterized by significantly sub average intellectual functioning. Existing concurrently with related limitations in two or more of the following applicable adaptive skills areas, communication self care, home living social skills, community use self – direction, health retardation manifests before age 18."

እንግዲህ ይህ የአእምሮ ውስንነት ችግር ትርጉም ያለቀለት ባይሆንም በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ በተጨማሪም የአእምሮ ውስንነት ችግር ትርጓሜ ተቀባይነት እእንዲያገኝ ከዚህ የሚከተሉትን እሳቤዎች ማካተት አለበት፡፡

- የባህል የቋንቋና የመግባባት ልዩነቶችን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባና አግባብነት ባለው ጥናታዊ አሰሳ የተደገፈ ሲሆን፣
- ራስን ችሎ ሕይወትን ለመምራት የሚያስችል የዕለት ተዕለት ተግባራት ክህሎቶች ባህሪያት ላይ የሚያንባርቁት ውስንነቶች በዚያው በሚኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ ካለ የዕድሜ እእኩዮች ጋር ተወዳድሮ ዝቅተኛነቱ የተረጋገጠ ሲሆን፣
- ራስን ችሎ ሕይወትን ለመምራት የሚያስችሉ ክህሎቶች ውሱንነት በተቃራኒው ካለ ጥንካሬ ወይም ከሌላ ሰው ችሎታ ጋር የተገናዘበ ሲሆን፣
- አግባብነት ያለው ድጋፍ ለተራዘመ ጊዜ በማድረግ የአእምሮ ውስንነት ችግር ያለበትን ሰው የሕይወት ተግባሩን በአጠቃላይ ሊያሻሽል የሚችል መሆኑን የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

**ለ/ <u>የአእምሮ ውስንነት ችግር ደረጃዎች</u>**

የአእምሮ ውስንነት ችግር የተለየዩ ደረጃዎች አሉት፡፡ እ እነዚህም መለስተኛ፣ መካከለኛ፣ ከባድና በጣም ከባድ ተብለው ይታወቃሉ፡፡

**<u>መለስተኛ የአእምሮ ውስንነት ችግሮች</u> (Mild Intellectual Disabilities )**

ይህን ችግርለማወቅ አስቸጋሪ ነው፡፡ በሰለጠነው ዓለም ቀላል የአእምሮ ውስንነት ችግር ያለባቸው ግለሰቦች ችግራቸው የሚታታወቀው ት/ቤት ከገቡ በኋላ ሲሆን በትምህርት አቀባበል በጣም ይደክማሉ፣ ከአንድ የትምህርት ደረጃ ወደሌላው ለመተላለፍ ያዳግታቸዋል፡፡ ቀላል የሆነ የአእምሮ ውስንነት ችግርን በአብዛኛው በኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ውስጥ አሁን ባለንበት የዕድገት ደረጃ በትክክል መለየት አይቻልም፡፡ ሆኖም ዘመናዊ የትምህርት ዕድል ባገኙትና የኢኮኖሚ ብቃት ባላቸው ጥቂት የኀብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ ይህንን ሁኔታ ማወቅ ይቻላል፡፡

<u>**መካከለኛ የአእምሮ ውስንነት ችግሮች**</u> **(Moderate Intellectual Disabilities)**

መካከለኛ የአእምሮ ውስንነት ችግር ያለባቸው ሕፃናት በአካላዊ እድገታቸው እምብዛም ከሌሎች ህፃናት አይለዩም። በንግግር ችሎታቸው፣ በማኀበራዊና ግላዊ ክንዋኔዎች የአእምሮ ዕድገት ዝግመትእ እንደሌላቸው ልጆች አይቀላጠፉም:: ከጉዳቱ ነጻ እንደሆኑት ህጻናት በወቅቱ መናገር አይችሉም:: የዕድገት ወቅቱን ጠብቀው ራሳቸውን ችለው መመገብ፣ ልብሳቸውን መልበስ፣ ንፅህናቸውን መጠበቅ፣ ወዘተ. የመሳሰሉትን ለማድረግ ይቸግራቸዋል:: የመማር ችግር ይገጥማቸዋል:: አንዳንድ ጁሎፎች እንሚጠቅሱት በረቱ ቢባል በተምህርታቸው ከ2ኛ ክፍል በላይ አይዘልቁም::

<u>**ከባድ የአእምሮ ውስንነት ችግሮች**</u> **(Severe Intellectual Disabilities)**

በዚህ ደረጃ የማገኙ ሕፃናት የአካዳሚና የአእምሮ ብስለት እ እንዲሁም ግላዊና ማኀበራዊ ክንዋኔን በተመለከተ እእድገታቸው በጣም አዝጋሚ ነው:: ከባድ የአእእምሮ ውስንነት ችግር ያለባቸው ሀጻናት መቆም፣ መሄድ፣ መናገር፣ ራሰን መመገብ መቻል ወዘተ... የመሳሰሉትን መተግበር አይችሉም። ቢችሉም እንኳን ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት ካለፈ በኋላ ነው። እንዲሁም እነዚህ ህጻናት ትምህርት ቤት ገብተው ለመማር አይችሉም:: አብዛኛዎቹ ህጻናት ተደራራቢ የአካል ጉድለት ይታይባቸዋል። የእጅና የእግር ክፍሎች መጣመም፣ መቆልመም፣ የእይታ ወይም የመስማት ችግር፣ ሽንት ወይም ዓይነምድርን መቆጣጠር አለመቻልና የመሳሰለት ይከሰታሉ።

<u>**በጣም ከባድ የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ችግሮች**</u> **(Profound Intellectual Disabilities)**

በጣም ከባድ የአእምሮ ውስንነት ችግር ያለባቸው ሕፃናት አካላዊ ዕድገታቸው እጅግ ዝቅተኛ ሲሆን አካላዊ ጉድለቶች ይኖሩባቸዋል:: ዕድሜያቸው ከሕፃንነት ጊዜ ሳያልፍ ይሞታሉ:: ካደጉ በኂላም በቂ ትኩረትና ክብካቤ ስለማይደረግላቸው በምንም ዓይነት ራሳቸውን አይችሉም:: የግል ንፅህናቸውንእ በሌላ ሰው ድጋፍና እርዳታ ካልሆነ በስተቀር በራሳቸው ማከናወን አይችሉም:: ከባድና በጣም ከባድ የአእምሮ ውስንነት ችግር ካለባቸው ሰዎችመካከል 1/3ኛ ያህሉ በሚጥል በሽታ ይጠቃሉ:: በሌላ በኩል የአእምሮ ውስንነት ችግር ደረጃ በኢንተለጀንስ ቴስት አማካይነት ሊለካ የሚችል ነው:: ይህ መለኪያ የተለያዩ ጥያቄ-ዎችን ያቀፈ በመሆኑ የአእምሮ እ እድገት ደረጃን ለመለካት የሚያገለግል ነው:: ሆኖም መለኪያው አስተማማኝ የሚሆነው ከተመሳሳይ ባህል፣ ቋንቋ እድገት ደረጃና ሁኔታዎች ለመጡ ተፈታኞች ሲቀርብ ነው::

**ሐ/. የአእምሮ ውስንነት ችግሮች መንስዔዎች**

የአእምሮ ውስንነት ችግሮች መንስዔዎች ብዙውን ጊዜ በሚገባ አይታወቅም። ችግሩ ከ6 እስከ 15 በመቶ አይበልጡም:: ይሁን እንጂ የአዕምሮ ውስንነት ችግር መንስዔዎችን በሁለት ዋና ዋና ደረጃዎች ከፍለን ስናያቸው እእያንዳንዳቸው ደግሞ ከተለየዩ ምክንያቶች ሊመጡ እእንደሚችሉ ልንረዳ ይገባናል:: ዋና ዋናዎቹም:-

ሀ/ አካላዊ መንስዔዎች

ለ/ ባህላዊ መንስዔዎች ተብለው ይከፈላሉ::

**አካላዊ መንስዔዎች (Organic /Physiological Causes)**

አንዳንድ ጊዜ የሚወለዱ ልጆችን አካላዊና አእምሮአዊ ጤንነት ከሚወስኑት አንዱ የዘር ውርስ ነው:: ለዚህም መንሰዔ የዘር ውርስ ተሸካሚዎች /ክሮምዞምስ/ ጉድለት፣ የውስጥ ሰውነት ንጥረ ነገሮች ሂደት /ሜታቦሊዝም/ መቃወስና በዘር ውርስ የሚፈጠሩ የአንጎልና የነርቭ ህመሞች ይገኙበታል:: አንዳንድ ጊዜ የሚወለዱ ሕፃናት አንጎል ወይም የራስ ቅል በጣም ትንሽ ሆኖ ወይም ከአንጎላቸው ውስጥ ከመጠን ያለፈ ፈሳሽ ሞልቶና የራስ ቅሉ በጣም ተልቆ ሲገኝ ለአእምሮ ውስንነት ችግር ሊያጋልጥ ይችላል::በፅንስ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችም ለዚህ ጉዳት ሊዳርጉ ይችላሉ:: እእነዚህም:-

- የደረሰ ፅንስ በፀረ-ህዋስ /ጀርሞች/ መለከፍ / ኢንፌክሽን/:- ለምሳሌ እ እንደ አባላዘር በሽታዎች ዓይነት የፀረ ህዋስ ልክፍት በእርግዝና ወቅትእ የእናትየው ላይ ከደረሰ ይኸው ሁኔታ ወደ ፅንሱ ይተላለፋል፣
- ✓ የአልኮል ሱሰኝነት፣ የሲጋራና ሌሎች ሊጎዱ የሚችሉ መድሀኒቶችንና አደንዛዥ ዕፆችን በእርግዝና ወቅት መውሰድ፣
- ✓ በእርግዝና ወቅት የሚከሰቱ የደም ግፊቶች፣ በቂ ምግብ አለማግኘትና ሌሎች በሽታዎች፣
- ✓ በወሊድ ጊዜ የሚደርሱ ችግሮች፣
- ✓ በማኅፀን ውስጥ እእድገቱን ሳያበቃ ያለጊዜ የሚወለድ ሕፃን / Immature birth/

- ✓ በምጥ ጊዜ ከሚፈለገው በላይ መቆየትና የኦክስጅን እጥረት፣
- ✓ በወሊድ/በምጥ ጊዜ የሕፃኑ አመጣጥ ያልተስተካከለ መሆን፣
- ✓ የእናትና የተረገዘው ሕፃን ደም አንድ ዓይነት /አለመሆን / RH Factor/ ወዘተ ናቸው።

**ባህላዊ መንስዔዎች (Cultures Familiar Causes)፡-** እነዚህ መንሴዎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሲሆኑ እእነርሱም፡-

- ✓ ድህነት፣ የቤተሰብ መፍረስ፣ የወላጆች ወይም የአሳዳጊዎች ቸልተኛነት የባህሪ ተፅዕኖ የመሳሰሉ ናቸው፡፡
- ✓ ሌሎችም የተለያዩ የአካባቢ የኢንዱስትሪ ብክለቶች (ለምሳሌ የብረታ ብረትና የሌሎች ብናኞች)
- ✓ በሕፃንነት ጊዜ የሚደርሱ አደጋዎች፣ የተለያዩ ብክለቶች፣ የምግብ አለመመጣጠን፣ በምግብ ውስጥ የአዮዲን ጨው እጥረት ሲኖር ወዘተ. ናቸው፡፡

**መ/ የአእምሮ ውስንነት ችግር ያለባቸውን መለየትና አሰሳ ማድረግ**

የአእምሮ ውስንነት ችግር እንደጉዳቱ ዓይነትና ደረጃ የሚለያይ ሲሆን አሰሳ ማድረግና መለየት የሚከተሉትን ባሕሪያትን ሊያሳይ ይቻላል፡፡

- ✓ ከሌሎች ጋር የመግባባት ችግር፣ በመማር ሂደት አሉታዊ ተፅዕኖ ሲያሳድር፣
- ✓ በባሕርይ ቁጠኝነት፣ ሰውን የመራቅና ኃግለኝነት፣ ዕምቢተኝነትና አጥፊነት፣
- ✓ ጉዳቱ ተደራራቢ ሲሆን እእንደልብ ለመንቀሳቀስ አለመቻል፣
- ✓ በአካላዊ ዕድገት መጫወት፣ ወዘተ ሲሆኑ ሌሎች ባህሪያትና ችግሮች ደግሞ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ቀርበዋል።

**የአእምሮ ውስንነት ችግር ያለባቸው ሕፃናት ባህሪያትና የሚታዩ ችግሮች**

| ዘርፍ | የሚያሳዩት ጠባይ | የሚታዩባቸው ችግሮች |
|---|---|---|
| የግንዛቤ<br>Cognitive | ውስን የማስታወስ ችሎታ፣ውስን መረጃና አጠቃላይ እውቀት፣ውስብስብ ነገሮችን መረዳት አለመቻል<br>ዘገምተኛ የትምህርት አቀባበል | ትኩረት ማጣት<br>ደካማ የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፣የመግባባት ችግር፣ፈተና መውደቅ፣መደበኛ ትምህርት በጣም የሚከብዳቸው |
| የቀለም ትምህርቶች<br>Academic | የቀለም ትምህርት ይዘቶችን የመማር ችግር፣ብዙ የሚማሯቸውን የትምህርት ይዘቶችን ለመሥራትና ለመገንዘብ አለመቻል ወይም ውሱንነት መኖር፣ፕ ሮብሌሞችን የመፍታት ችግር፣ይዘቶችን የመረዳት ችግር | ውስን ትኩረት<br>ደካማ የአደረጃጀት ክህሎቶች<br>አጠያየቅ አለማወቅ /ውስንነት/<br>መመሪያ አለመከተል<br>በጊዜው የመከታተልና ሌሎች በት/ቤት የሚከናወኑ ክህሎቶች ውሱንነት |
| የአካል<br>Physical | በአካልና በአእምሮ እእድገት መካከል ያለው ሰፊ የችሎታ ጉድለት | ከአካላዊ ዕድገት አኳያ ሲነፃፀር ከሚጠበቀው በታች የወረደ አፈጻጸም |
| የባህሪ<br>Behavioral | የግልና የማህበራዊ ኑሮ ውሱንነት፣<br>ከአቻ ጓደኞቹ ጋር እእኩል መራመድ አለመቻል፣<br>የግል ኑሮ ክህሎት እጦት፣<br>የሥራ አፈፃፀም ድክመት /ውሱንነት/፣ | ዘገምተኛነትና ዳተኝነት መነጫነጭ፣<br>በክፍል ውስጥ መረበሽ፣<br>በማህበራዊ ኑሮ ገለልተኝነት፣<br>አግባብ ያልሆነ አስነዋሪ ተግባር ማከናወን |
| የመግባባት<br>Communication | ዝቅተኛ የቋንቋ እእድገት<br>ለማዳመጥናለመናገር የቃላት ውሱንነት | መመሪያ የመከተል ችግር<br>ጥያቄ የመጠየቅ ችግር<br>የመግባባት ችግር |

**ሠ/ የአእምሮ ውስንነት ችግር ላለባቸው የሚደረግ የትምህርትና ማኅበራዊ ኑሮ እእገዛ አሰጣጥ (Intervention Strategies)**

- **ከጅምር/ ቀደም ብሎ የሚደረግ እገዛ (Early Intervention)**

የአእምሮ ውስንነት ችግርን ለመከላከል የሚቻለው የችግሩ መንስዔ በሆኑ ነገሮች ላይ በወቅቱ እርምጃ በመውሰድ ጉዳቱ እንዳይከሰት በማድረግ ነው፡፡ በእርግዝና ወቅት ከመጀመሪያው አንስቶ እእስከ ወሊድ ድረስ አልፎ አልፎ ወደ ጤና ባለሙያ ዘንድ በመሄድ የእርግዝናውን ሂደት መከታተል አስፈላጊውን ህክምና በማድረግ በሚወለድ ሕፃን ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሁኔታዎቸን በጊዜ ለማስወገድ እጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የወሊድ አገልግሎትን በማሻሻል በልምድ አዋላጆችና በጤና ባለሙያች አማካኝነት መወሰድ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች የሳይንሳዊ ዕውቀትን ሥልጠና በመስጠት ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችን በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ ይቻላል፡፡ ስለዚህ፡ -

**<u>በእርግዝና ወቅት ለእናትቱ ተገቢውን እንክብንቤ ሁሉ ማድረግ</u>፣ ይህም፤-**

- ☞ የሥራ ጫናን መቀነስ፣
- ☞ አካላዊ ጉዳት እእንዳይደርስ ጥንቃቄ ማድረግ፣
- ☞ ለበቂና ለተመጣጠነ ምግብ (Maternal Nutrition) ትኩረት መስጠት፣
- ☞ የአልኮል መጠጦችንና አደንዛዥ ዕጾችን አለመወሰድ፣
- ☞ ሲጋራ አለማጨስ

**ለህጻናት ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ፡-**

- ☞ ሕፃናት ህመም ወይም ለየት ያለ ባህል ሲታይባቸው ወደ ሕክምና አገልግሎት መስጫ ተቋም መውሰድ፣
- ☞ የእናት ጡት ወተት በብቃት እንደያገኙ ማድረግ፣
- ☞ የአትክልት ዓይነቶችንና የእንሰሳት ተዋፅኦን በበቂ መጠን እእንደያገኙ መጣር፣
- ☞ አዮዲን ያለበት ጨው መመገብ ወይም የአዮዲን ዘይት በመርፌ መልክ መስጠት፣
- ☞ ዕድሜ በጣም ሳይገፋ በወቅቱ ልጅ መውለድ፣

**ረ/ የአእምሮ ውስንነት ችግር ላለባቸው ትምህርታዊ እእገዛ ስለመስጠት**

ከላይ በጽሑፉ እ እንደተገለጸው የአእምሮ ውስንነት ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የግንዛቤ፣ የቀለም ትምህርቶች፣ የአካል የአእምሮእእድገት አለመመሳሰል፣ የባህሪና የመግባባት ችግር እንዳለባቸው ተገልጿል፡፡ ስለሆነም እነዚህ ሁሉ ችግሮችእ እያሉ የተለየ አገልግሎት ሳያገኙ መደበኛውን የሥርዓተ-ትምህርት መርህ ግብር ከሌሎች መሠል ጓደኞቻቸው ጋር እኩል መማር ይቸግራቸዋል፡፡ ስለዚህ በመደበኛ ት/ቤት ውስጥ እንደችሎታቸውና ፍላጎታቸው መጠን ልዩ እገዛ እ እየተሰጣቸው ሊማሩ ይችላሉ፡፡ በትምህርቱም ሂደት ከቀለም ትምህርት ይልቅ ወደ ሙያ ትምህርት (Vocational) እእንዲያደሉ ማድረጉ አስፈላጊ ነው፡፡

የአእምሮ ውስንነት ችግር ያለበትን ተማሪ ለማሰልጠን የትምህርቱ አሰጣጥ ሁኔታ የሚከተሉትን ተግባራት በአካተተ መልኩ ቢሆን ይመከራል።

- በተግባር የተደገፈ እእንዲሆን ማድረግ፣
- በተቻለ መጠን ከቃል ይበልጥ በሥዕል የተደገፈ ቢሆን ፣
- ሥልጠናው ወደፊት ግለሰቡ በሚሰራበት ቦታ እእንዲሆን ማድረግ፣
- የመርሳት ችግር ስላለባቸው ሥልጠናው ጥልቀትያለው (Intensive) ቢሆን ፣
- የተማሪውን ውጤት በየጊዜው መገምገም፣
- በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ አንድ ግብ ብቻ ትኩረት ያደረገ ትምህርት መስጠት፣
- ተማሪው ለሚሳሳተው ሁሉ ወዲያውኑ እርምትና ግብረ መልስ (Immidiate Feed Back) መስጠት፣
- ማትጋት፣
- ለማገዝ በቅድሚያ የተማሪውን የሥራ ፍንጭእእንደያሳይ መገፋፋት ወዘተ... ናቸው።

**ሰ/ የአእምሮ ውስንነት ላለባቸው የሕይወት ክህሎትና ሙያዊ ዕድገት እእገዛ አሰጣጥ**

ራስን ችሎ ሕይወትን ለመምራት የሚያስችል የዕለት ተዕለት ተግባራት (Adaptive Behavior)፣ የአእምሮ ውስንነት ችግር ያለበት ሰው የችግሩ ደረጃ ሊሰጠው የሚገባው አገልግሎት ወዘተ. የሚወሰኑት ምን ያህል ራስን ችሎ ህይወቱን ለመምራት የሚያስችል የዕለት ተዕለት ተግባራትን ያከናውናል? ብለን ልንጠይቅ ይገባል፡፡ እእነዚህ የዕለት ተዕለት ተግባራት ባህሪያቶች ከዚህ እእንደሚከተለው ቀርበዋል።

1. **በግል የሚከናወኑ (Independent – functioning) ተግባራት፡ -**
   - መብላት
   - መጸዳዳት
   - የግል ንጽህና አጠባበቅ
   - የልብስ አያያዝ
   - ጉዞ
   - በአጠቃላይ በግል የሚከናወኑ
2. **አካላዊ ዕድገት (Physical Development)**
   - ስሜታዊ ዕድገት
   - የእንቅስቃሴ ዕድገት
3. **ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ (Economic activity)**
   - የገንዘብ አያያዝ
   - በጀት አመዳደብና ግብይት
4. **የቋንቋ ዕድገት (Language Development)**
   - አገላለጽ
   - መረዳት /መገንዘብ/
   - ማህበራዊ የቋንቋ ዕድገት
5. **የቁጥርና የጊዜ ዕውቀት**

**6. የቤት ውስጥእንቅስቃሴዎች**

- ንጽህና
- የምግብ ቤት ተግባራት (Kitchen duties)
- ሌሎች የቤት ውስጥ ተግባራት

**7. የሙያ ተግባራት (Vocational Activities)**

**8. ራስን መምራት (Self - direction)**

**9. ኃሀላፊነትን መውሰድ (Responsibility)**

**10. ማህበራዊነት (Socialization) ናቸው።**

**መልመጃ: አራት**

**<u>ከተራ ቁጥር 1-5 ላሉ ጥያቄዎች በ “ሀ”ምድብ የተገለፁትን በ “ለ” ምድብ ከተገለፁት ጋር በማዛመድ መልሱ::</u>**

**ሀ**

1. የአእምሮ ብሰለት ጉልህ በሆነ ልዩነት ከአማካዩ ምታች መሆንና የግላዊና ማኅበራዊ ክንዋኔዎች ብቃት መጓደል ማለት ነው::
2. ዕድሜያቸው ከሕፃንነት ጊዜ ሳያልፍ ይሞታሉ:
3. የአእምሮ ውስንነት ችግር ለማሰስ የሚረዳ ዘዴ
4. በእርግዝና ወቅት የአልኮል መጠጦችንና አደንዛዥ ዕጾችን አለመወሰድ
5. የችግሩ መንስዔ በሆኑ ነገሮች ላይ በወቅቱ እርምጃ በመውሰድ ጉዳቱ እንዳይከሰት ማድረግ

**ለ**

ሀ. ጉዳቱ ተደራራቢ ሆኖ እእንደልብ ለመንቀሳቀስ አለመቻል

ለ. የአእምሮ ውስንነት ችግር እእንዲፈጠር ይረዳል ::

ሐ. ከጅምሩ ጀምሮ የሚደረግ እገዛ

መ. በጣም ከባድ የአእምሮ ውስንነት ችግር ያለባቸው ሕፃናት

ሠ. የትምህርቱ አሰጣጥ ሁኔታታ በተግባር የተደገፈ እእንዲሆን ማድረግ

ረ. የአእምሮ ውስንነት ችግር

### 2.2.4 የአካል/የእንቅስቃሴና የጤንነት ጉዳት

**ሀ/ትርጉምና ምንነት**

የአካልና የጤና ችግር ዓይነታቸውና የጉዳቱ መጠን የተለያዩ ብዙ ችግር ያለባቸው ሰዎችን የሚያቅፍ ነው፡፡ የአካልና የጤና ጉዳት ዓይነቱ ከመብዛቱ የተነሣ በጋራ የሚታይ ባህሪ የለውም፡፡ መገለጫዎቹም በጣም የተለያዩ ናቸው፡፡ ከነዚህ መካከል የአርቶፔዲክና የማዕከላዊ ነርቭ መጎዳት ዋነኛው ነው፡፡ የአርቶፔዲክ ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ችግራቸው የአጥንት መጋጠሚያዎች የእግርና የእጅ ጡንቻዎችእንደልብ አለመታዘዝ ነው፡፡ በተጨማሪም እ እነዚህን የሰውነት ክፍሎች የሚቆጣጠረው የአእምሮ ክፍል መጎዳት የግለሰቡን እ እንቅስቃሴ ከቁጥጥር ውጪ ያደርገዋል፡፡ የአርቶፔይክና የነርቭ ጉዳት ዓይነቶች የሚታወቁት የትኛዎቹ የሰውነት ክፍሎችእ እንደተጎዱ በመለየት ነው፡፡ እእነዚህም የጉዳቱ ዓይነትና መጠን፡-

- ፖድሪፕሌጂያ ሁለት እእጆችና ሁለት እእግሮች ሲጎዱ
- ፓራፕሌጂያ  ሁለት እግሮች ሲጎዱ
- ሂሚፕሌጅያ የቀኝ ወይም የግራ የሰውነት ክፍል ሲጎዳ
- ሞኖፕሌጂያ አንድ እእጅ ወይም አንድ እግር ሲጎዳ የሚሰጥ መለያ ሲሆን
- ሴብራል ፓልሲ እእንቅስቃሴን የሚቆጣጠረው የአእምሮ ክፍል ሲጎዳ
- ስፓስቲስቲ በጡንቻ መኮማተር ምክንያት የማዲርስ የእንቅስቃሱ ቅንብር ችግር
- አታቲዩይድ የእራስ የእጅና የእግር እእንቅስቃሴ ከቁጥጥር ውጭ ሲሆን
- አታክሲክ ሚዛን ያለመጠበቅ ችግር
- ፖሊዮ የልጅነት እልምሻ
- የአንጎል መጎዳት በተለያዩ ውጫዊ አደጋዎች መንስኤነት የሚያጋጥም የአንጎል መጎዳት
- ቃጠሎ (በእሳት መቃጠል የተነሳ የሚደርሱ የቆዳ መሸብሸብ የጡንቻዎች መኮማተር..
- የአከርካሪ አጥንት መጎዳት

**ለ/ የአካልና ጤንነት ጉዳቶች ዓይነቶችና መንስዔዎቻቸው**

**የልጅነት እልምሻ**

የልጅነት እልምሻ የሞተር ነርቮችን የሚያጠቃ በሽታ ነው:: የልጅነት እልምሻ ከቦታ ወደ ቦታታ የመንቀሳቀስ ችግርን ያስከትላል:: አንዳንድ ጡንቻዎች ተግባራቸውን ማከናወን ያቅታቸዋል:: የልጅነት እልምሻ አብዛኛውን ጊዜ የሚከሰተው በህጻናት ላይ ነው::

**መንስኤው**

የልጅነት እልምሻ የሚከሰተው በዓይን ሊታይ በማይችል ቫይረስ /ረቂቅ ህዋስ/ አማካኝነት ነው:: ይኸው ቫይረስ በምንመገበው ምግብ፣ በምንጠጣቸው ፈሳሾች ውስጥና እንዲሁም በበሽታታ በተጠቁ ልጆች ዓይነ ምድር ውስጥ ሊገኝ ይችላል:: በሽታው ከአንዱ ወደ ሌላው ሊተላለፍ የሚችለው በሽታው በያዘው ሰው ዓይነምድር፣ በሳል ወይም በማስነጠስ አማካኝነት ነው::

**የሚያስከትለው ችግር**

በሁኔታዎች ያለመመቻቸት የተነሳ ከሚከሰቱት ችግሮች መካከል የሚከተሉት ዋናዎቹ ናቸው።

- የመጀመሪያ ደረጃ ችግሮች የሆኑት እንደ እንፎሎዊንዛ፣ተቅማጥ፣ ትውከት፣ የመሳሰሉት መከሰት፣
- የክንዶችና የእግሮች እንቅስቃሴ አለመኖር፣
- የሁለተኛ ደረጃ ችግሮች መከሰት ማለትም እእንደ መራድና አንዳንድ የሰውነት ክፍሎችን ለማንቀሳቀስ ያለመቻል፣
- አንዳንድ የአካል ክፍሎች መደበኛ ተእግባራቸውን ማከናወን ስለሚቀንሱ ወይም ስለሚያቆሙ እእድገታቸው አገልግሎት እንደሚሰጡት ጡንቻዎች ያለመሆን፣
- ምበሽታው የተጠቁ እእጆችና እእግሮች አንሰው፣ ቀጥነው ወይም አጥረው መገኘት፣
- በሽታው በሚያስከትለው ከፍተኛና ተደራራቢ የሆነ የአካል ጉዳት ተጎጂወእ እንደልብ ተንቀሳቅሶ የግል ህይወቱን ለመምራት ያለመቻል::

የልጅነት ልምሻን መከላከል የሚቻለው በዋነኝነት በክትባት ነው፡፡ ይህ ክትባት ለሁሉም ህጻናት እእድሜያቸው ስድስት ወር ከመድረሱ በፊት መሰጠት አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአካባቢንና የግል ንፅህናን መጠበቅ ለመከላከሉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ በድንገተኛ የእጅና የእግር መዛል ምልክት የታየበትን ህጻን በአፋጣኝ በ3 ቀናት ውስጥ ወደ አቅራቢያው ጤና ድርጅት ወስዶ ማስመርመርና በወቅቱ ማሳከም ተገቢ ነው፡፡

አንድ ህጻን የጉንፋን መያዝ ምልክቶች ከታዩበት መርፌ መወጋት የለበትም፡፡ ምክንያቱም ህፃኑ የልምሻ በሽታው /ቫይረስ/ ከብዶት ከሆነ መርፌ የተወጋበት ክንድ ወይጸ እግር እእንቅስቃሴውን ሊያቆም ይችላል፡፡ ህፃኑ በጡንቻው ላይ ህመም የሚሰማው ከሆነ ፎጣዎችን በሙቅ ወሁኃ ነክሮ የታመሙትን ጡንቻዎች መያዝ ህመሙእ እንዲቀንስለት ይረዳዋል፡፡ በልምሻ ቫይረስ የተጠቁትን እግሮችና እጆች ሊንቀሳቀሱ በሚችሉበት አቅጣጫዎች ሁሉ ማንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡ በይበልጥም በአካባቢው ወደሚገኘው የህክምና ተቋም በመሄድ ባለሙያን ማነጋገር በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡

**ፓራላይዝድ/ሽባ መሆን (Paralysis)**

ችግሩ የጡንቻ መድከም ወይም አቅም ማጣት ነው፡፡ ይህም ሁኔታ በሰውነት ክፍል በሚገኙ ጡንቻዎች ላይ ሊከሰት ይችላል፡፡ በአመዛኙ ግን የሚደረገው በእግር ጡንቻዎች ላይ ነው፡፡ ፓራላይዝድ መሆን ባንድ የሰውነት ክፍል በኩል የሚከሰት የስሜት እእንቅስቃሴ ችግር ሲሆን መንስዔው በተለያዩ ምክንያቶች በአንጎል ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡ በአንጎል ግራ በኩል የሚደርስ ጉዳት በስተቀኝ የአካል ክፍል ላይና በስተቀኝ የአንጎል ክፍል ላይ የሚደርስ ጉዳት በስተግራ የአካል ክፍል ላይ ሽባነትን ያስከትላል።

**መንስኤው**

ፓራላይዝድ መሆን ወይም በከፊል ፓራላይዝድ መሆን በአንጎል ላይ በሚደርስ አደጋ፣ በበሽታታ ወይም ወደ አንጎል በሚሰራጭ የደም መጠን ማነስ ሊከሰት ይችላል፡፡

**የሚያስከትለው ችግር፡-** በመጀመሪያ ደረጃ በአንድ የሰውነት ክፍል በኩል ያነሰ የእንቅስቃሴ ቁጥጥር መኖር፣/ ከተገቢው በላይ ወይም በታች የሆነ እ እንቅስቃሴ መኖር፣/ የቀነሰ ስሜት ወይም አነስተኛ ንቃት በአንድ የሰውነት ክፍል በኩል መታየት፣ የመናገር ችግር/ በቀኝ በኩል በማለት አጋማሽ ሽባነት ሊታይ ይችላል፡፡

**በሁለተኛ ደረጃ ችግሮች፡-** የመገጣጢያ ግትርነት/የእጅ መታጠፍናእየእግር ወደታች በሚያመለክት አቅጣጫ መሆን፣ አነስተኛ የሰውነት ሚዛን አጠባበቅ በመራመድና በመብል ጊዜ በሚገባ መቆጣጠር ያለመቻል ናቸው፡፡

**መከላከያው**

ከፊል ሽባነት አንዴ ከተከሰተ ለመፈወስ የሚያስችል ምንም መድሀኒት የለም፡፡ አንጎል ከደረሰበት ጉዳት የማገገምና ሌሎች የሰውነት ክፍሎችን የመቆጣጠር ልምምዱ እንደገና የሚያደርግበት ጊዜ እእንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡ የእጅ ወይም የእግር ወይም የመገጣጠሚያ ግትርነትን ለመከላከል ከፊል ሽባነት የደረሰበትን የሰውነት ክፍል በየቀኑ በብዙ አቅጣጫዎች ማንቀሳቀስ ይረዳል፡፡ በከፊል ፓራላይዝድ የሆነ ሰው እእጁንና እግሩን በማንቀሳቀስና እነዚህን የስውነት ክፍሎች ተግባር ላይ በማዋል አጋማሽ ሽባ የሆነውን የሰውነት ክፍል ለመጠቀም እንደገና መለማመድ አለበት፡፡

**<u>የአካል መንቀጥቀጥ /Cerebral Palsy/</u>**

የአካል መንቀጥቀጥ የአንጎል ጉዳት ከወሊድ በፊት፣ በወሊድ ጊዜ ወይም በመጀመሪያዎቹ የህይወት ዓመታት በአንጎል ጉዳት ምክንያት የሚከሰት ሰውነትን የመቆጣጠር አቅም የሚቀንስ በሽታ ነው፡፡

**መንስኤው**

የአካል መንቀጥቀጥ በሽታ መንስዔዎች በወሊድ ወቅት የሚደርስ የአንጎል ጉዳትና ኃሀይለኛ ትኩሳት ወይም መመረዝ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**የሚያስከትለው ችግር፡-** የተመቻቹ ሁነታዎች ካለመኖራቸው የተነሳ ከሚከሰቱት ችግሮች መካከል የመጀመሪያ ደረጃ ችግሮች ተብለው የሚጠቀሱት፡-

- የንግግር አለመስተካከል
- የእንቅስቃሴ መስተጓገል
- ሽንትና ዓይነ ምድርን ያለመቋጠር
- ዝቅተኛ ግንዛቤና ያለመግባባት ችግሮች □□□የሁለተኛ ደረጃ ችግሮች ተብለው የሚጠቀሱት □□□□-

- የመገጣጠሚያዎች ግትርነት
- በአንድ ቦ□ ብቻ ከመቆየት የተነሳ የሚፈጠር የአልጋ/የጫና/ ቁስል፣
- ምግብ ለመመገብ፣ ለመጠጣት፣ ለመጸዳዳት፣ ለመልበስ፣ ለሚደረግ □□□□ ተግባር ረዳት መፈለግ፣
- ተከ□□ይና ከቁጥጥር ውጭ በሆነ እ□ንቅስቃሴ የተነሳ ያለደጋፊ ለመቀመጥ፣ ለመቆም ወይም ለመራመድ ያለመቻል፣

**መከላከያው**

የአካል መንቀጥቀጥ በሽታ በእርግዝና ወቅት እንዳይከሰት እናቶች መርዝነት ያላቸውን ነገሮችና ሌሎች ከባድ መድሀኒቶች ከመውሰድ እእንዲቆጠቡና በቂ የሆነ የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡

**<u>እጅና እግርን ማጣት/መቆረጥ</u>**

ከአካል ክፍሎች አንዱን ወይም ሁለቱን ማለትም እእጅን ወይምእ እግርን በተለያዩ ምክንያቶች ማጣት ማለት ነው፡፡

**መንስኤው**

የአካል ክፍልን ማጣት መንስዔው የተለያዩ አደጋዎች፣በሽታዎች፣ ፈንጂና የጦር መሣሪያዎች የጉዳቱ መንስኤዎች ሲሆኑ በተጨማሪም በወሊድ ወቅት አንዱ ወይም ከዚያ በላይ አካል ጎድሎ ህፃን ሊወለድ ይችላል፡፡

**የሚያስከትለው ችግር**

በተመቻቸ ሁኔታ አለመኖር ከሚከሰቱት ችግሮች መካከል

- የአካል ክፍል ማጣት/ ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ችግር ነው፡፡/
- ሰውነት አንዱን የአካል ክፍል በሚያጣበት ወቅት ተከትለው ከሚመጡት የሁለተኛ ደረጃ ችግሮች ውስጥ ከቀሪው አካል በላይ ያለውን የአካል ክፍል በአንድ አቅጣጫ ብቻ ከፍ አድርገው ከመያዝ የተነሳ በመገጣጠሚያዎች ላይ ግትርነት መፍጠር፣
- በተቆረጠው ቦታ ላይ ቁስል ወይም ኢንፌክሽን መፈጠር፣

- የእግር ወይም የእጅ መቆረጥ የደረሰበት ሰው የዕለት ከዕለት ተግባሩን እ እንደልብ ለማከናወን አስፈላጊውን ድጋፍ/እእገዛ (Assertive Device) ካላገኘ ለመራመድ ወይም ለመስራት ይቸገራል፡፡

**መከላከያው**

ለአካል ክፍሎች መጎዳት ወይም ማጣት ከሚዳርጉ የተፈጥሮና የሰው ሠራሽ አደጋዎች ማለትም ከፈንጂ አደጋ፣ በሥራ ቦታ፣ በትራፊክ ከሚደርሱ አደጋዎች ከእሳት አደጋና ከመሳሰሉት መጠንቀቅ ናቸው።

**<u>የእግር መርገጫ መታጠፍ (Club Foot)</u>**

የታጠፈ የእግር መርገጫ ማለት ከወሊድ በፊት ሕፃኑ ከማህፀን ውስጥእእያለ በአቀማመጥ ችግር በአንድ ወይም በሁለቱ  እግሮቹ ላይ የሚደርስ የቅርጽ አለመስተካከል ነው፡፡ ከሚወለዱ አንድ ሺ ህፃናት መካከል ሦስቱ በእግራቸው ወይም በእግሮች መርገጫ መታጠፍ ጉዳት ይደርስባቸዋል፡፡

**መንስኤው**

የእግር መርገጫ መታጠፍ መንስዔው በውል አይታወቅም። ምናልባት ህፃናት በእርግዝና ወቅት በእናታቸው ማህፀን ውስጥ ከሚኖረው አቀማመጥ የተነሳ የእግሮቻቸው መርገጫዎች ወደ ውስጥ ታጥፈው ሊወለዱ ይችላሉ፡፡ አልፎ አልፎ በአከርካሪ ላይ በሚደርስ ችግር ምክንያት ችግሩ ይከሰታል፡፡ በሰረብራል ፐልሲ /Cerebral plasy ፣በልጅነት እልምሻ፣ በሰውነታችን መገጣጠሚያዎች ላይ በሚከሰት ህመም /Arthritis/ ወይም በሰረሠር ላይ /Spinal Cord/ ከፍተኛ ጉዳት የእግሮች ቀስ በቀስ የመታጠፍ ጉዳት ሊደርስ ይችላል፡፡

**የሚያስከትለው ችግር**

- በመጀመሪያ ደረጃ በእግር ወይም ቆ እግሮች መጫሚያ ላይ የእግር አቅጣጫው ያልተስተካከለ ቅርጽ መከሰት፣ በውስጥ በኩል ያለው የእግር ቆዳ ማጠር፣
- በእግር መታጠፍ በሚመጡ የሁለተኛ ደረጃ ችግሮች የተነሳ በውጪኛው እግር መራመድና በዚህም ሳቢያ የቅርጽ ብልሽትን መባባስና የውጪውን ቆዳ መጎዳት፣

- የእግሮች መጫሚያዎች ለብዙ ጊዜያት በዚሁ አቀማመጥ ከቆዩ አጥንቶች በትክክለኛ ው ቦታቸውና አቅጣጫቸው በማደግ ፈንታ በተዛባው አቅጣጫ የማደግና በዚህም የተነሳ በእንቅስቃሴ ላይ አስቸጋሪ ሁነታ መፈጠር

**መከላከያው**

በአብዛኛው የታጠፈ ግር ከባለሙያ በሚገኝ ድጋፍ ሊስተካከል ይችላል፡፡ ጥሩ የህክምና ውጤት ለማግኘት ግን ህክምናው ህፃኑ እንደተወለደ ወዲያውኑ መጀመር ይኖርበታል። ምክንያቱም ዓመታት ባለፉ ቁጥር ከሕፃነኡ እድገት አኳያ ማስተካከል በጣም እየከበደ ስለሚሄድ ነው፡፡ ህክምናው በማሸትና በውስጥ እግር በኩል ያለውን ቆዳ በመዘርጋት እንዲሁምእእግርን ለረዥም ጊዜ በማንቀሳቀስና በትክክለኛው አቅጣጫ ይዞ በማቆየት ነው፡፡ የተዛቡ አጥንቶችን ለማስተካከል የቀዶ ጥገና ህክምና ሊደረግ ይችላል፡፡ የታጠፈ እግር ላለባቸው ልጆች ወላጆች የእግር ቅርፅ ብልሹነትን ለማስተካከል ማድረግ የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ለመረዳት እንዲችሉ ፈጥነው ወደ ህክምና ተቋምእ እንዲሄዱ መምከር ያስፈልጋል፡፡

**<u>የሥጋ ደዌ (Leprosy)</u>**

የሥጋ ደዌ በባሲለስ ጀርም በሳይንሳዊ አጠራሩ ማይጾ ባክትሪም ሌፕሬ /Myco Bactrium Leprae/ በሚባለው የባክቴሪያ ህዋስ አማካኝነት የሚመጣ በሽታ ነው፡፡ በሽው የታወቀው ሃንሰን በመባል በኖርዌይ ሀገር እ.ኤ.አ. በ1873 ነው፡፡ ይህም ለብዙ ሺህ ዓመታት በብዙ ሀገሮች ባህልና ሃይማኖት በህዝቦች ዘንድ ስር ሰዶ የቆየውን በሽታው በዘርና በመሳሰሉት ይመጣል የሚል የተሳሳተና የተዛባ አመለካከት የሻረና ለዘመናዊ መድሀኒት መገኘት ፈር የቀደደ ነው፡፡ ከዚህ አኳያም ብዘዎቹ ሃገሮች የሃንሰን በሽታ /Hansen’s Disease/ እእያሉ ስለሚጠሩት ለበሽታውና ለተጠቂው የተሰጡ የተዛቡ አሉታዊ ስሞችን ከማስቀረት አኳያ ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል፡፡ የሥጋ ደዌ በህክምና ከሚድኑ በሽታዎች ውስጥ የሚመደብ ነው፡፡ ይሁን እእንጂ ህክምናው በወቅቱና በአግባቡ ካልተወሰደ በሽታው በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡ ሆኖም ከሥጋ ደዌ አካል ጉዳተኞች ጋር በአንድ አውቶቡስ መቀመጥ፣ በምግብ ቤቶች፣ በትምህርት ቤቶች በመቀመጫዎች፣ በመታጠቢያ ቦታዎች በመቀራረብ ንኪኪነት ከለሌ በሽታው አይዝም፡፡

**<u>የሚጥል በሽታ /ኤፒሌፕሲ/</u>**

የሚጥል በሽታ ማለት በተደጋጋሚ ህሊናን አስቶ የሚያንቀጠቅጥ ሁኔታ ተብሎ ሊገለፅ ይችላል፡፡ እከሴረብራል ኮርቴክስ /Cerebral Cortex/ የሚነሳ ሆኖ የንዝረቱ ስርጭት ወደ መሐል አንጎል ከደረሰና ወዲያውኑ መላውን አንጎል ካዳረሰ የሚጥል በሽታን ያስከትላል፡፡ ይህም በሽታታ የተነሳበት ሰው ከጥቂት ሴኮንዶች እስከ ሦስት ደቂቃ አካሉ ይንቀጠቀጣል፣ ይግተረተራል፣ እእንዲሁም በሙሉ ወይም በከፊል በአካል፣ በህሊና ንቃትና ግንዛቤ ያለው ቁጥጥር ይጠፋል፡፡

አንዳንድ የሚጥሉ በሽታዎች ሙሉ በሙሉ ባይድኑም 80% የሚሆነው በመድሀኒት ዕርዳታታ በቁጥጥር ስራ ሊውል ይችላል፡፡ ፐቲትማል የሚባለው የሚጥል በሽታ ከዕድሜእዕድገት ጋር ሊተው የሚችል ሲሆን ግራንድማል ደግሞ ከባድ የሚጥል በሽታ ሆኖ ሙሉ በሙሉ ባይድንም በህክምና እርዳታ በቁጥጥር ሥር ይውላል፡፡ በሽታው ሊነሳ ሲል ከሚያሳያቸው ምልክቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ የአይን መርገብገብ መፍጠጥ፣ ፊትን መቋጠርና ፊታ ማድረግ፣ የመረበሽ ጠባይ ማሳየት፣ መፍዘዝና መደነጋገር ናቸው፡፡ የበሽታው ሰለባ የሆነ ሰው ተደራራቢ የሆነ ችግር የሚደርስበት ሲሆን ይህም ከከባድ ጉዳት እስከ ሕይወት ማጣት የሚያስከትል ነው፡፡

**መንሰኤው**

ለሚጥል በሽታ መነሻ ምክንያት ከሚሆኑት መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ከወሊድ በፊትና በወሊድ ጊዜ ሕፃኑ ላይ የሚደርስ አደጋ ሲኖር ሲሆን ብዙ ጊዜ ከእርግዝና ወቅት የጤንነት መታወክና አስቸጋሪ ምጥ ጋር ሊዛመድ ይችላል።
- በአንጎል ውስጥ በተፈጥሮ ያልተስተካከለ ወይም የጎደለ ክፍል ሲኖር (Cerebral Malformation)
- በሕፃንነት ጊዜ የነበሩኃሀይለኛ የትኩሳት በሽታዎች፣ የአንጎል ኢንፌክሽን (infection) ለምሳሌ ማጅራት ገትር /Meningitis/ ኢንሴፊላይተስ (Encephalitis) የወባ በሽታ ሲከሰቱ፣
- በአንጎል ውስጥ የሚያድጉ እጢዎች (Brain Tumors)፣
- በሰውነት ውስጥ የሚገኙ ንጥረ ነገሮች (Chemicals) በልክና በትክክል አለመገኘት፣

- በተለያዩ አደጋዎች ጭንቅላት ሲመታና አንጎል ላይ ጉዳት ሲደርስ፣
- የአካል በመርዞች መበከል (Poisoning)፣
- በዘር መተላለፍና የመሳሰሉት ናቸው::

**የሚያስከትለው ችግር**

ሕመሙ ያለበት ሰው ወድቆ ሕሊናውን ከሳተ ለሀጩና ምራቁ አፍኖት መተንፈስ ይከለክለዋል፣ ጉንጭቹንና ምላሱን ይነክሳል፣ ጥርሶቹን ይሸራርፋል:: እየጋሉ ብረቶች፣ ድንጋይና ስለት ነገሮች ተሸከርካሪዎች ባሉበት ቦታና በእሳት አቅራቢያ በመሳሰሉት ላይ ከወደቀ ከባድ ጉዳት ያስከትላል::

**መከላከያው**

የሚጥል በሽታን ለመከላከል መወሰድ ካለባቸው ርምጃዎች ዋና ዋናዎቹ:-

- አንድ ሴት ካአረገዘችበት ጊዜ ጀምሮ እስክተወልድ ድረስ የህክምና ክትትል ማድረግ፣
- ማዋለድ በህክምና ተቋማትእእንጂ ባልሰለጠነ -አዋላጆችእእርዳታ እንዳይካሄድ መጠንቀቅ፣
- የተወለደውን ሕጻን ወዲያውኑ የጤንነቱን ሁኔታ ማስመርመር፣ ሕፃኑ ከተወለደ በኋላ ፀረ ስድስት ክትባት ማስከተብ፣ የህክምና ክትትል ማድረግ፣
- ራስ ቅል /ጭንቅላት ላይ ምንም ዓይነት አደጋ እንዳይደርስ መከላከል፣
- የራስ ቅል በዱላ፣ በድንጋይ፣ በመኪና አደጋና በሌሎች ሁኔታዎች ሲጎዳ ስለሚችል ጥንቃቄ መውሰድ ነው::

**ሐ/ የአካልና የጤንነት ጉዳት/ችግር ያላቸውን መለየትና ማሰስ**

እእንግዲህ የአካል ጉዳት በአእምሮ መጎዳት፣ በተለያዩ ውጫዊ አደጋዎች መጋለጥና በጦርነት ሊከሰት የሚችል ሲሆን በእናቶች በኩል በሚመጡ አንዳንድ ኢንፌክሽን፣ በወሊድ ወቅት በሚያጋጥሙ ጉዳቶችና ከወሊድ በኋላ በሚያጋጥሙ መጎዳቶችም ችግሩ ሊከሰት ይችላል:: የአካል ጉዳት ሁሉ የአእምሮ መጎዳትን አያመለክትም:: ይህም ማለት

ሁሉም የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች አእምሮአቸው የተጎዳ ነው ማለት አይደለም፡፡ አንዳንዶቹ የተዋጣላቸው የአእምሮና የሥነ ጥበብ ባለቤቶችሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**መ/ የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ባህሪያት**

1. ጡንቻን የመቆጣጠር ችግር፣
2. ሚዛን የመጠበቅ ችግር፣
3. ያልተስተካከለ የእግር አረማመድ፣
4. እጅ፣ እግርና ሌሎችም የሰውነት አካሎች የመተሳሰር ሁነታ፣
5. ውሱንእንቅስቃሴ፣
6. ዝግ እርምጃ፣
7. ስለራሳቸው አሉታዊ አመለካከት መፍጠር፣
8. ማህበራዊ ግንኙነት የመፍጠር ችግር ዋናዎቹ ናቸው።

የአካል ጉዳት ያለባቸው ህፃናት የጉዳታቸው መጠንና ሁኔታ የተለያየ ሆኖ ጉዳቱ ነጻ ሆነው ከመንቀሳቀስ ሆስፒታል እስከ ማስተኛት ያለውን ሊያጠቃልል ይችላል፡፡ የችግሩ ሁኔታ በጨቅላነታቸው ከታወቀና ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ/ተግባር ከተከናወነ ጉዳቱ ሊያስከትል የሚችለውን አሉታዊ ሥነልቦናዊ ችግር መቀነስ ይቻላል፡፡ እነዚህም የማስተካከያ እርምጃዎች/ተግባራት(interventios)፡-

1. የእንቅስቃሴ ልምምድ፣
2. የመርጃ መሣሪያዎች ድጋፍ መስጠት፣
3. በህክምና የህመሙን መጠን መቀነስ፣
4. ቀዶ ጥገና ማድረግ ፣
5. በትምህርት ቤት ያሉ መምህራን ህጻናቱ በት/ቤት እያሉ ካመማቸው ፍቃድ መስጠትና በፍርሀትና በይሉኝታ ከአቅማቸው በላይ እንዳይሰሩ መቆጣጠር የሚኖርባቸው ሲሆን በተጨማሪም ፡-
    - የጤናና የአካል ጉዳት የሚያስከትለውን አሉታዊ ሥነልቦና ስሜት መገንዘብ፣
    - የመማሪያ ክፍሎችና የት/ቤቱን ግቢ ለተማሪዎች ምቹ ማድረግ፣

- ተማሪዎች የሚሰሩባቸውን ማቴሪያሎች ማመቻቸትና አስፈላጊም ከሆነ በፍላጎታቸውና በችሎታቸው መሰረት ሁኔታዎችን ማስማማት፣
- አደጋ ሲደርስ ምን ማድረግ እእንደሚገባ ማሳወቅ ወዘተ. ናቸው፡፡

**ሠ/ የአካልና የጤንነት ጉዳት ላለባቸው የትምህርትና ማኀበራዊ ኑሮ እገዛ አሰጣጥ**

ጉዳቱ ያለባቸው ህጻናት በማህበራዊ ኑሮ በሚኖሩበት አካባቢ ለእንቅስቃሴ እንዲደያመቹ ሊከናወኑ የሚገባቸውን ነገሮች ማከናወን የሚያስፈልግ ሲሆንእነዚህም ነገሮች/ ተግባራት፡-

- ጉዳቱ የደረሰባቸው ህጻናት ወደ ህንፃ ውስጥ መግባትና መውጣት እእንዲችሉ ደረጃዎችንና መወጣጫዎችን ማመቻቸት፣
- ወደ አውቶብስ መግባትና መውጣት እንዲችሉ ሁኔታዎች ማመቻቸት፣
- በቁመታቸውና በፍላጎታቸው መጠን ከፍና ዝቅ የሚሉ ጠረጰዛና ወንበር እእንዲኖራቸው ማድረግ፣
- በየመንገዶቹ በግዴለሽነት የሚጣሉእእንቅፋቶችን ማስወገድ፣
- በፍላጎታቸው መጠን በቀላሉ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪ ወንበሮች አቅርቦትን ማሟላት፣
- ከሁሉም በላይ የአካል ጉዳተኝነት በማንኛውም ጤነኛ በሆነ ሰው ላይ በየትኛውም አጋጣሚ (በእሳት አዳጋ፣በመኪና አደጋ፣በጦርነት፣በድብደባ. . . ወዘተ) ሊደርስ የሚችል መሆኑን በመገንዘብ በቤት ውስጥ፣ በት/ቤት፣ በወላጆች፣ በመምህራን፣ በተማሪዎች በአጠቃላይም በህብረተሰቡ አሉታዊ አመለካከት መፍጠር ተገቢ እንዳልሆነ መምከር አስፈላጊ ነው፡፡

**መልመጃ: አምስት**

ከተራ ቁጥር 1-5 ላሉት ጥያቄዎችን በ “ሀ” ምድብ የተገለፁትን በ “ለ” ምድብ ከተገለፁት ጋር በማዛመድ መልሱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሁለት እጆችና ሁለት እግሮች ሲጎዱ | ሀ. ሞኖፐሌጂያ |
| 2. የቀኝ ወይም የግራ የሰውነት ክፍል ሲጎዳ | ለ. ስፓስቲስቲ |
| 3. አንድ እጅ ወይም አንድ እግር ሲጎዳ የሚሰጥ መለያ | ሐ. ሴብራል ፓልሲ |
| 4. እእንቅስቃሴን የሚቆጣጠረው የአእምሮ ክፍል ሲጎዳ | መ. ፖድሪፐሌጂያ |
| 5. ያለመጠበቅ ችግር | ሠ. ፖሊዮ |
| 6. በጡንቻ መኮማተር ምክንያት የሚርስ የእንቅስቃሱ ቅንብር ችግር | ረ. የእግር መርገጫ መታጠፍ |
| 7. የልጅነት እልምሻ | ሰ. አክሲክ |
| 8. በባሲለስ ጀርም በሳይንሳዊ አጠራሩ ማይጆ ባክትሪም ሌፐሬ በሚባለው የባክቴሪያ ህዋስ አማካኝነት የሚመጣ በሽታታ | ሸ. ሂሚፐሌጅያ |
| 9. በአንድ ወይም በሁለት እእግሮች ላይ የሚደርስ የቅርጽ አለመስተካከል | ቀ. የሚጥል በሽታ /ኤ.ፔሌፐሲ/ |
| 10. በተደጋጋሚ ህሊናን አስቶ የሚያንቀጠቅጥ በሽታታ | በ. ኤች አይ ቪ/ኤድስ |
| | ተ. የሥጋ ደዌ |
| | ቸ. ፓራላይዝድ/ሽባ መሆን |

### 2.2.5 የመግባባትና የቋንቋ ችግር ያለባቸው ሕፃናት

**ሀ/ የመግባባትና የቋንቋ ችግሮች ምንነት**

መግባባት (ግንኙነት) ከሁሉም በላይ በንግግርና በመረጃ ልውውጥ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ግንኙነት በመልዕክት ላኪውና (Sender) በመልዕክት ተቀባዩ (Receiver) መካከል የእርስ በርስ ግን ኙነት ወይንም ሀሳብ ለሀሳብ የመለዋወጥ ሂደት (Communication process) ነው፡፡ በዚህ ሂደት፡-

ሀ/ መልዕክቱ ላኪው (Sender)

ለ/ መልዕክቱ (Message)

ሐ/ የመልዕክቱ ማስተላለፊያ አማራጮች (Channels)

መ/ የመልዕክቱ ተቀባይና (Receiver) ግብረ መልስ (Feed Backs) በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

**ለ/ የመግባባት ችግር ዓይነቶች**

ሰዎች ሀሳባቸውን እንደፈላጉትእእንዳይገልጹና መልዕክቱን እንዲያስተላልፉ የሚያደርግ የንግግርና የመግባባት ችግሮች ይከሰታሉ፡፡ ቨርጋሰን (እእኤአ. 1990) የመግባባት ችግር ማለት በማንኛውም ሁኔታ አንድ ሰው እንደልቡ እንዳይግባባ የማደናቀፍ ሂደት ሲሆን ይህም የንግግር ወይም የቋንቋ ችግር ነው ብሏል፡፡ የመገናኘት ወይም የመግባባት ችግር በሁለት ይመደባል፡፡ እእነዚህም የቋንቋና የንግግር ችግሮች ናቸው፡፡

<u>የንግግር ችግር</u>፡- ይህ ችግር ድምጽን በትክክልና በጥራት ለመጥራትና ለማውራት ያለመቻል ችግር ነው፡፡ የንግግር ችግር ያለበት ሰው በመገናኘት ጊዜ እንዳሰበውና እ እንደፈለገው መልዕክቱን ለማስተላለፍና ለመግለፅ ስለማይችል የመናደድና የመጨነቅ ስሜትን/ ባህርይን ያሳያል፡፡

ይስድሌክና አልጎዝን የተባሉ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሊቃውንቶች (እ.ኤ.አ 1995) እንደገለጹት የንግግር ችግር ማለት ድምፅ በትክክል ለማውጣትና ቋንቋን በትክክል ለመጥራት ያለመቻልና በጥራት ያለመናገር ማለት ነው ብለዋል፡፡ ዋና ዋና ችግሮችም፡-

**<u>አንደበትን የመግለጽ ችግር</u>** (Articulation disorders):- ይህም የፈለገውን ድምጽ በመናገር ሀሳብን ለመግለጽ ያለመቻልን ያመለክታል። ስለዚህ ይህ ዓይነት ችግር ያለባቸው ሰዎች ሀሳባቸውን ለመግለጽ ቢችሉም በትክክለኛ ድምፅ አይገልጹም::

**<u>የድምፅ ችግር</u>:-** ይህ ችግር ድምፅን በጥራትና በከረዜማነት በማስተጋባት በሚናገሩበት ወቅት ለማውጣት ወይም እንደፈለጉት ለመግለፅ አለመቻል ነው:: የዚህ ዓይነት ችግር ያለባቸው ሰዎች ድምጻቸው በጣም ጎርናና ወይም ሻካራ ስለሚሆንባቸው ሀሳባቸውን እእንደፈለጉት ወይምእእንደልባቸው አይገልጹም::

**<u>የመናገር ችግር</u>** (Fluency Disorder) ይህ ችግር ሰዎች በሚናገሩበት ጊዜ በመኮላተፍ ወይም በማመሳቀል (Cluttering) ወይም በመንተባተብ (Stuttering/Stammering) ሃሳባቸውን ለመግለጽ ያለመቻልን ያመለክታል። ይህ ችግር ያለባቸውን ሰዎች ሌሎች የማህበረሰቡ አባላት ጉዳቱን ግለሰቡ እራሱ ግለሰቡ ሆን ብሎ ያመጣው ነገር አድርገው ስለሚቀበሉትና በሚናገሩበትም ጊዜ መሳቅ፣ ማፌዝና፣ ማሽሟጠጥ ስለሚያሳዩባቸው በግላዊ ህይወት፣ ጉዳተኞቹ በማህበራዊ ኑሮና በባህላዊ ሁኔታ የመጨነቅና የመፍራት ስሜትን ያሳያሉ::

**<u>የቋንቋ ችግሮች (Language Disorders)</u>**

የቋንቋ ችግሮች የሚከሰቱት ከቅርጽ፣ ከይዘት ወይም ከፍሬ ነገር መልዕክትና ከተግባራት አጠቃቀም ጋር በተያያዙ ሁኔታዎች ነው::

**የቋንቋ ቅርፅ (Language Form):-** በቋንቋ አጠቃቀም፣ በዐረፍተ ነገር አገላለጽ ወዘተ.. ከመሳሰሉት ጋር የሚከሰት የፎኖሎጅይ፣ ሞርፎሎጅና ሰንታክስ ችግሮችን ያጠቃልላል::

**የቋንቋ ይዘት (Languages Content):-** ስንል ለቃላቶችና ዐረፍተ ነገሮች ትርጉምና የዳሰሳ ሃሳቦች ለመግለጽ ያለመቻል ችግሮች ናቸው::

**የቋንቋ ተግባር (Language Function)** ይህ የቋንቋውን መሰረተ ሀሳብ ካለመረዳት የተነሳ ለመግባባት ያለመቻልን የሚያጠቃልል ነው::

**ሐ/ የመግባባት ችግሮች መንስዔዎች**

የመግባት ችግሮች መንስዔዎች ተፈጥሮአዊና አካባቢያው በሆኑ ሁኔታዎች የሚከሰቱ ናቸው፡፡ እእስከአሁን ባሉት የምርምር ውጤቶች መሠረት የሚከተሉት ዝርዝሮች ለችግሮቹ መንስዔዎች ሆነው በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እ

- በድምጽ ማውጫ አካባቢ በሚገኙ የሰውነት ክፍሎች ላይ በሚፈጠሩ በሽታዎች
- ውስጣዊና ውጫዊ የሰውነት አካሎች ላይ በሚደርሱ ጉዳቶች ለምሳሌ የላንቃ አለመቃናት፣ ድምፅን ማስተጋባት በሚችሉ ጡንቻዎች ላይ በሚደርሱ ጉዳቶች ችግሮች የጥርሶች ያለመኖር ... ወዘተ.
- በቅድመ ወሊድ፣ በወሊድ ጊዜና በድኅረ-ወሊድ ጊዜ በሚፈጠሩ ልዩ ልዩ ችግሮች ናቸው፡፡

ቻይና ፍሮድማ የተባለው ሊቃውንት ለሕፃናት የንግግር ችግሮችን ሊያመጡ የሚችሉ ምክንያቶችን እእንደሚከተለው አቅርቧል፡፡

- የአእምሮ እእድገት ውስንነት ችግር
- አካባቢያዊ ተጽእኖዎች
- የመስማት ችግሮች
- የስሜቶች መረበሽና የባህርይ ችግሮች
- የሰውነት የንግግር ክፍሎች በትክክለኛ ቦታታ አለመሆን... ወዘተ ናቸው፡፡

**መ/ የመግባባት ችግር ያለባቸውን ህፃናትን መለየትና ማሰስ**

ሕፃናት ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ ንግግራቸውንና ቋንቋቸውን እእያሳደጉ ይመጣሉ/ያድጋሉ፡፡ በዚህ የእድገታቸው ሂደት አንዳንድ ሕፃናት በጣም ፈጣን ሲሆኑ ሌሎቹ አማካይ ወይም ዝግምተኛ ናቸው፡፡ ስለዚህም በቋንቋ እድገታቸው እኩል አለመሆናቸውን በመረዳት ህፃናትን ለይተው በማወቅና በማሰስ አስፈላጊውን እገዛ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ የንግግር ችግር ያለባቸው ህፃናትና ወጣቶች በት/ቤቶች ውስጥ ልዩ እእገዛ ካልተደረገላቸውና የእድሜ ዕኩዮቻቸው ይህን ግንዛቤ በመያዝ ችግሩ በማንም ላይ

ሊከሰትና ሊኖር እእንደሚችል አውቀው ካልተገኙ ጉዳቱ የደረሰባቸው ህፃናትና ወጣቶች መሳቂያና መሳለቂያ ይሆናሉ::

ሜራክና ሃይኝ (እ.ኤ.አ 1986) እእንደጻፉት የመግባባት ችግሮችን በሚከተሉት ሁኔታዎች መለየት ይቻላል:: :-

- በራሱ ደስተኛ ያለመሆን
- በሚያስተላልፈው ድምፅ መልዕክት ላይ ስህተት መኖር
- በማህበራዊ ግንኙነት ተጠቃሚ ለመሆን ያለመቻል
- የመማር ዕድል ያለመኖር

ስለሆነም የመግባባት ችግሮች ያለባቸውን ሕጻናት ለይተው ማወቅና ተገቢውን እገዛ ማድረግ የመምህሩ ተግባር ነው:: በዚህም ወቅት ህፃኑ ምን ያህል ቋንቋውን መናገር እንደሚችልና የሚናገራቸውን ቃላቶች ማሰስ አንድ ዘዴ ሊሆን ይችላል:: የመግባባት ችግር ያለባቸውን ሕፃናትና ወጣቶች ለመለየት የሚረዱ ዘዴዎችን ሪፖርና ኤሜሪክ (እ.ኤ.አ 1990) በአራት ልዩ ዘርፎች ከፍሎ እንደሚከተለው አስቀምጧል።

ሀ/ የህፃኑን የኋላ ታሪክ ማጥናት

ለ/ የቋንቋ ናሙናዎችን ወስደው ማጥናት

ሐ/ መደበኛ ቴስቶችን ማዘጋጀትና

መ/ ልዩነቶችን መገምገም ናቸው::

**የግለሰቡን የኋላ ታሪክ ማጥናት፡-** ይህም ወላጆችን በማነጋገር:-

- በእርግዝና ወቅት ስለነበረው ሁኔታእእናቶችን በመጠየቅ በጨቅላነት ጊዜ ህፃናት ስለነበራቸው ሁኔታ መረዳት፣
- የወላጆች ቅንብር /አወቃቀር እንዴት እእንደሆነ በመጠየቅ መረዳት፣
- የሕፃኑ የሕክምና ታሪክን ማወቅ ማለትም አስፈላጊውን ክትባትና ሕክምና ወስደው እእንደሆነ መረዳት ፣

- የሕፃኑ የዕድገት ሁኔታዎችን ማወቅ ማለትም የመንቀሳቀስ ሁኔታ፣የግል ጥንቃቄና የመግባባት ክህሎቶችን ጠይቆ መረዳት፣
- እበቤት ውስጥ የሕፃኑ የቋንቋ አጠቃቀምና የቤተሰቦች እገዛ እንዴት እንደነበረ ወዘተ የመሳሰሉትን ማጥናት ማለት ነው፡፡

ቴስቶችን በመስጠት የህፃኑን የሚከተሉት ባህሪያትን መለየትና መገምገም ይቻላል፡፡

መስማት የሚረብሹ ሁኔታዎችን መፈተን፣እነዚህም፡-

- የጋራ የሆኑ ቃላቶች ማስታወስን፣ ዐረፍተነገሮች መረዳትን፣ መመሪያዎች መከተልን አዛዞችን መደጋገምን ወዘተ. ናቸው።
- የማየትና የማንበብ ችግሮችን መለየት፡- ይህም የሕፃኑ የማዛመድ ችለታን፣ታ ፊደላትን ሥዕሎችን፣ የምልክት ቃላቶቸን በቃል የመናገር ችሎታዎችን፣
- የንግግርና የቋንቋ ችግሮችን፣ ሕፃኑ ራሱን ለመግለጽ ያለውን ችሎታ፣ የድምፅና የእንቅስቃሴ ሂደት የማየትን፣ የጽሑፍ ችግሮችን፣ ቁጥሮችንና ፊደላትን የመጻፍና የመገልበጥ ክንዋኔዎችን፣ የማስላት ችግሮችን፣ቀላል የሂሳብ ሥራዎችን የመሥራት ክህሎቶችን፣ የገንዘብ ወይም የሳንቲሞች አቆጣጠርን፣ የቀናት የወራት አቆጣጠርን ለይተው የመናገር ችሎታዎችንና ሌሎች ተመሳሳይ ክህሎቶችን የማከናወን ችሎታዎችን መለየትን ያጠቃልላል።

<u>የቋንቋ ናሙና ወስደው ስለማጥናት</u>፡- ይህም የሕፃኑን የመናገር ችግሮችን የሚያንፀባርቁ ናሙናዎችን መሰብሰብና ሙሉ በሙሉ የማይናገር ከሆነ በጤና ባለሙያ በምልክት ቋንቋ መለየት ይቻላል።

**መደበኛ ቴስቶችን በማዘጋጀትና ልዩነቶችን በመገምገም**፡- እ ሕፃኑ ቋንቋን የሚገልፅበትን/ የሚያስረዳበትን ሁኔታዎችታ ለመለየት የሚረዱ ቴስቶችን በማዘጋጀትየሚፈጸም ሲሆን የህፃኑ ባህሪያትን ለመለየትና ለማሰስ ይረዳል፡፡

**ሠ/ የመግባባት ችግር ላለባቸው ሕፃናት የሚደረጉእእገዛዎች**

- ከቤተሰብ ጋር በመነጋገር
- ከሌሎች የዕድሜ እእኩዮቻቸው ጋር ማነፃፀር

- የችግራቸውን ዓይነት ተከትሎ መለየትና ማዳመጥ
- ልምምድ እንዲያደርጉ ማድረግ
- ማበረታት
- ልጆች እንዳይስቁባቸው ጉዳዩን ግልፅ ማድረግ ወዘተ. ናቸው፡፡

**መልመጃ: ስድስት**

1. እሜራክና ሃይኝ (እ.ኤ.አ 1986) እእንደጻፉት የመግባባት ችግሮችን ለመለየት የሚያስችሉ ዘዴዎችን በዝርዝር ጻፉ፡፡

2. ቻይና ፍሮድማ በተባለው ሊቃውንት አገላለጽ በሕፃናት ላይ የንግግር ችግሮች ሊያመጡ የሚችሉ ምክንያቶችን ዘርዝሩ፡፡

**2.2.6 የባህሪ ችግር ያለባቸው ህፃናት**

**ሀ/ የባህሪ ችግር ምንነትና ትርጉም**

**ትርጉም፡-** የባህሪ ችግር ላለባቸው ህፃናትና ወጣቶች አንድ ወጥ የሆነ ትርጉም ለመስጠት ባይቻልም አንዳንድ ምሁራኖች እእንደገለጹት የባህሪ ችግር ያለባቸው ተማሪዎች፡-

- ስሜታቸው የተረበሸ፤ ለመማር የማይፈልጉ፣
- ከዕድሜ እኩያዎቻቸው ጋር በፀባይ፣ በሥራ መግባባት የማይችሉና የማይፈለጉ ባህሪያትን የሚያሳዩ፣
- ደስተኛ ያልሆኑ፣ በአቋማቸው ፈሪ የሆኑ ወይም ደንብና ህግን የሚጥሱ፣ አድርጉ የተባሉትን ለማድረግ የማይሞክሩ፣ የማይታዘዙ፣ ንብረት ማበላላሸትንና ማውደምን የሚወዱ፣ የሚረብሹና የሚያውኩ... ወዘተ ናቸው፡፡
- የጸባይ ጉድለት፣አለመታዘዝ፣የቅናት መንፈስ፣መረበሽ፣ማጥፋትና ማበላሸት፣
- ራሳቸውን ንቀው መታየት፣ የበታችነት ስሜትን በማሳየት ራሳቸውን መጥላት፣ በአለባበሳቸውና በድርጊታቸው ሁሉ ተስፋ መቁረጥን ማሳየት፣

- ያለመረጋጋት ባህሪን የሚያሳዩ፤ የሚቅበጥብጡ፣ የማያዳምጡ፣ ከት/ቤት አዘውትረው የሚቀሩ፤ በትምህርታቸው ደካማ የሆኑና ዕቅድና ዓላማ የሌላቸው፡
- በማኀበራዊ ህይወታቸው የተጠሉና የተገለሉ፡ ከሌሎች ሰዎች ጋር የማይግባቡ፣ በመጥፎ ድርጊት ላይ የተሰማሩ ወይም ያተኮሩ፣ በስርቆት ስራ ላይ ያተኮሩ፣ የተገለሉ በትምህርት ቤት ከመማር ይልቅ ዙረትን የሚመርጡ፣ የሚዋሹ፣ ውሸትን ለማሳመን የሚጥሩ ናቸው::

ይሰልድክና አልጎዝን (1994) የባህሪይ ችግር ያለባቸው ህፃናት/ወጣቶች የሚከተሉትን ባህሪያትን ያሳያሉ በማለት ገልጿል::

- የግንዛቤ ማነስ ወይም ስሜታዊ መረበሽ የማታይባቸው፣ የማስታወስ ችግር፣ የማሸበር ሁኔታ የሚያንፀባርቁ፣ በትምህርታቸው ከአማካይ ውጤት በታች የሚያመጡ ናቸው። ብሏል::
- በትምህርታቸው ደካሞች፣ የተረሱና ምንም ትኩረት የማይሰጡና የማይጨነቁ ናቸው::
- መረጋጋት የማይታይባቸው፣ የተጨነቁና ደስተኛ ያልሆኑ፣ ከሌሎች ጋር ብዙም ጊዜ የእርስ በርስ ግንኙነት ለማድረግ የማይችሉ፣
- እእንዝላልነት የሚያጠቃቸው፣ ከጥሩ ነገር ይልቅ መጥፎ ነገሮችን ለማከናወን የሚወዱ፣ ረባሾች፣ ተንኮለኞችና ትምክህተኞች ናቸው በማለት አጠቃሏል።

**ሐ/ ለባህሪ ችግር መንስኤዎች፡-**

እንደሌሎች የአካል ጉዳቶች ሁሉ የባህሪ ችግሮች ሊከሰቱ የሚችት ከወሊድ በፊት፣ በወሊድ ጊዜና ከወሊድ በኋላ በሚከሰቱ የተለያዩ ክስተቶች ነው:: ለምሳሌ ከወሊድ በፊት በእርግዝና ጊዜ በእናቲቱ ላይ የሚከሰቱ ሁኔታዎች ማለትም በቂ ምግብ ያለማግኘት፣ አልኮልና ዕፅችን መውሰድ፣ ለነፍሰጡር እናቶች የሚሰጡ ክትባቶችን ያለመውሰድ፣ ያለሐኪም ትእዛዝ የማይፈቀድ መድሀኒቶችን መውሰድ ወዘተ ናቸው::

- <u>በአካባቢያዊና በግላዊ ሁኔታዎች :</u>-የሚኖሩበት አካባቢ ተፅዕኖ፣ የኀብረሰቡ የአኗኗር ሁኔታዎች፣ የእድሜ እእኩዮቹ ተጽዕኖ፣ ወቅታዊ ነባራዊ ሁኔታዎች /የሚዲያ ተፅዕኖ/፣ ከባህል የሚወረሱ ባህሪያት ወዘተ. ናቸው::

**በአካባቢያዊ ሁኔታዎች፡-**

በቤትና ትምህርት ቤት አካባቢ በሚከሰቱ ተፅዕኖዎች፡- ለምሳሌ በልጅና በቤተሰብ መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች፣ በወላጆች መካከል የሚፈጠሩ ችግሮች፣ አለመረጋጋት፣ ፍቺ፣ ጭቅጭቅና ንትርክ ከሕፃንነት ጊዜ ጀምሮ ተፈላጊውን እእንክብካቤ ያለማድረግ፣ ልዩ ሆኖ ማደግ ፣አካላዊ ቅጣቶች፣ በትምህርት ቤት የሚከሰቱ ተፅዕኖዎች፣ ተማሪውን ያለመረዳት፣ ከምክር ይልቅ ቅጣትን ማስቀደም ሞራልን የሚነኩ ስድቦችን መሳደብ ወዘተ. ናቸው፡፡

**መ/ የባህሪ ችግሮችን ለመፍታት የምናደርጋቸው ወይም የምንሰጣቸውእእገዛዎች**

- ተማሪዎችን ለይቶ ማወቅና በተቻለ መጠን ከማራቅ ይልቅ ማቅረብ፣ ከማንቋሸሽ/ ከመሳደብ ይልቅ መምከር፣
- ከወላጆች ጋር ግንኙነት በመፍጠር መከታተልና መምከር፣
- በባለ ሙያ የታገዘ ምክር የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ተከታታይነት ያለውን ምክር እንዲያገኙ ማድረግና መከታተል፣
- አሉታዊ የሆኑ ባህሪያትን በአዎንታዊ ባህሪያት እንዲተኩ አእምሮአቸውን መቀየር የሚችሉ ነገሮች እእንዲያዩ ማድረግ፣
- ራሳቸውን እንዲቆጣጠሩ ማድረግና ተፈላጊ ያልሆኑ ባህሪያቸኝ እንዲተው ንቁና አምራች ዜጎች እ እንዲሆኑ ሁልጊዜ ራሳቸው ለጠቃሚ ሥራ ላይ ትኩረትእ እንዲሰጡ በተቻለ መጠን ማበረታታትና መደገፍ፣
- ተፈላጊ የሆኑ ባህሪያትን ሊያመጡ የሚችሉ የክፍል ውስጥ ደንቦችን ማውጣትና እእንዲተገበሩ ማድረግ፣
- ጥሩ ባህሪያትን ባሳዩ ቁጥር መሸለምና ማበረታታት፣
- ራሳቸውን በራሳቸው እእንዲቆጣጠሩ ማስተማር ወዘተ... ናቸው፡፡

መልመጃ ሰባት

1. የባህሪ ችግር ማለት ምን ማለት ነው? አብራሩ።

2. የባህሪ ችግሮች መንስኤዎች ምንድን ናቸው?

3. የባህሪ ችገሮችን ለመፍታት የምንሰጣቸውእእገዛዎች ምንድንናቸው?

### 2.2.7 የመማር ችግር (Learning Deficiency) ያለባቸው ሕፃናት

#### ሀ/ የመማር ችግር ትርጉምና ምንነት

የመማር ችግር (Learning Deficiency) ያለባቸው ሕፃናትና ወጣቶች የሚባሉት የሚማሩትን ትምህርት ቶሎ ወይም ፈጥነው የማይረዱ፣ ከጓደኞቻቸው ጋር እኩል ሊሄዱ የማይችሉ፣ በውጤታቸው ከአማካይ በታች የሆኑ፣ አንድን ነገር ከሌላው ለይተው ለማወቅ ችግር ያለባቸው፣ ሲጠየቁ| ለመመለስ የሚፈሩ፣ ወይም የማይችሉ ወዘተ... ሁኔታዎች ያሉባቸው ናቸው::

#### ለ/ የመማር ችግሮች መንስዔዎች

**<u>የተማሪው የግል ሁኔታዎች</u>**

- ያለመዘጋጀት፣ ፍላጎት ማጣት፣ ደንታ ቢስ መሆን፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ለምን ወደ ት/ቤት እንደመጣ አለማወቅ፣ አለማሰብ፣
- ሌሎች ግልጽ ያልሆነና እበውስጡ የታመቁ ውስጣዊ የሆኑ የሥነ ልቦና ችግሮች፣

**<u>የአድሜ እኩዮቻቸው ተጽዕኖ</u>**

- የእድሜ እእኩዮቹ አመለካከት በጎ ያለመሆን( መናቅ፣ ማግለል፣ አለማቅረብ፣)
- አለመተባበር፣ መሳደብ፣ ማንቋሸሽ፣
- የትምህርት ቤቱ /የመምህራን ሁኔታ
- ተማሪውን ከማበረ□□ት ይልቅ መሳደብና ማንቋሸሽ (ለምሳሌ ደደብ□ አህያ ሰነፍ □□ □□□□)
- ክትትል ያለማድረግ፣ችግሩን ያለመረዳት፣አካላዊ ቅጣትንመጠቀም፣ ከክፍል ማስወጣት፣ ከወላጆቹ ጋር ግንኙነት አለማድረግ፣
- ለብቻቸው እ□ንዲቀመጡ ማድረግ፣ ድጋፍ ያለማድረግ፣

**<u>የቤተሰብ ሁኔታዎች</u>**

- ክትትል ያለማድረግ፣ የሚያስፈልጋቸውን አለማሟላት፣መስደብ፣ማንቋሸሽ፣ ፍላጎታቸውን ለይተው አለማወቅ፣
- ፊቺ፣ መጣላት፣ የቤተሰብ ብዛት፣ የቤተሰብ መለያየት፣

<u>ወቅታዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎች</u>

በየጊዜው በዓለም አቀፍ፣ በአህጉርና በሀገር አቀፍ እንዲሁም በትንሽ አካባቢ ደረጃዎች የሚከሰቱ ወቅታዊ ሁኔታዎች፣በሚዲያ የሚተላለፉ ፊልሞች፣ በኢንቴርነት የሚለቀቁ የሕፃናትንና የወጣቶችን አመለካከትና አስተሳሰብ የሚሠርቁ አሉታዊ የሆኑ ተጽዕኖዎች፣ በመማር ሂደት ላይ ያልተፈለጉ ተፅዕኖዎች ስለሚያሳድሩ በሕፃናት ላይ የመማር ችግሮችን ያስከትላሉ፡፡

**ሐ/ የመማር ችግር ላለባቸው ህፃናት የሚደረጉ እእገዛዎች**

- ችግሮችን ለይተው ማወቅ፣ ከወላጆች ጋር ግንኙነት መፍጠርና እእንዲያበረታቷቸው ማድረግ ፣ሂደቱንም መከታተል፣
- ፍቅር ማሳየት፣ አለመለየት፣ እንዲሠሩ ሁልጊዜ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ማበረታታት፣
- አለመሳደብ፣ አለመምታት፣ እንዲያጠኑ መገፋፋት፣
- የተለያዩ የጥናት ስልቶችን ማሳየት፣
- ለሚያደርጉትን ስራ ወይም እንቅስቃሴ ማድነቅ፣
- ከጓደኞቻቸው ጋር አብረው እንዲሠሩ መምከርና ጓደኞቻቸውም እእንዲያቀርቡዋቸው ማድረግ፣
- ያለማቋረጥ መምከርና መከታተል፣፣
- ወደባለሙያ በመላክ አሰፈላጊውን የአመራርና የምክክር አገልግሎት እእንዲያገኙ ማድረግ ፣ውጤቱንም መከታተል ወዘተ ናቸው፡፡

## መልመጃ ስምንት

1. የመማር ችግር ማለት ምን ማለት ነው?

2. የመማር ችግሮች መንስዔዎችን ዘርዝሩ፡፡

### 2.2.8 የአካባቢያዊና ባህላዊ ተፅዕኖ ያለባቸው ሕፃናት

#### ሀ/ የአካባቢያዊና ባህላዊ ተፅዕኖ ያለባቸው ሕፃናት ምንነትና ትርጉም

እነዚህም ህጻናት በድህንት ሕይወት ውስጥ የሚኖሩ፣ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች/አሳዳጊዎች ጋር አብረው የሚኖሩ፣ ከአንድ ወላጅ ጋር የሚኖሩ ወይም ሁለቱንም ያጡ፣ ወዘተ ሲሆኑ ድጋፍና ፍቅር ያጡ፣ የጎዳና ተዳዳሪዎች፣ በሰው ቤት በሠራተኝነት የሚኖሩ ህጻናትም በዚህ ምደባ ሊጠቃለሉ ይችላሉ። እነዚህ ህጻናት ት/ቤት ሲገቡም አስፈላጊው ሁሉ ያልተሞላላቸው ናቸው:: ህጻናቱ ትኩረትና ድጋፍ ካልተደረገላቸው በትምህርታቸውም ዝቅተኛ ውጤት የሚያመጡ ወይም የሚያቋርጡና የሚወድቁ ይሆናሉ።

የአካባቢያዊና ባህላዊ ተፅዕኖ ያለባቸው ሕፃናትና ወጣቶች የሚባሉት ዝቅተኛ ከሚባሉ ጎሳዎች/ብሔረሰቦች አካባቢ የሚመጡ ሲሆኑ በዚህም የተነሳ እበትምህርትቤት ውስጥ በመምህራኖቻቸው የማይፈለግ አመለካከትና ተፅዕኖ ይደርስባቸዋል:: ይህም አመለካከት በተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ላይ ጎጅ የሆነ ሚና ይኖረዋል። በአጠቃላይ ሕብረተሰቡ፣ ባህሉና አካባቢው በሕፃናትና ወጣቶች በተለይም በሴቶች ላይ አዎንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራሉ። ይህ ተጽዕኖም በትምህርት አቀባበልም ላይ እንደሚንጸባርቅ መገመት አያዳግትም።:

ከላይ የተጠቀሱት ተፅዕኖዎች ከሚስተዋልባቸው አካባቢዎች የሚመጡ ሕፃናት ፍላጎታቸው ስለማይሟላ እ በትምህርት ቤት ቆይታቸው ደስተኞች አይሆኑም፣ ብዙውን ጊዜም አጥፊዎች ይሆናሉ:: እነዚህ ህጻናት ዝምተኞች ናቸው:: ከሌሎች የዕድሜ ዕኩዮቻቸው ጋር መገናኘትና መግባባት አይፈልጉም:: በእነዚህም ምክንያቶች ከፍተኛ ችግር ይገጥማቸዋል::

**ለ/የአካባቢያዊና ባህላዊ ተፅዕኖ ያለባቸው ሕፃናት ማንነት**

**<u>ለተለያዩ ብዝባዛዎች የተጋለጡና የተናቁ ሕጻናት (Abused and neglected children)</u>**

በአካባቢያዊና ባህላዊ ተፅዕኖ ስር ያሉ ሕፃናትና ወጣቶች ለተለያዩ ብዝባዛዎች የተጋለጡና የተናቁ ናቸው:: እነዚህ ህጻናት ለጉልበት ብዝበዛ፣ለግብረ ሥጋዊ ግንኙነት ብዝባዛና ጥቃት የተጋለጡና የተናቁ ናቸው:: በዚህም ምክንያት በማህበራዊ ሕይወታቸውና በሥነ ልቦናቸው የተጎዱና በአብዛኛውም የትምህርት ዕድል የተነፈጉ ዜጎች ናቸው:: እነዚህ

ሕፃናት በእነዚህና በሌሎች ምክንያቶች ስሜታቸው፣አካላቸው፣ አእምሮአቸውና ማሕበራዊ ሕይወቻቸው የተጎሳቀ ቆለናየተጎዳ ነው።:

**<u>ቤተ-አልባ ወይም መኖሪያ ሥፍራ የሌላቸው ሕፃናት (Home less children)</u>**

እነዚህ ህጻናትእመኖሪያ ሥፍራና ቤት በማጣት ማደሪያቸውን በመንገድ ዳር ባሉ የአውቶብስ ማቆሚያ ሥፍራዎችና በየበረንዳዎች ያደረጉ ሕፃናትና ወጣቶች ሲሆኑ ለተለያዩ ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ችግሮች የተጋለጡ፣ በልመና ሥራ የሚተዳደሩ፣ ከዚያም አልፈው ለሴብነት፣ ለኪስ አውላቂነትና ለሥርቆት ድርጊቶች የተጋለጡ ናቸው። ህጻናቱ የመማር ዕድል የተነፈጉ ዜጎች ናቸው:: እነዚህ ልጆች ትምህርት ቤት የመግባት ዕድል ቢገጥማቸው እንኳን በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ዘንድ የተናቁ፣ የተጠሉና የሚጠረጠሩ በመሆናቸው ልዩ ሥነ ልቦናዊና ማህበራዊ ድጋፍ የሚሹ ናቸው::

**<u>አልኮል የሚጠጡና አደንዛዥ ዕፅ የሚወስዱ ሕፃናት (Alcohol and substance abuse)</u>**

አልኮል የሚጠጡና ህገወጥ የሆኑ አደንዛዥ ዕፆችን የሚወስዱ ተማሪዎች በሕይወታቸው የተጎሳቀሉና በትምህርታቸው የሚወድቁ ከመሆናቸውም በላይ ደስተኞች ያልሆኑ፣ በስርቆት የተሰማሩና ሕገወጥ የሆኑ ሥራዎችን የሚሠሩ፣ በህብረተሰቡ ውስጥ የተጠሉ ናቸው:: እ እነዚህ ህጻናት ሕፃናትና ወጣቶች ጤናማና ምርታማ ዜጎች ሆነው እእንዲወጡ ልዩ ድጋፍና እ እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸውና ልዩ ፍላጎት ያሏቸው ናቸው:: ለእነዚህ ህጻናት የሚሰጠው ድጋፍ መጀመር ያለበት ከሕፃንነት ዕድሜ ወይንም ከመዋዕለ ሕፃናት ትምህርት ቤት ጊዜ ጀምሮ መሆን አለበት::

**<u>በድህነት ሥር ያሉ ሕፃናት (Children living with Poverty)</u>**

በድህነት ጥላ ሥር ያሉ ሕፃናት ህይወታቸው አስጊ ሁኔታ ላይ ያለ ከመሆኑም ባሻገር በትምህርታቸው ውጤት ዝቅተኛ ነው። የወላጆቻቸው ቁጥጥር፣ ክትትልና ድጋፍ አነስተኛ በመሆኑ ሁሌም ለተለያዩ አደጋዎች የተጋለጡና ጤንነታቸውም አስጊ በሆነ ሁኔታ ላይ ይገኛል።

**<u>በልጅነት /በወጣትነት እድሜአቸው ነፍሰጡርና የሆኑና የወለዱ ( Young, pregnant and parents)</u>**

እነዚህ ህጻናትና ወጣቶች ገና በአፍላ ወጣትነት ዕድሜ ማለትም ከሕፃንነት ዕድሜ ወደ ወጣትነት ዕድሜ በመሸጋገር ላይ የሚገኙ ሕፃን ወጣቶች ሲሆኑ ወጣቶቹ ላልተፈለገ ዕርግዝናና ለተለያዩ አደጋዎች ከመሆናቸውም በላይ በተምህርት ውጤታቸውም ዝቅተኛ ናቸው። እነዚሁ ሕፃናት በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ይገኛሉ:: ስለዚህ ልዩ ድጋፍና እእንክብካቤ የሚያፈልጋቸው ስለሆነ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናት ናቸው::

<u>**የራሳቸውን ሕይወት ለማጥፋትና ለወጣት አጥፊነት የተጋለጡ ሕፃናት (Warning signs for suicide/ violence)**</u>

**እነዚህ ህጻናትና ወጣቶች:-**

- ወላጆቻቸውን በሞት ያጡና በጓዳኞቻችው ተቀባይነት ያጡ፣
- በቂ የእንቅልፍ ዕጦት ያለባቸው፣ ባልታወቁ ምክንያቶች የሰውነታቸው ክብደት የሚቀንስ፣
- ያልታሰቡና ያልተጠበቁ ውጤቶችን በትምህርታቸው የሚያስመዝግቡ፣
- አፈጣጠራቸውንና ስብዕናቸውን እያዩ ሚጠሉ፣አደንዛዥ ዕፆችን የሚወስዱና አዛውትረው አልኮል መጠጦችን የሚጠጡ ናቸው::

## ሐ/ የአካባቢያዊና ባህላዊ ተፅዕኖ ላለባቸው ሕፃናት የሚደረጉ ትምህርታዊ፣ ሥነ ልቦናዊና ማኅበራዊ ድጋፎች

የአካባቢያዊና ባህላዊ ተፅዕኖ ያለባቸውን ሕፃናትና ወጣቶችለመደገፍ የወላጆች/አሳዳጊዎች፣ የህብረተሰቡና የመምህራን ተሳትፎ ወሳኝ ሚና አለው። ለእነዚህ ህጻናትና ወጣቶች መሰጠት ያለባቸው ድጋፎች እንደሚከተለው ተዘርዝረው ቀርበዋል።

- በተማሪዎች መካከል የባህል፣ የቋንቋና የሥነ ልቦና ልዩነቶች መኖራቸውን በመረዳት እንደሁኔውታው በማገናዘብ ማስተናገድና ከጓደኞቻቸውጋር ተከባብረውና ተደጋግፈው እንዲያድጉና እ እንዲማሩ ማመቻቸት፣ ይህ ልዩነታቸው ሀብታቸውና ውበታቸው መሆኑን ማሳወቅ፣

- ትምህርታዊ አገልግሎት ከማቅረብ በተጨማሪ ፍላጎታቸውን በነፃነት እ እንዲገልጹና እንዲያስረዱ በማድረግ ችሎታቸውንታእንዲጠቀሙበቂ የሆነ የምክክር አገልግሎት ያለማቋረጥ መስጠት፣
- እእክፍል ውስጥ ተማሪዎችእ ርስበርስ ተጋግዘው በቡድንእእንዲሠሩና ልምዳቸውን እእንዲያካፍሉ ማድረግና ማበረታታት፣
- በተማሪዎችና በመምህራን መካከል አዎንታዊ የሆነ ግንኙነት እ እንዲኖር ጥረት ማድረግና መከባበር፣ መምህራንም በተማሪዎች መካከል እየዞሩ ድጋፍ መስጠት፣
- የመማር ማስተማር ሂደቱ የተማሪዎቹን የእርስበርስ ግንኙነትንና ልማዳቸውን ያማከለ መሆኑን መገምገም፣
- የተማሪዎችን የኂላ ታሪክ ማወቅ፣ ስለተማሪው በቂ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ስለቤተሰቦቹ ማወቅ፣ ስለተለያዩ ህዝቦችታታሪክ ማጥናት፣ መናገርና ተማሪዎችም ስለ ባህላቸው፣ ስለራሳቸውና ስለቋንቋቸው ያለመሸማቀቅ ነጻ ሆነው እንዲናገሩ ማበረታታት፣
- ተከታታይ ምዘናዎችን መስጠት ውጤቱን በግልጽ ማሳየት፣
- በመምህራን ለተማሪዎቻቸው ሁልጊዜ በጎ አመለካከት እንዲኖራቸው ማድረግና ማንኛውንም መድሎና መገለል ማስወገድ ወዘተ ናቸው፡፡

## መልመጃ ዘጠኝ

1. የአካባቢያዊና ባህላዊ ተፅዕኖ ያለባቸው ሕፃናት እእነማን ናቸው?

______________________________
______________________________
______________________________
______________________________

2. በማሕበራዊ፣ በሥነ ልቦናቸውና ትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ የአካባቢያዊና ባህላዊ ተፅዕኖ ላለባቸው ሕፃናት ምን ዓይነት ድጋፍ ማድረግ እንችላለን?

______________________________
______________________________
______________________________
______________________________

## 2.2.9 ተደራራቢ የአካል ጉዳቶች ያለባቸው ህፃናት

ይህ ስያሜ የሚያመለክተው አንድ ሕፃን ከአንድ በላይ የሆኑ የአካል ጉዳቶች ሲኖሩት የሚታዩበትን ችግሮች ነው። ለምሳሌ የማየትና የመንቀሳቃስ ችግሮች፣ የጤናና የመንቀሳቀስ ችግሮች፣ የአእምሮእእድገት ዝግመት፣ የመናገር ችግር፣ የመስማትና የመናገር ችግር ወዘተ. በአንድነት በአንድ ሰው ላይ በአንድ ጊዜ ሊከሰቱ ይችላሉ:: እነዚህ ችግሮች በአንድ ላይ ሲከሰቱ ተደራራቢ የአካል ጉዳቶች ይባላሉ::

የአካላዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ ሲያቅታቸው የሚታዩ የእጅና የእግር መቆረጥና ወይም አለመሥራት፣ ለማየት፣ ለመስማት፣ ለመናገር ወዘተ. ያለመቻል ችግሮች በአካላዊ መጓደል ውስጥ የሚካተቱ ናቸው:: ሕፃናትን ለተደራራቢ የአካል ጉዳተኝነት የሚዳርጉ ዋና ዋና የመንቀሳቀስና የጤና ችግሮች የሚባሉት:-

- ☞ የልጅነት ልምሻ/ ፖሊዮ ( Polio)
- ☞ ፓራላይዝድ መሆን (Paralysis)
- ☞ የአካል መንቀጥቀጥ ይግም አንቅስቃሴ የሚቆጣጠር የአንጎል ክፍል መጎዳት (Cerebral Palsy)
- ☞ የእጅና የእግር ማጣት መቆረጥና አንዳንድ የሰውነት ክፍሎች ያለመፈጠር (Orthopedic Neurological Impairment)
- ☞ የእግር መርገጫ መታጠፍ (Club foot)
- ☞ የሥጋ ደዌ በሽታ መከሰት(leprosy)
- ☞ የልብ ድካም (Heart Fauliraity)
- ☞ የአስም በሽታ (Asthma)
- ☞ የሚጥል በሽታ (Epilepsy)
- ☞ የስኳር በሽታ(Diabetes)
- ☞ ሔሞፊሊያ (Hemophilia)
- ☞ የአጥንት መገጣጠሚያዎች ጉዳት (Spinal Cord Injuries) ወዘተ. ናቸው::

**የተደራራቢ አካል ጉዳቶች መንስዔዎች**

ከላይ ለተለያዩ የአካል ጉዳቶች መንስዔዎች ናቸው ተብለው የተዘረዘሩት ለተደራራቢ የአካል ጉዳቶችም መንስዔዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ሌሎች ተፈጥሮአዎና አካባቢያዊ የሆኑ ሁኔታዎችና ክስተቶች ለአካል ጉዳተኝነት ዋና መንስዔዎች ይሆናሉ።

**የተደራራቢ አካል ጉዳቶች ያለባቸውን ሕፃናትን መለየት ማሰስና እገዛዎችን መስጠት**

ከላይ የተለያዩ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ሕፃናትን ለመለየት፣ ለማሰስና አስፈላጊ የሆኑ ትምህርታዊና ማኅበራዊ እገዛዎች ማድረግን በሚመለከት የተዘረዘሩት ሁሉ ተደራራቢ የአካል ጉዳት ላለባቸው የሚተገበሩ ናቸው።

**መልመጃ አሥር**

1. ተደራራቢ የአካል ጉዳት ዓይነቶችን ከመንስዔዎቻቸው ጋር በማገናዘብ ከጓደኞቻችሁ ጋር እከተወያያችሁ በኋላ መለሳችሁን ጻፉ።


ESD

## 2.3 ልዩ ተሰጥኦ ችሎታ ያላቸው ህፃናት

### ሀ/ ልዩ ተሰጥኦና ችሎታ ያላቸው ትርጉምና ምንነት

እነዚህ ህጻናት በሂሳብ፣ በቋንቋ፣ በአርት፣ በሙዚቃ፣ በፈጠራ ሥ^ና በመሳሰሉት ዘርፎች ከፍተኛ ችሎታ ያላቸውንና ችሎታቸውን በተግባር የሚያሳዩትን ያጠቃልላል። እነዚህ ህጻናት ከዕድሜ እኩዮቻቸው ጋር ሲወዳደሩ ከተጠበቀው በላይ የሚሰሩ፣ የአእምሮ ችሎታቸው ከፍተኛ የሆነና፣ የሚሰጣቸውን ሥራ ፈጥነው የሚሠሩ፣ ችግሮችን በቀላሉ የሚፈቱ፣ የመፈላሰፍ ችሎታ ያላቸው፣ አርቆ አሳቢዎች ሆነው እናገኛቸዋለን። እነዚህ ህጻናትና ወጣቶች አንዳንድ ጊዜ በጣም የተለዩ/የላቁ (exceptional children) ይባላሉ:: ለምሳሌ ከትላልቅ/ታዋቂ ሰዎችና ፈላስፋዎች መካከል እንደእቻሪልስ ዳርዊን፣ አልበርት አንስታይን፣ ስግሙንድ ፍሩድ አይሳክኒውቶን፣ የመሳሰሉት በልዩ ችሎታቸውና ተሰጥኦአቸው በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው::

### ለ/ ልዩ ተሰጥኦና ችሎታ ያላቸው ሕጻናት የሚያሳዩአቸው ባህሪያት

- በአእምሮአዊ ስራቸው (Cognitive task) ፈጥነው የሚያውቁ ናቸው። በቋንቋቸው፣ በንባብ ችሎታቸው፣ በአርትማቲክ፣ ምክንያታዊ በሆነ መንገድ በማገናዘብ ወዘተ ፈጣን ናቸው::
- በትምህርት ተግባር (Academic task):- በትምህርት ክትትላቸው ከፍተኛ ውጤት የሚያስመዘግቡ ሲሆን ከጓደኞቻቸው ጋር ሲወዳደሩ በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ከፍተኛ ውጤት የሚያስመዘግቡ ናቸው::
- በጉልበት ስራዎች (Physical tasks) ከጓደኞቻቸው ጋር ሲወዳደሩ ልዩ በሆነ መንገድ በፍጥነትና በጥራት የሚያከናውኑ ናቸው::
- በባህሪያቸው (Behavioral task):- ልዩ የመግባባት ችሎታ፣ በፍጥነት የመረዳት ችሎታ፣ ያላቸው ሲሆኑ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ፈጣን የሆኑ፣ በተግባርም ተደማጭነት ያላቸው ናቸው። እነዚህ ህጻናት ማኀበራዊና ግላዊ ፍላጎትን በማሟላት ለየት ያሉ ናቸው::
- በመገናኛ (Communication) በቀላሉ ከሌሎች ጋር ግንኙነት የማድረግ ችሎታ አላቸው። ህጻናቱ በፍጥነት የሚረዱና የሚግባቡ ናቸው።: ጀምስ ዲንለሮፐ

የሚከተሉትን በጎና ገንቢ የሆኑ የልዩ ተሰጥኦና ችሎታ ያላቸው ህፃናት /ወጣቶች ባህርያትን ገልጿል፡፡

**<u>በጎ/ጥሩ ባህሪያት</u>**

- በቀላሉ ፈጥነው ይማራሉ፣
- የተማሩትን በቀላሉ ያስታውሳሉ፣
- ለመረዳት ሲሉ አጥብቀው ይጠይቃሉ፣
- በንግግር ችሎታቸው የላቁ ናቸው፣
- በማንበብ ይደሰታሉ፣
- ቃላቶችንና ሀሳቦችን በማመንጨት በጣም ታታዋቂና ደስተኞች ናቸው፣
- ለነገሮች ፈጥነው ምክንያቶችን ያውቃሉ፣ ያመነጫሉ፣ መፍትሔም ያሰቀምጣሉ፣
- ሀሳቦችን ለማጠቃለል ከፍተኛ ችሎታ አላቸው፣
- ነገሮችን አማካይ ችሎታ ካላቸው ልጆች ፈጥነው ያውቃሉ፣
- ታላላቆቻቸውን ለመረዳትና ለማወቅ ፈጣንና ደስተኞችም ናቸው፣
- ነገሮችን ቶሎ ለማወቅና ለመመራመር ከፍተኛ ደስታ ያላቸው ሲሆን ፈጣንም ናቸው፡፡

**<u>አሉታዊ/የማይፈለጉ ባህሪያት</u>**

- እረፍት ወይም የተረጋጋ መንፈስ የላቸውም፣
- ረባሾችና ትኩረት የሚያንሳቸው ናቸው፣
- በእጅ ጽሁፋቸው ግድ የለሾች ናቸው፣
- በክፍል ስራቸው ለየት ያሉና በንግግራቸው ፈጣንና ትክክለኛ የሆኑ ናቸው፣

*ሐ/ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ህጻናትና ወጣቶች ማሰስና መለየት*

**ወላጆችና መምህራን ልዩ ተሰጥኦ/ችሎታ ያላቸውን ልጆችን እእንዴት መለየት ይችላሉ?**

- በቋንቋቸው፣ በሚያፈልቁት ሀሳብ አካባቢያቸው በመቃኘት ፈጣን ሆነው ሲገኙ፣ የተጻፈ ነገሮችን ለማንበብ ሲሞክሩ ወይም ሲወዱ፣ የተለያዩ ታሪኮችን ለመናገር ጥረት ሲደርጉ ወይም ሲናገሩ፣ ልዩ የሥዕል ችሎታ ሲኖራቸው፣ በሙዚቃ ሥራቸው ያዩትን ሲረዱና ሲመራመሩ እንዲሁም የመሳሰሉትን መገለጫዎች ሲያሳዩ እነዚህ ህጻናትና ወጣቶች ልዩ ተሰጥኦ/ችሎታ ያላቸው መሆኑን ለመለየት ያስችላል። በተጨማሪም መምህራን፣ የትምህርት ሳምንቶችን የስነ ልቦና ባለሙያዎችንና የተለያዩ ሳይንሳዊ የሆኑ ዘዴዎችን ተጠቅመው ልዩ ተሰጥኦ/ችሎታታ ያላቸውን ሕፃናትና ወጣቶች መለየት ይችላሉ::

**የሚከተሉት ዘዴዎችን መጠቀም ይቻላል።**

- ሀ/ በቡድን የችሎታ መለኪያ ቴስቶችን በመስጠትና በዚህ ውጤት ተንተርሰው የግል የችሎታ ታ መለኪያ ቴስቶችን መስጥት፣
- ለ/ አንድ ወጥ የችሎታ መለኪያ ቴስቶችን በመስጠት (A standardized achievement test)
    - በትምህርት ቤት በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች የሚያስመዘግቧቸው ጠቅላላ ውጤቶችን በማየት፣
    - መምህሩ በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ ተማሪው የሚያደርገውን ቅኝት በማድረግ የሚታዩ የተማሪውን ችሎታ ማየት፣

**መ/ ልዩ ተሰጥኦ/ችሎታ ያላቸው ተማሪዎችን ለመዳሰስ የሚረዱ መመሪያዎች/ዘዴዎች**

- **ማሳደግ/ማበረታት፡-** መምህሩ ልምዱን ወይንም ከስርዓተ ትምህርቱ ላይ ካለው በተጨማሪ እእያሠራ ቢያበረታታ ተማሪውን የበለጠ እ እንዲመራመርና እእንዲያውቅ ያደርገዋል፣ ችሎታውን ያጠነክራል፣ ከክፍል ጓደኞቹ በተሻለ ሁኔታ እንዲንቀሳቀስ ይመክራል፣ አቅጣጫውን ያሳያል::
- **ሁኔታዎችን ማመቻቸት/ማፋጠን፡-** የተማሪው እ እድገት የሚዳበርበትን ሁኔታኔታ ማመቻቸትን የሚመለከት ሲሆን ለምሳሌ በአንድ ዓመት ሁለት ክፍል እንዲማር

ማድረግ፣ አንድ ክፍል እእንዲዘል ማድረግ ወደ ከፍተኛ ትምህርት እእንዲገባ አቅጣጫ ማሳየት መረጃ መስጠት ይቻላል።

**መልመጃ አሥራ አንድ**

1. ልዩ ተሰጥኦና ችሎታታ ያላቸው ሕፃናት የሚባሉት የትኞቹ ናቸው?

2. ልዩ ተሰጥኦ/ችሎታ ያላቸው ተማሪዎችን ለመዳሰስ የሚረዱ መመሪያዎች/ዘዴዎች ምንድን ናቸው?

**ከመልመጃ አንድ እእስከ መልመጃ አሥር ለተሠጡት ጥያቄዎች የተቀመጡ መልሶች (Keys)**

**መልመጃ አንድ**

**ክፍል አንድ:**

1. ውሸት
2. ውሸት
3. እውነት
4. ውሸት
5. እውነት

**ክፍል ሁለት**

6. ረ
7. ሐ
8. ሠ
9. ሀ
10. ለ

**ክፍል ሦስት**

11. ሀ
12. መ
13. ሐ

**መልመጃ ሁለት**

**ክፍል አንድ:**

1. ውሸት
2. እውነት
3. ውሸት
4. እውነት
5. ውሸት
6. እውነት

**ክፍል ሁለት**

7. መ
8. ሀ
9. መ
10. መ
11. ሐ
12. መ
13. መ
14. ሐ

**መልመጃ ሦስት**

1. ውሸት
2. እውነት
3. ውሸት
4. ውሸት
5. እውነት
6. ውሸት
7. እውነት
8. እውነት
9. ውሸት
10. እውነት

**መልመጃ አራት**

1. ረ    2. መ    3. ሀ    4. ለ    5. ሐ

**መልመጃ አምስት**

1. መ    4. ሐ    7. ሠ    10. ቀ
2. ሸ    5. ሰ    8. ተ
3. ሀ    6. ለ    9. ረ

**መልመጃ ስድስት**

1. ሀ. በራሱ ደስተኛ ሳይሆን ሲቀር

   ለ. በሚያስተላልፈው ድምፅ መልዕክት ላይ ስህተት ሲኖረው

   ሐ. በማህበራዊ ግንኙነት ተጠቃሚ ለመሆን ሳይችል ሲቀር

   መ. የመማር ዕድል ሳያገኝ ሲቀር

2. ሀ. የአእምሮ እእድገት ውስንነት ችግር

   ለ. አካባቢያዊ ተጽእኖዎች

   ሐ. የመስማት ችግሮች

   መ. የስሜቶች መረበሸና የባህርይ ችግሮች
   ሠ. የሰውነት የንግግር ክፍሎች በትክክለኛ ቦታታ አለመሆን... ወዘተ ናቸው፡፡

**መልመጃ ሰባት**

1. የባህሪ ችግር ላለባቸው ህፃናትና ወጣቶች አንድ ወጥ የሆነ ትርጉም ለመስጠት ባይቻልም አንዳንድ ምሁራኖች እእንደገለጹት የባህሪ ችግር ያለባቸው ተማሪዎች:

   - ስሜታቸው የተረበሸ፤ ለመማር የማይፈልጉ፣ ከዕድሜ እኩያዎቻቸው ጋር በፀባይ፣ በሥራ መግባባት የማይችሉና የማይፈለጉና ባህሪያትን የሚያሳዩ፣ ደስተኛ ያልሆኑ፣ በአቋማቸው ፈሪ የሆኑ ወይም ደንብና ህግን የሚጥሱ፣ አደርጉ የተባሉትን ለማድረግ የማይሞክሩ፣ የማይታዘዙ፣ ንብረት ማበላላሸትንና ማውደምን የሚወዱ፣ የሚረብሹና የሚያውኩ... ወዘተ ናቸው፡፡

2. ለባህሪ ችግሮች መንስዔዎቹ፡-

- እእንደሌሎች የአካል ጉዳቶች የባሪ ችግሮች መንስዔዎች ሊከሰቱ የሚችት ከወሊድ በፊት፣ በወሊድ ጊዜና ከወሊድ በኋላ በሚከሰቱ የተለያዩ ክስተቶች ነው፡፡ ለምሳሌ ከወሊድ በፊት በእርግዝና ጊዜ በእናቲቱ ላይ የሚከሰቱ ሁኔታዎች /በቂ ምግብ ያለማግኘት፣ አልኮልና ዕፅችን መውሰድ፣ ለነፍሰጡር እናቶች የሚሰጡ ክትባቶቸን ያለመውሰድ፣ ያለሐኪም ትእዛዝ የማይፈቀድ መድሀኒቶችን መውሰድ ወዘተ ናቸው፡፡

- በአካባቢያዊ በግላዊ ሁኔታዎች፡- የሚኖሩበት አካባቢ ተፅዕኖ፣ የኀብረሰቡ የአኗኗር ሁኔታዎች፣ የእድሜ እ እኩዮቹ ተጽዕኖ ወቅታዊ ነባራዊ ሁኔታዎች /የሚዲያ ተፅዕኖ/፣ ከባህል የሚወረሱ ባህሪያት ወዘተ. ናቸው፡፡

- ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች፡- በቤትና በትምህርት ቤት አካባቢ በሚከሰቱ ተጽእኖዎች ለምሳሌ በልጅና በቤተሰብ መካከል በሚፈጠሩ አለመግባባቶች፣በወላጆች መካከል በሚፈጠሩ ችግሮች፣ፍቺ፣አለመረጋጋት፣ጭቅጭቅና ንትርክ፣ ከህጻንነት ጊዜ ጀምሮ ተገቢውን እንክብካቤ አለማድረግ፣ ልዩ ሆኖ ማደግ፣ አካላዊ ቅጣት፣በትምህርትቤት የሚፈጸሙ ተጽዕኖዎች፣ተማሪውን ያለመረዳት፣ከመምከር ይልቅ ቅጣትን ማስቀደም፣ ሞራልን የሚነኩ ስድቦችን መሳደብ ናቸው።

3. የባህርይ ችግሮችን ለመፍታት የምናደርጋቸው ወይም የምንሠጣቸው እእገዛዎች፡-

- ተማሪዎችን ለይተው ማወቅና በተቻለ መጠን ከማራቅ ማቅረብ፣ ከማንቋሸሽ/ከመሳደብ ይልቅ መምከር፣
- ከወላጆች ጋር ግንኙነት መፍጠር መከታተልና መምከር፣
- በባለሙያ የታገዘ ምክር የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣መልዕክት ያለውን ምክር እእንዲያገኙ ማድረግና መከታተል፣
- አሉታዊ የሆኑ ባህሪያትን በአዎንዊ/በጎ በሆኑ ባህሪያት እእንዲተኩ አእምሮአቸውን መቀየር የሚችሉ ነገሮች እእንዲያዩ ማድረግ፣

- ራሳቸውን እንዲቆጣጠሩ ማድረግና ተፈላጊ ያልሆኑ ባህሪያትንእ እንዲተው እንቁና አምራች ዜጎች እእንዲሆኑ ሁልጊዜ ራሳቸው ለጠቃሚ ሥራ ላይ ትኩረት እንዲሰጡ በተቻለ መጠን ማድረግ፣
- ተፈላጊ የሆኑ ባህሪያትን ሊያመጡ የሚችሉ የክፍል ውስጥ ደንቦችን ማውጣትና እንዲተገበሩ ማድረግ፣
- ጥሩ ባህሪያትን ባሳዩ ቁጥር መሸለምና ማበረታታት፣
- ራሳቸውን በራሳቸው እእንዲቆጣጠሩ ማስተማር ወዘተ... ናቸው፡፡

<u>**መልመጃ ስምንት**</u>

1. የመማር ችግር ማለት አንድ ሕፃን የሚማረውን ትምህርት ቶሎ ወይም ፈጥኖ የማይረዳ፣ ከጓደኞቹ ጋር እእኩል ሊሄድ የማይችል፣ በውጤቱ ከአማካይ በታች የሆነ፣ አንድን ነገር ከሌላው ለይቶ ለማወቅ ችግር ያለበት፣ ሲጠይቅ ለመመለስ የሚፈራ ወይም የማይችል ወዘተ... ያለበት ማለት ነው፡፡

2. የመማር ችግሮች መንስዔዎች
   - ያለመዘጋጀት፣ ፍላጎት ማጣት፣ ደንታታቢስ መሆን፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ለምን ወደ ት/ቤት እእንደመጣ አለማወቅ፣ አለማሰብ፣
   - ለሌሎች ግልጽ ያልሆኑ እውስጡ የታመቁ ውስጣዊ የሆኑ የሥነ ልቦና ችግሮች፣
   - የእድሜ እእኩዮቹን አመለካከት መናቅ፣ ማግለል፣ አለማቅረብ፣
   - አለመተባበር፣ መሳደብ፣ ማንቋሸሽ፣
   - ተማሪውን ከማበረታታት ይልቅ መሳደብና ማንቋሸሽ (ለምሳሌ ደደብ አህያ ሰነፍ ወዘተ ብሎ መሳደብ)
   - ክትትል ያለማድረግ፣ ችግሩን ያለመረዳት፣ አካላዊ ቅጣትን መጠቀም፣ ከክፍል ማስወጣት፣ ከወላጆቹ ጋር ግንኙነት አለማድረግ፣
   - ለብቻቸው እንዲቀመጡ ማድረግ፣ ድጋፍ ያለማድረግ፣

- ክትትል ያለማድረግ፣ የሚያስፈልጋቸውን አለማሟላት፣ መስደብ፣ ማንቋሸሽ ፣ፍላጎታቸውን ለይተው አለማወቅ፣
- ፍቺ፣ መጣላት፣ የቤተሰብ ብዛት፣ የቤተሰብ መለያየት፣
- በየጊዜው በዓለም አቀፍ፣ በአህጉርና በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚከሰቱ ወቅታዊ ሁኔታዎችና በአካባቢዎች የሚከሰቱ ሁኔታዎች፣ በሚዲያ የሚተላለፉ ፊልሞች፣ በኢንቴርነት የሚለቀቁ የሕፃናትንና የወጣቶቸን አመለካከትና አስተሳሰብ የሚሠርቁ አሉታዊ የሆኑ ተጽዕኖዎች፣ በመማር ሂደት ላይ ያልተፈለገ አቅጣጫዎች/አመለካከቶች ስለሚያሳድሩ በሕፃናት መማር ላይ ችግሮችን ያስከትላሉ፡፡

<u>**መልመጃ ዘጠኝ**</u>

1. የአካባቢያዊና ባህላዊ ተፅዕኖ ያለባቸው ሕፃናት የሚባሉት በድህንት ሕይወት ውስጥ የሚኖሩ፣ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች/አሳዲጊዎች ጋር አብረው የሚኖሩ፣ ከአንድ ወላጅ ጋር የሚኖሩ ወይም ሁለቱንም ያጡ፣ ወዘተ ሲሆኑ ድጋፍና ፍቅር ያጡ፣ የጎዳና ተዳዳሪዎች፣ በሰው ቤት በሠራተኝነት የሚኖሩ በዚህ መድብ የሚጠቃለሉ ናቸው። እነዚህ ልጆች ት/ቤት ሲገቡም አስፈላጊው ሁሉ ያልተሞላላቸው፣ትኩረትና ድጋፍ የማይደረግላቸው ናቸው። በመሆኑም በትምህርታቸው ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘግባሉ፣ ወይም ደግሞ ያቋርጣሉ ካለሆነም ክፍል ይደግማሉ። ህጻናቱ ዝቅተኛ ከሚባሉ ጎሳዎች/ብሔረሰቦች አካባቢ የሚመጡ ሊሆኑ ስለሚችሉ እበትምህርት ቤት ውስጥ በመምህራኖቻቸው በጎ ያልሆነ አመለካከትና ተፅዕኖ የሚደርስባቸው ናቸው ማለት ነው፡፡

2. በማሕበራዊ፣ በሥነ ልቦናቸውና ትምህታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ የአካባቢያዊና ባህላዊ ተፅዕኖ ላለባቸው ሕፃናት መደረግ ያለባቸው ድጋፎችና እገዛዎች፡-
   - በተማሪዎች መካከል የባህል፣ የቋንቋና የሥነ ልቦና ልዩነቶች መኖራቸውን በመረዳት እንደየሁኔታው ማስተናገድና ከጓደኞቻቸው ጋር ተከባብረውና ተደጋግፈው እንዲያድጉና እ እንዲማሩ ማድረግ፡፡ በመካከላቸው ያለው ልዩነት ሀብታቸውና ውበታቸው መሆኑን ማስተማር እና እንዲያከብሩት ማበረታታት፣

- መደበኛ የትምህርት አገልግሎት ከመስጠቱ ጎን ለጎን ፍላጎታቸውን በነፃነት እእንዲገልጹና እ እንዲያስረዱ በማድረግ ችሎታቸውን እንዲጠቀሙ በቂ የሆነ የምክክር አገልግሎት ያለማቋረጥ መስጠት፣
- እበክፍል ውስጥ ተማሪዎች እእርስበርስ ተጋግዘው በቡድንእእንዲሠሩና ልምዳቸውን እእንዲያካፍሉ ማድረግና ማበረታታት፣
- በተማሪዎችና መምህራን መካከል በጎና ጥሩ የስራና የሙያ እንዲኖር ጥረት ማድረግና መከባበር፣ መምህሩም በተማሪዎች መካከል በመዘዋወር ድጋፍ እየሰጡ ልጆቹ እንዲረዳዱ ማድረግ፣
- የመማር ማስተማር ሂደቱ የተማሪዎቹን የእርስበርስ ግንኙነትንና ልማዳቸውን ያማከለ መሆኑን መገምገም፣
- የተማሪዎችን የኋላ ታታሪክ ማወቅ፣ ስለተማሪው በቂ መረጃዎችን በመሰብሰብ ስለቤተሰቦቹ ግልጽ ግንዛቤ መያዝ፣ ስለተለያዩ ህዝቦች ታሪክ ማጥናት፣ መናገርና ተማሪዎችም ስለ ባህላቸው ስለራሳቸውና ስለቋንቋቸው ያለመሸማቀቅ ነፃ ሆነው እእንዲናገሩ ማበረታታ፣ና
- ተከታታታይ ምዘናዎችን መስጠትና ውጤቱን በግልጽ ማሳየት፣
- መምህራን ለተማሪዎቻቸው ሁልጊዜ በጎ አመለካከት እንዲኖራቸው ማድረግና ማንኛ ውንም መድሎና መገለል ማስወገድ ወዘተ ናቸው፡፡

<u>**መልመጃ አሥር**</u>

1. ተደራራቢ አካል ጉዳቶች የሚባሉት የማየት፣ የመንቀሳቃስ፣ የአእምሮ ውስንነት፣ የመናገር ወዘተ ችግሮች በአንድነት በአንድ ሰው በአንድ ጊዜ ሲከሰቱ ማለት ነው፡፡ ተደራራቢ አካል ጉዳቶች መንሰዔዎችም ሊሆኑ የሚችሉት፡ ለሌሎች የአካል ጉዳቶች በተናጠል የተዘረዘሩት መንስዔዎች ናቸው፡፡

## የዋቤ መጽሐፍት (References)


1. ዓለሙ አበራ (1995)፡ ሕይወት በየነ (1998)፤ የልዩ ትምህርት በ10+1 ደረጃ ለሚሠለጥኑ ዕጩ መምህራን የተዘጋጁ ሞጁሎች፣ ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ፡ አዲስ አባባ።

2. ዴቪድ ዋርነር (1996)፡ የመንደራችን አካል ጉዳተኛ ሕፃናት፡ ለማሕበረሰብ የጤና ሠራተኞች፤ ለተሃድሶ ሠራተኞችና ለቤሰቦች የተዘጋጀ መመሪያ፡ ትርጉም ሃንዲካፕ ኢንተርናሽናል ከሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚ/ር ጋር በመተባበር፡አዲስ አባባ ኢትዮጵያ።

3. Geareheart W., & Geareheart J. (1988). The Exceptional Students in regular classroom (4th ed.). Columbus: Merill Publishing Company.

4. Guranick, & Bennett E. (1987). The Effectiveness of early Intervention for at Risk and Handicapped Children. Orlando, Florida: Academic Press, Inc.

5. ማሞ መንገሻ (1990) የተለየ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች በመደበኛ ትምህርት ቤት በቅንጅት ማስተማር ለመምህራን ማሰሠልጠኛ ተቋማት አስልጣኞች የተዘጋጀ ፅሑፍ/ ትምህርት ሚ/ር።

6. ምኒልክ ደስታ (1989) የአዕምሮ ዕድገት፡ ዝግመት የኢትዮጵያ የአዕምሮ ዕድገት ዝግመት ያለባቸው ሕጻናትና ወጣቶች ብሔራዊ ማሕበር በሲዊድን ህፃናት አድን ድርጅት ትብብር የተዘጋጀ አዲስ አባባ፡ ኢትዮጵያ።

7. ሳንድይ ኒይማን ዴቮራህ ግሪንስቴን ዳርሌና ዳቪድ ትርጉም መኮንን ሙላት (1998) መስማት የተሳናቸው ሕጻናትን መርዳት፡ መካነ የሱስ የተሳናቸው ት/ቤት ሆሳዕና።

8. Tirussew T. (2000). Human Disabilities: Development, Educational & Psychological Implications. Department of Educational Psychology. AAU, Ethiopia.

9. Ysseldyke and Alggozzine. (1995). Special Education: A Practical Approach for Teachers (3rd ed). Houghton, Muffl ln Company, Boston Massachusetts.